## የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን

# ተሐድሶ

ቅጽ አንድ

### ሳታድግ ያረጀች የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን

ፀጋአብ በቀለ

Million Belete
Private Library

Please Read
and RETURN

ሚያዝያ ፩፲፮ ዓ.ም

ሐዋሳ

Copyright© 2014 Tsega-Ab Bekele
All right reserved

*መጀመሪያ እትም ሚያዝያ ፳፻፮ ዓ.ም*

**አዘጋጅና አሳታሚ**
**ፀጋአብ በቀለ**

*የአሳታሚው የጽሑፍ ፈቃድ ካልተሰጠ በስተቀር መጽሐፉን በከፊልም ሆነ በሙሉ ማባዛትና ማሠራጨት በሕግ የተከለከለ ነው።*

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተወሰዱት ከመጀመሪያው እትም የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። የዘመን አቆጣጠርን በተመለከተ የአውሮፓውያን የዘመን አቆጣጠር (እ.ኤ.አ) በማለት እንዲሁም የኢትዮጵያ የዘመን አቆጣር ደግሞ (ዓ.ም) በማለት ተለይተዋል።

**ጥያቄ፣ አስተያየትም ሆነ ሒስ ካለዎት**
**ጸሐፊውን በሚከተለው አድራሻ ሊያገኙ ይችላሉ**

**ፀጋአብ በቀለ**
የመ.ሣ. ቁ 1077፤ሐዋሳ፤ ኢትዮጵያ
*email; tehadeso2006@gmail.com*

የሽፋን ዲዛይን - ዘካርያስ ገርማ
ትሽን ዲጂታል ስቱዲዮ - ሐዋሳ
0911945840/0916116674
*email;dcawassa@gmail.com*

# የቀደሚ አንባቢያን አስተያየት

ብስለት ባለው ሁኔታ በተዘጋጀው በዚህ መጽሐፍ ወንድማችን ፀጋአብ በቀለ የእግዚአብሔርን ቃል፥ የታሪክን እውነታ፥ የሌሎች ሰዎችን ጥናቶችና ልምዶች፥ እንዲሁም ነባራዊ የሆኑ ዓለም አቀፋዊና አገራዊ ሁኔታዎችን በመዳሰስ እውነተኛው መጽሐፍ ቅዱሳዊና መንፈሳዊ ተሐድሶ ምን እንደሚመስልና ለዚህም ተሐድሶ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለምንና እንዴት መነሣት እንዳለባት ያስተምራል። ይህም የተሐድሶ ደወል ከታሪክ እንድንማር፥ የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን አንድነት ለመገንባትና ለመጠበቅ ሊያስከፍል የሚችለውን ዋጋ ሁሉ እንድንከፍል፥ የግል ሕይወታችንንና የቤተ ክርስቲያን አሠራሮቻችንን ንጹህና ቅዱስ በሆነው በእግዚአብሔር ቃል እንድንፈትሽና እንድናጠራ፥ በመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ላይ በመታነጽ ለአገራችን ሁለንተናዊ ዕድገት ተግተን እንድንሠራ፥ እንዲሁም በዓለም አቀፋዊው የወንጌል ተልእኮ ላይ ያለን ድርሻ የጎላ እንዲሆን ከፍተኛ የሆነ ድምጽ ያሰማል። እንግዲህ በዚህ መጽሐፍ ደራሲው እውነትን በድፍረት ይናገራል፤ በእግዚአብሔር ቃል የበላይነትና በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ላይ የተመሠረተ እውነተኛ የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶን ይናፍቃል፤ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን አንዲት እንደሆነችና በአገራችን የክርስቶስን ስም የሚጠሩ ሁሉ በአንድነት መኖርና ማገልገል እንዳለባቸው ያምናል፤ እንዲሁም ከራሳችን አልፈን ሌሎች አገሮችን እንድንጠቅም ራእይ ይሰጣል። መጽሐፉን የሚያነቡ ሁሉ የአመለካከትና የሕይወት ለውጥ እንደሚያገኙ፥ ራእያቸው እንደሚሰፋ፥ ስንዴውን ከእንክርዳድ መለየት የሚያስችል ዕውቀት እንደሚቀስሙ፥ በሕይወታቸው ክርስቶስን ለመምሰል እንደሚያድጉ እርግጠኛ ነኝ፤ ጸሎቴም ነው።

በቀለ ሻንቆ *(ፒ.ኤች.ዲ)*

**የካምፓስ ክሩሰድ ፎር ክራይስት ዓለም አቀፍ ምክትል ፕሬዚዳንት - ዩ.ኤስ.ኤ**

በብርቱ የተሐድሶ ናፍቆት የጋለ፤ በጠቃሚ ንባባት የደለበ፤ በአገራችን ስላሉት ሁሉም አብያተ ክርስቲያናት እንድናስብ የሚጎተጉተን፣ የተሐድሶ ጉዳና የሚጠቁም ወቅታዊ ጥሪ ነው። ስለ አገርና ስለ ቤተ ክርስቲያን ይገደኛል የሚል ሁሉ ሊያነበው ይጠበቅበታል። ለወንድማችን ፀጋአብ አሁንም ጸጋውን ይጨምርልን እያልሁ እመርቃለሁ።

ንጉሤ ቡልቻ

የኢትዮጵያ ቃለ እግዚአብሔር አንባቢያን ማኅበር ዋና ጸሐፊ

ይህ መጽሐፍ ያለፈውን ታሪክ ብቻ ሳይሆን በ21ኛው ክፍለ ዘመን በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ፊት የተደቀኑ እንቅፋቶችንና ዕድሎችን ለታሪክ አጥኚዎች፣ ለነገረ መለኮታውያን፣ ለፖለቲከኞች፣ ለአስተማሪዎች፣ ለተማሪዎች፣ ለሰባኪዎችና ለሕዝበ ክርስቲያኑ በቃሉ የተፈተነና በጠንካራ ጥናት የተረጋገጠ እውነት በገሃድ ያሳያል፤ ለለውጥና ለተሐድሶ በምክንያታዊነት በድፍረት ይሞግታል፤ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከከበባት መንፈሳዊ እርጅናና ሞት የመውጫው መንገድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ተሐድሶ ብቻ እንደሆነ አበክሮ ያስረዳል:: በእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ሊነበብ የሚገባ ታላቅ የዘመኑ መጽሐፍ!

**ተክለአብ ሽብሩ (ፒ.ኤች.ዲ)**

**አሜሪካ ተኔስኢ ስቴት ዩኒቨርሲቲ - ረ/ፕሮፌሰር**

ወንጌላዊ ፀጋአብ በቀለ *"የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ"* በሚል ያዘጋጀው ይህ መጽሐፍ የተሐድሶን መጽሐፍ ቅዱሳዊነት ታሪካዊነት መሠረት በያዘ መልኩ የአገራችን ቤተ ክርስቲያን ሁለንተናዊ ተሐድሶ በጉጉት በሚናፍቅ ልብ አቅርቦልናል:: የተሐድሶ ያለህ! ብሎ ለሚጮህ ትውልድ በጊዜው የተወለደ ወቅታዊ መጽሐፍ ነው፤ ፀግሽን ጌታ ይባርከው::በዚህ ትውልድ ሊነበብ የተገባው መጽሐፍ ሆኖ አግንቸዋለሁ::

**ጎሣ እሼቱ**

**በኢትዮጵያ ወንጌላውያን ተማሪዎችና ምሩቃን ማህበር (ኢቫሱ)**

**የደቡብ ቢሮ አስተባባሪ**

ይህ መጽሐፍ በ21ኛው ክፍለ ዘመን ያለችው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከታሪክ ስህተት እንድትማርና ያለችበትን ዘመንና ትውልድ ተረድታ ወደፊት መንቀሳቀስ ትችል ዘንድ የተጻፈ ነው:: ድህረ ዘመናዊ በሆነ ትውልድ መካከል እግዚአብሔር ለቤቱ አገልግሎት እንዳስነሣቸው የሚያምኑ አገልጋዮች በሙሉ ይህን መጽሐፍ ቢያነቡ ብዙ ጥቅሞችን እንደሚያገኙ እምነቴ የጸና ነው::

**ኢንጅነር ሉሉ ጫንዶ**
**የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ መምህር**

ከ18 እስከ 25 ዕድሜ ያለው ቤተ ክርስቲያንንም ጨምሮ ማንኛውም ድርጅት ራሱን ካላደሰ ዘለቀታ እንደማይኖረው ምሁራኖች በአጽንኦት ይገልጻሉ:: ወንድማችን መጽሐፉን ለንባብ ሲያበቃ የማንቂያ ደወልን በእጃችን ማስገባቱ ነው:: የተሐድሶን ምንነት፣ ለምንነት፣ እንዴትነትና መቼነት በትክክል ያነበበ አስነባቢ መሆኑን በግሌ ተረድቼዋለሁ:: *"አገር ሲያረጅ ጃርት ያፈራል"* እንዲሉት ያለጊዜው እርጅና ተጫጭኖን የተላበስነውን ማንነትና ያፈራነውን አላስፈላጊ መራራ ፍሬዎች አስወግደን እንድንታደስ ጥሪ አቅርቦልናል:: እናንብበው፣ እናስነብበው፤ ያነጋግረን እንነጋገርበት::

**መጋቢ ተስፋዬ ነንቆ**
**በደቡብ አፍሪካ ፍሪ ስቴት ዩኒቨርሲቲ**
**የነገረ መለኮት ፒኤችዲ ተማሪ**

ጸሐፊው በእግዚአብሔር ቃል ላይ መሠረት በማድረግ በብዛታቸውም ሆነ በጥራታቸው እጅግ የላቁ መጻሕፍትን መዳሰሱና ማጣቀሱ፣ በስሜታዊነት ሳይሆን በምክንያታዊነት ላይ ማውጠንጠኑ፣ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የተሐድሶ እንቅፋቶችን ፈልፍሎ በማውጣት ከቃሉ መፍትሔን ማመልከቱ፣ አስደናቂ ታሪካዊ ፍሰቱና እንዲሁም ሚዛናዊነቱ ይኼን መጽሐፍ ልዩ አድርጎታል።

ሰለሞን በርሔ ተድላ
የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ
የታሪክና የቅርስ አስተዳደር ትምህርት ክፍል መምህር

ማንም ለውጥ ናፋቂና ተሐድሶ ጩኸት በውስጡ የሚያስተጋባ ሁሉ ሊያነበው የሚገባ በብዙ ድካምና ጥንቃቄ የተዘጋጀ ድንቅ መጽሐፍ መሆኑን ባገኘሁት የማንበብ ዕድል ለመገንዘብ ችያለሁ። ያለምንም ማጋነን ሳይሰለች እስከ መጨሻው ገጽ በታላቅ ጉጉት ሊነበብ የሚችል መሳጭና እያንዳንዱ ሰው ቆም ብሎ ርዕስ ጉዳዩ የራሱ እንደሆነ እንዲገነዘብ የሚያግዝ ሞጋችና በጥናት የተደገፈ መጽሐፍ ነው። አንብቦ ለተጠቀመበት ሁሉ ለራሱ ብቻ ሳይሆን ለቤተ ክርስቲያንና ብሎም ለአገሩ መፃኢ ዕጣ ፈንታ የራሱን በጎ አስተዋፅኦ እንዲያበረክት የሚግዝ ነው።

ቄስ መሠረት መሻገሪያ
ሐዋሳ ታቦር መካነ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን

የእግዚአብሔርን ቃል እኛ በፈለግነው መስቀያ ላይ ለማንጠልጠል የእውነት ማድበስበሻ እና ጭብጥ አሳቡን ማሳቻ መንገዶችን ስንፈልግ የመንፈስ ቅዱስን አሳብ ስንቃወም ተገኝተናል፤ ዕድሜ ጠገብ ውሸቶችን እንደ እውነት በመቁጠር የጽድቅ መንገድ አድርገናቸው እግዚአብሔር በልጁ ካዘጋጀልን ጽድቅ ክብር እንደጎደልን ይህ መጽሐፍ የማይካድ እውነት በገሃድ ይናገራል። የአገሬ ሕዝብ ጽድቅ እንደራበው ዘመኑን እንዳይጨርስ የተጻፈውን ይህን መጽሐፍ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ያንብብ።

ወንድም መኮንን ደጉ በላይ
የሻሸመኔ ሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ

ይህ መጽሐፍ ቤተ ክርስቲያን በታሪክና በዕድሜ ብዛት ሳይሆን በቅዱስ መንፈስና በቃሉ ምሪት፣ በፍቅርና በእምነት በሚታደርገው እርምጃ ለራሷ ታድሳ ሁለንተናዊ ተሐድሶ የምታመጣበትን መንገድ ያሳያል። በዕድሜያቸው ትንሽ ቢሆኑም እንኳ ለአገራቸው ሁለንተናዊ ለውጥና ለዓለም መልካም ተጽዕኖ ምክንያት እየሆኑ ያሉትን የደቡብ ኮሪያና የቻይና ቤተ ክርስቲያንን ሕያው ምሳሌነት በመጥቀስ ያስቀናናል።

ታደለ ጥላሁን
የሕግ አማካሪ

ኢትዮጵያ በርካታ አዳዲስ አስተሳሰቦችን በየወቅቱ ከተጋፈጡ አገራት አንዷ ነች። ከዚህ አንጻርም የዘርፉ ምሁራን ዘመን የተጠቀመባቸው ዕሳቤዎች ለማስተዋወቅ በአንድ በኩል ባሕል ወለዱን ኃይል በመፍራት አዝጋሚ የሆነ ተለምዶአዊ የለውጥ ዘዴ አማራጭን በሌላ በኩል ደግሞ በየቦታው ፈጣን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ለውጦች የሚፈነጥቁ ተምሳሌታዊ የለውጥ አብዮትን ሲሹላት ይታያሉ። የኢትዮጵያ ታሪክ ግን ሁለቱም አማራጮች ተስፋ በሚያስቆርጥ ሁኔታ ያልተሳኩ መሆናቸውን ፍንትው በማድረግ ያስረዳል። አዝጋሚነቱ ባሕላዊ ያሰመሰወጥን፤ አብዮታዊነቱ ደግሞ አላስፈላጊ ውድ ዋጋዎችን አስከፍሎአታል። ኢትዮጵያ ያልተፈተሸ አገረ-ወለድ ባሕልም ሆነ ደም አፍሳሽ መዳረሻ የለሌው እሳተገሞራዊ ለውጥ አያስፈልጋትም፤ አያሻትም። ነገር ግን ከራስ ከውስጥ የሆነ ሁለንተናዊ ለውጥና ሽግግር በብዙ ያሻታል። የፀጋአብ በቀለ "ተሐድሶ"ም ለእንዲህ ዓይነቱ ለውጥና ሽግግር ግልጽ ደፋርና ተገቢ አቅጣጫ አመልካች ነው። ለዚህ ስኬቱም "እንኳን ደስ አለህ" ልለው እወዳለሁ።

**ግርማ መሐመድ (ፒ.ኤች.ዲ)**
**በቤልጅየም የባሕል ፍልስፍና ረ/ፕሮፌሰርና የ"*Understanding Religion and Social Change in Ethiopia*" መጽሐፍ ደራሲ**

መጽሐፉ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን የትናንትና የዛሬ ገጽታዎችን በጥናትና በመረጃ አስቃኝቶን የክርስትና ልኩት በሆነው የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት በመፈተሽ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ሕይወትና የሞት ጉዳይ መሆኑን ይተነትናል። ወንድማችን ችግሮቻችንን እከኩ ከማለፍ ይልቅ በድፍረት በማፍረጥ የተሐድሶን ምንነትና እንዴትነት በመጽሐፍ ቅዱስ አንጻር በማመልከት ለተሐድሶ ናፋቂ ትውልድ አቅጣጫን አመልካች፣ ወሳኝና ወቅታዊ መሣሪያ አቀብሎናል። እሮጌ ነገር የሰለቸውና ተሐድሶ የናፈቀው ሁሉ ሊያነበው የሚገባው ድንቅ መጽሐፍ።

**ወቹ ቦሩ**
**በመካነ ኢየሱስ ሴሚናሪዮም የ2ኛ ዲግሪ የነገረ መለኮት ተማሪ**

በአገራችን ለቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ የተከፈለ የደም ዋጋና ለኢትዮጵያ ሁለንተናዊ ተሐድሶ መሠረቱ የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ መሆኑን በመገንዘብ በመንፈሱ ታድሼ ለቤቱ ተሐድሶ ይበልጥ ራሴን መስጠት እንዳለብኝ በቃሉ የተፈተነ፣ በጥልቅ ጥናት የተከሸነና የማያወላዳ ነገር እውነት በርቶልኛል። የግድ መነበብ ያለበት መጽሐፍ!

**መጋቢ በለጠ ሃጃሉ**
**የሀዋሳ ከተማ ዞን ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት ዋና ጸሐፊ**

ይህ መጽሐፍ የአገራችንን ቤተ ክርስቲያን ለለውጥ የሚጋብዝና አሁን የሚታየውን የተሐድሶ ዕድል ባትጠቀም በሌሎች ዓለማት እንደተከሰተው ሁሉ አሁን ካለችበት የባሰ ክፉ አደጋ እንደሚጠብቃት ቃሉን መሠረት በማድረግ በግልጽ ያስጠነቅቃል። የተሐድሶ መሣሪያ ለመሆን ራሳቸውን የሰጡ ሁሉ ሊያነቡት የሚገባ፣ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የዘመናት ጓዳ ጎድጓዳ የፈተሸና በገሃድ ለሁሉም ያሳየ የዘመኑ ድንቅ መጽሐፍ እንደሆነ ከልብ እምናለሁ።

**ያዕቆብ ዙላ**
**የሐዋሳ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ መምህር**

ባለራእይነት ክፍል አንድና ሁለት ካነበብኩ በኋላ ከፍተኛ ተጽዕኖ ፈጥሮብኝ ከመጻሕፍቱ ደራሲ ከሆነው ከወንጌላዊ ፀጋአብ በቀለ ጋር በአካል ባንተዋወቅም ልጽፍለት ተገደድኩኝ። ለህትመት እየበቃ ያለውን *"የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ"* የሚል ቀጣዩን መጽሐፍ ለማንበብ በውስጤ የተፈጠረውን ብርቱ ረሃቤን ገለጽኩለት። ይህን መጽሐፍ መጀመሪያ ለማንበብ ከበቁት ጥቂት ሰዎች አንዱ በመሆኔ ትልቅ ደስታ ተሰምቶኛል። ይህ መጽሐፍ ክፍለ ዘመኑን የሚመጥን፣ በወሳኝ ጊዜ፣ ለወሳኝ ትውልድ የተደረሰ በዓይነቱ ልዩና አስደናቂ መጽሐፍ ነው። በግምት፣ በመላምትና በግላዊ ቁንጽል አመለካከት ላይ ሳይሆን በእግዚአብሔር ቃል፣ በጥልቅ ታሪካዊ ጥናትና ትንተና ላይ ተመርኩዞ እውነትን ሳያመቻምች ለአንባቢያን በድፍረት ይናገራል። ስታነቡት የለውጥና የተሐድሶ ራእይን ይዛችሁ ለተግባር እንዲትነሡ የግድ ይላል። እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ይህን መጽሐፍ ማንበብ አለበት።

**ቦሻ ቦንቤ**  
**በአርባ ምንጭ መምህራን ትምህርት ኮሌጂ**  
**የታሪክ መምህርና ተመራማሪ**

እንደዚህ ዓይነት ድንቅ የሆነና በመረጃ የፋፋ መጽሐፍ ማግኘት ብዙ መጻሕፍትን እንደማገላበጥ ያህል ስለሚጠቅመን የማይታለፍ ድንቅ መጽሐፍ አግኝተናልና ሁላችን እንድናነበው ብቻ ሳይሆን እንድናጠናው እጋብዛለሁ።

**ደረጀ ኃይሌ**  
**የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ**  
**የሥነ ጽሑፍ (ፒ.ኤች.ዲ) 4ኛ ዓመት ተማሪ**

ይህን መጽሐፍ በጥንቃቄ አንብብያለሁ። ቃሉንና ታሪካዊ መረጃን መሠረት በማድረግ በቀረበው ግልጽ የለውጥ ጥሪ ለልቤ ደርሷል፤ እንዲሁም ብዙ ተምረበታለሁ። እግዚአብሔር ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ በቃሉ ታጥቀን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እርምጃን እንድንወስድ እጠራን እንደሆነ ተሰምቶኛል። መጽሐፉ በቃሉ ላይ እውነተኛ እምነት ላላቸው ድፍረትና ኃይል የሚሰጥ፣ የተሐድሶና የለውጥ ጠንካራ መሠረት ጣይና የቤተ ክርስቲያን ባላንጣን ምሽግ የሚያሳይ የመንፈሳዊ የጦርነት ካርታ ነው። በዘመኑ የለውጥና የተሐድሶ መሣሪያ እንዲሁም ለአገርና ለቤተ ክርስቲያን የበረከት ምክንያት ለመሆን ራሳቸውን ያዘጋጁ የዚህ ዘመን ታሪክ ሠሪዎች ሁሉ እንዲያነቡ እጋብዛለሁ።

**ዘርሁን ገብሬ**  
**የመካነ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን**  
**የክርስቲያን ትምህርትና የነገረ መለኮት ክፍል ተጠሪ**

# መታሰቢያነቱ

የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ጥያቄን እንደ እግዚአብሔር ቃል አንግበው በመነሣታቸው ሰማዕት ለሆኑት ለአባ እስጢፋኖስ፣ ለደቂቀ እስጢፋኖስ፣ ለአለቃ ታዬ እንዲሁም የእነርሱን ዱካ በመከተል ዛሬም እየተወገዙ፣ እየተሰደቡ፣ እየተሰደዱና የባሕርይ ገደላ እየተካሄደባቸውም እንደ እበው ቃሉ ላይ ቆመው ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ መልካሙን የእምነት ገድል በመጋደል ላይ ላሉት የእምነት አርበኞች ሁሉ ይሁንልኝ።

# ማውጫ

ምስጋና xiii
መቅድም (በአጬ ዶ/ር ደረጀ ኃይሉ) xiv
መግቢያ xvi

## ክፍል አንድ

## የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ታሪክ

**፩ የቤተ ክርስቲያንና የተሐድሶ ምንነት 20**

የቤተ ክርስቲያን ምንነት 20
የተሐድሶ ምንነት 22
*የተሐድሶ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት* 24
*ተሐድሶ የሚለውን ቃል በትክክል እንረዳ* 25
*ሦስቱ የተሐድሶ የእንግሊዝኛ ቃላት ፍቺዎች* 26
የመነቃቃት ምንነት 29
የመነቃቃትና የተሐድሶ ልዩነት በንፅፅር 33
ተሐድሶ ጠሪ የኢትዮጵያ የቤተ ክርስቲያን ነባራዊ ሁኔታ 34
የተቀየጠ ክርስትናችን 36
አስማት በክርስትና ጥላ ሥር 38
የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን 43
ኢመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮዎች 46
የተለጠጠ ነገረ ማርያም 46
*"ያለ እመቤታችን ዓለም አይድንም"* 48
*"ያለ እመቤታችን ሥላሴ አይታወቅም"* 48
*"ሁሉም በእርሷ (በድንግል) ሆነ"* 49
*"የእመቤታችን ስም የሚጠራ አያፍርም"* 49
*"ቤዛዊት ዓለም ቤዛዊት ኩሉ"* 49
*ተአምረ-ማርያም የተዛባ የነገረ ማርያም መሠረት ነው* 52
*የመጽሐፍ ቅዱስ ምንነት* 56
የአማርኛና የኦሮምኛ መጽሐፍ ቅዱስ አጭር ታሪክ 56
ስደት የጠገበ መጽሐፍ 57
"ስማንያ አሐዱ- በቃሉ ሲመዘን" 59
"ገመና ዘቮቬዱ" 59
የፕሮቴስታንት እብያተ ክርስቲያናት 64
አደጋዎች 64
ብሔርተኝነት የተስፋፋበት ካምፕ መምሰሉ 66
የነቀዘ የአሠራር ዋሻ 70

**፬ ከሉተር የቀደሙ የተሐድሶ ጥያቄዎች በኢትዮጵያ** **85**

የዐፄ ያግበ ጽዮን ዘመን (1278 - 1286) 85
የደቂቀ እስጢፋኖስ ዘመን 87
የአባ እስጢፋኖስ በዐፄ ይስሐቅ ተቀባይነት ማግኘት 87
የአባ እስጢፋኖስ በዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ችሎት ስለመወገዛቸው 88
የአባ እስጢፋኖስ ሰማዕት መሆን 93
የደቂቀ እስጢፋኖስ በጳጳስ ፊት 95
የደቂቀ እስጢፋኖስ የማሰቃያ/መግደያ/ መንገዶች 98
ከሰማዕት ደም የተወለዱ ሰማዕታት 101
ዘግናኙን ግድያ ያነበቡ ምን አሉ? 102

**█ የዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ማንነት** **104**

የዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ መልካም ሥራዎች 104
የዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮዎች 105
በእርሱ ዘመን የተፈጠሩ የኑፋቄ ትምህርቶቹ? 106
ኢሰብዓዊ ድርጊቶቹ 108
ሚስቶቹና ቁባቶቹ 111
ለአባቶች ምክር ቦታ አልነበረውም 114
ዘርዓ ያዕቆብና ቤተ ክርስቲያን 115
ዘርዓ ያዕቆብና ማርያም 118
ሌሎች ስለ እርሱ ምን አሉ? 120
ሰይፍ ወደ ሰገባው ይመለስ 125

**፮ "የቀዳሚ ምሁር" የተሐድሶ ሐሳብ** **127**

አለቃ ታዬ ገብረማርያም /1853 - 1916 ዓ.ም/ 127
"እኔ ለእምላክ እንጂ ለሥዕል አልሰግድም!" 131
የአለቃ ታዬ ሥራዎች 132
አለቃ ታዬ ለአገር የነበራቸው ታላቅ ራእይ 133
የአለቃ ታዬ ተቀባይነት ማጣት 134
የአለቃ ታዬ ዜና ዕረፍት 134
የአለቃ ታዬ እህት ሙሸ 137
የአለቃ ታዬ አጽም ለውግዘት? 139

**፯ የዘመናችን የተሐድሶ እንቅስቃሴ** **142**

"የፕሮቴስታንት ቅጥረኞች" 142
"የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ልጆች ነን" 144
የአብያተ ክርስቲያናት አንድነትና ልዩነት 148

**፰ ያልታደሰው ክርስትናችን የዕድገታች ሞጋች** **152**

ክርስትናችን ራስ ተኮር መሆኑ 153
ክርስትና በስብከት ወይስ በኃይል? 154
*የኦርቶዶክስ ክርስትና በካፋ* 157

ተሐድሶ ለዓለም ለውጥ ምክንያት ሆኗል 258
ተሐድሶ ሃይማኖትና እምነትን ለያይቷል 260
ተሐድሶ በዓለማችን የሥራን ባሕል ለውጧል 261

**፲ ክርስትና የዓለም የሕዳሴና የዕድገት መሠረት ነው 265**

ደቡብ ኮሪያ 265
የኢትዮጵያ አርበኞች የደም ዋጋ ለደቡብ ኮሪያ ነፃነት 265
የክርስትና ሚና ለደቡብ ኮሪያ ዕድገት 266
*የደቡብ ኮሪያ ዲያስፖራና የሚሲዮናዊነት ራእይ* 268
*ክርስትና ለደቡብ ኮሪያ ማኅበረሰብ ለውጥ* 269
*ክርስትና ለደቡብ ኮሪያ ኢኮኖሚ ዕድገት* 269
*ደቡብ ኮሪያውያን ዛሬ በዓለም በምን ይታወቃሉ?* 271
*ለደቡብ ኮሪያ የጠቀመው ክርስትና ለኢትዮጵያ ለምን?* 272
ክርስትና ለቻይና ኢኮኖሚ ምጥቀት 274
*የቻይናውያን ዓለምን በወንጌል የመድረስ ራእይ* 276
*የቻይና ሁለንተናዊ ለውጥ በመስቀል* 277
*ከቻይና ክርስትና ምን እንማራለን?* 278
ክርስትና ለምዕራቡ ዓለም ሁለንተናዊ ዕድገት 280

**፲፩ የተሐድሶ ጥሪ ለኢትዮጵያ ፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያናት 283**

ጥንት ቤተ እምነት አልነበረም 285
ቤተ እምነት ምንድነው? 287
ቤተ እምነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት የለውም 288
ቤተ እምነትና ማዕከላዊነት 289
የእግዚአብሔር ሰዎች ስለ ቤተ እምነት ምን ብለዋል? 290
የኢትዮጵያ ቤተ እምነቶች ሁኔታ 292
የተሐድሶ አስፈላጊነት ለፕሮቴስታንቶች 293
ተሐድሶ የሚፈልጉ ዐበይት ጉዳዮች 295

**፲፪ የቤተ ክርስቲያን እርጅና፣ ሞትና ተሐድሶ 300**

የደከሙ ኃያላን 303
በሞት ሂደት ላይ ያለች ቤተ ክርስቲያን ምልክቶች 303
ቤተ ክርስቲያን ከልደት እስከ ሞት 8 ደረጃዎች 305
የቤተ ክርስቲያን ሞት? 308
የቤተ ክርስቲያን ትንሣኤ 310
በብዙ ዕድሎችና አደጋዎች ተከበናል 312
የዓለም ዓይን በአፍሪካ ላይ ነው 315

**ማጠቃለያ 317**
**ዋቢ መጻሕፍት 322**
**የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች 333**
**መጠቁም 337**

# ምስጋና

ከሁሉ በማስቀደም በልጁ ሞትና ትንሣኤ አድኖኝ የኪዳኑ ልጁ ያደረገኝን፣ ወንጌልን እንድሰብክ ጥሪው ስገርመኝ ብዕሬን ለስሙ ክብር እንዳነሣ የመጻፍ ሸክም ጊዜ፣ ትጋትና ትዕግሥት የሰጠኝ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ።

ወንጌልን ከመስበክና ከማስተማር የመኖር ዓላማዬ ጋር በልቤ እየተቀጣጠለ የመጣው የጽሑፍ ሥራ ሰፊ ጊዜን፣ ብርቱ ትጋትንና ጥንቃቄ እንደሚፈልግ የታወቀ ሲሆን ሁለቱን አብረ ማስኬድ እንድችል በጎኔ ብዙዎች ተሰልፈዋል። በተለይ ውድ ባለቤቴ ቲያ ዳቃና ከልብ የሚንወዳቸው ልጆቻችን ትሁት፣ ሩት፣ ሚናሴና ልዕልት ብዙ ጊዜዬን በተለያዩ ቦታዎች በአገልግሎት አሳልፌ ቤት ስመለስ እንኳ ትንሹን የእነርሱን ጊዜ በመቀማት ቀንና ሌሊት በኮምፒዩተር ላይ ተጥጄ ይህን መጽሐፍ ስጽፍ ፍቅርና ጥንቃቄያቸው ትልቅ ጉልበት ሆኖኛል። ከልብ አመሰግናቸዋለሁ። በዚህ መጽሐፍ ሥራ የተሳተፉ ሰዎችን ብዛት ሳስብ የሁሉንም ስም መጥቀስ አልችልም። በጸሎታችሁ፣ በምክራችሁና በገንዘባችሁ ለዚህ ዘመን ተሻጋሪ ሥራ ከእኔ ጋር የቆማችሁ፣ እንዲሁም ቀዳሚ መጽሐፎቼን በማንበብ በጽሑፍ እንድበረታ የሞራል ስንቅ ያቀበላችሁኝን ሁላችሁንም ከልብ አመሰግናለሁ።

የዚህን መጽሐፍ ረቂቅ በማንበብ፣ በማረምና ገንቢ አስተያየት በመስጠት ብዙ ያስተማሩኝን የታሪክ ፕሮፌሰር ላጵሶ ጌ.ድሌቦ፣ አባቴ ዳቃ ጅሎ፣ እጩ ዶ/ር ደረጀ ኃይሌ፣ ኢንጅነር ሎሎ ጨንጄ፣ መምህር ሰሎሞን ቤርሔ፣ መምህር ኤፍሬም ጉሉፎ፣ መምህር አባይነህ ተናሸ፣ ቄስ መሠረት መሸሻ፣ ወንድም ዘርሁን ገብረ፣ መጋቢ በለጠ ሃይጃሎ፣ ወንጌላዊ ወቹ ቦሩ፣ ወንድም መኮንን ደጉ፣ የሕግ ባለሙያ ታደለ ጥላሁን፣ መምህር በሻ ቤንበ፣ መምህር ያዕቆብ ዘላ እንዲሁም ከባሕር ማዶ ጠቃሚ ምክር የለገሱኝ አብሮ አደግ ጓደኛዬ ረዳት ፕሮፌሰር ተክለአብ ሽብሩ፣ ረዳት ፕሮፌሰር ግርማ መሐመድና የሕይወት እርምጃዎቹ ለእኔ ትልቅ ትምህርት ቤት ለሆነኝ ዶክተር በቀለ ሻንቆ ከልብ አመሰግናችኋለሁ። በአገልግሎቴ የሁልጊዜ አጋሮቼ የሆኑ መምህር ፍቅረሥላሴ ኃይሉና እህት ሹና አብዲን ከልብ አመሰግናለሁ። የመጽሐፎቼን ሽፋን ዲዛዬን በማደረግ *"በምስል የግድ ልሰበክ"* የሚለውና የሚኮራበት የአዋሳ አሸን ዲጂታል ስቱዲዮ ባለቤት ዘካርያስ ግርማን አመሰግናለሁ። በመስተግዶአቸውና በሥራቸው ጥራት የሚያስመኩ የርኆቦት አታሚዎች ይህ መጽሐፍ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ለንባብ እንዲበቃ ትልቅ ሥራ ሠርተዋል፤ ልባዊ ምስጋናዬ ለሁሉም ሠራተኞች ይድረሳቸው።

# መቅድም

ወንጌላዊ ፀጋአብ በቀለ በእግዚአብሔር ጸጋ የተሞላ፣ በመንፈስ የተቃጠለ፣ ለቤተ ክርስቲያንና ለአገር ዕድገትና ለውጥ ግብዓት ልሆን የሚችል እምቅ አቅም ያለው፣ በሚያስፈልገው ዕውቀትና ክህሎት የታጠቀ ዘመኑን የሚመጥን አገልጋይ ነው። እንደዚህ ዘመኑን የሚያውቁና ለመጪው ጊዜ ቤተ ክርስቲያንንና አገርን አቅጣጫ የሚያሳዩ አገልጋዮች እንደሚያስፈልጉን ሳይታለም የተፈታ ነው። ከሰው በላይ ትልቅ ስጦታ የለምና፣ እግዚአብሔር እያስነሣልን ስላለው ባለራእይ አገልጋዮች ልናመሰግነው ይገባል።

ወንድማችን በጻፋቸው *"ባለራእይነት ቁጥር 1 እና 2"* ምርጥ በአገራችን በብዙሃን እየተነበቡ ባሉ ድንቅ መጽሐፎቹ እጅግ በጣም እንደተባረክን ብዙዎች ይስማሙበታል ብዬ አስባለው። መጽሐፎቹ ልጆቹ እንደሆኑ ሁሉ ቁርጥ አባታቸውን ይመስላሉ። ለትምህርታችን ይሆን ዘንድ የሕይወቱን አቅጣጫ አመልካች ራእዩን በመጽሐፎቹ ላይ አስፍሮልናል። ይህም ስለራእይ ቀመራዊ ዕውቀት አቀባይ ብቻ ሳይሆን የተግባር ሰውነቱን ያመለክታል። ቀደምት ሥራዎቹ ከራእይና ከባለራእይነት ጋር በተያያዘ ውስብስብ የአገራችንን ታሪካዊ ዳራ በሚዛናዊነትና በድፍረት ፈልፍሎ፣ ገለባውን ከፍሬው በመለየት ለዛሬው ችግሮቻችን መፍተኼ ጠቋምና ለነገ የላቀ ራእይ እንዲኖረን አጋዥ መሣሪያዎች ናቸው። ሥራዎቹ የበሰሉና ብዙ አመት የተደከመባቸው እንደሆኑ በሚገባ ያስታውቃሉ። በአጠቃላይ ድንቅ የሕይወት ጭማቂዎች፣ ተግባራዊ የራእይና የባለራእነት ትምህርት ቤቶች፣ እንደ አንብበን የሚናስቀምጣቸው ሳይሆኑ ሁሌም የሚንጠቀምባቸው መመሪያዎች ስለሆኑ ደግመን ደጋግመን እናጥናቸው፤ የቀጣዩም ትውልድ ሀብት ናቸው።

ወንድማችን ፀጋአብ *"የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ቅጽ-1"* በሚለው በዚህ በሦስተኛው ድንቅ መጽሐፉም ርዕሰ ጉዳዩ አገራዊም አለም አቀፋዊም ነው። በዚህ ሥራው የቤተ ክርስቲያን፣ የተሐድሶና የመነቃቃት ምንነት፣ ባለፉት ስምንት ምዕተ ዓመታት የተሐድሶ ጥያቄና የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ምላሽ፣ በአገራችን የተስፋፋው ጫፍ የነካ የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ፍርሃት ሁኔታ፣ ለቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ አሉታዊ ምላሻችን በአገር ዕድገት ላይ ያመጣው አሉታዊ ተጽዕኖ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ተሐድሶን የፈቀዱ አብያተ ክርስቲያናት ለአገራቸው ዕድገት የተጫወቱት አንጸባራቂ ሚናና የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ጥቅም የእግዚአብሔርን ቃል መሠረት በማድረግ በመረጃና ጥልቅ ጥናት በማያወላዳ ሁኔታ አቅርቦልናል።

ተሐድሶ ልንፈራው ሳይሆን፣ ልንጠማውና ልንራበው የሚገባ ጉዳይ እንደሆነ በምክንያታዊነት እየሞገተ ያስተምራል። ከሞተ ነገር በቀር ፍጥረት ሁሉ ለውጥ ወይም ተሐድሶ ያስፈልገዋል። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶን በመግፋቷ ምን ያህል እራሷንና አገርን ወደኋላ እንዳስቀረች በዚህ መጽሐፍ ላይ በሚገባ በመረጃ ተደግፎ ተተንትኖዋል። ጆሮ ያለው ይስማ!

ይህ መጽሐፍ ከጠባብነትና ከኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ዘመን ዘለቅ መረዳቶቻችንና ልምምዶቻችን ጋር አጋጭቶን ያፋታናል፤ ሁላችን ለቃሉ ተገቢውን ሥፍራ በመስጠት ለአገር እቀፍ ሕዳሴ መሠረት ለሆነው የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ እንድንነሣ የግድ ይለናል። ለመጽሐፍ ቅዱሳዊ ክርስትና ይሟገታል። ከሁሉም በላይ የአገራችን ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ እንደቀረበ፤ ማንም እንደማያስቀረው የቤቱ አዳሽ እግዚአብሔር እራሱ እንደሆነና የእኛ ድርሻ ከእርሱ ጋር በእምነት ለመሥራት መነሣት እንደሆነ በመዘርዘር መለኮታዊ ጥሪ ለአንባቢያን ያቀርባል። ለዚህ ትልቅ አላማ በምድራችን አበ እምነቶች ታላቅ የደም ዋጋ እንደ ከፍሉና እኛም የተሐድሶን መከር ለመሰብሰብ ማንኛውንም ዋጋ ለመክፈል በቃሉና በመንፈሱ ታጥቀን እንድንነሣ ይመክረናል፣ እንቅፋት ለመሆን እንደ ለመድነው ከተነሣን ሳናወቅ ከእግዚአብሔር ጋር እንዳንታገል ያስጠነቅቀናል።

ጸሐፊው *"የቤተ ክርስቲያን የተሐድሶ ያለህ!"* እያለ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ይጮሃል፣ አብራችሁ ከኔም ጋር ትጮሁና ለተሐድሶ በሁሉም አቅጣጫ ትሰለፉ ዘንድ ይችን ድንቅ መጽሐፍ እንድታጠኑና ለምድራችንም ሁለንተናዊና እውነተኛ ለውጥ በትጋት እንድትጸልዩ፣ እንድትሠሩና ካስፈለገም እንድትሞቱላት በታላቅ ትህትና እጠይቃለው። እግዚአብሔር ምድራችንን ይባርክ።

ደረጀ ኃይሌ
የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ መምህር
የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሥነ ጽሑፍ ተመራማሪና
የአራተኛ ዓመት (Ph.D) ተማሪ

# እንደ መግቢያ

የሰውን የአካል አፈጣጠር ስናጠን ከማሕፀን እስከ መቃብር ያለው ሂደት በለውጥ(ተሐድሶ) የታጀበ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ለምሳሌ፦ *የሰው የሆድ ግርግዳ በየሳምንቱ ይታደሳል፤ በእያንዳንዱ ደቂቃ ከ200 እስከ 300 ግራም ገደማ አክስጅን ያስፈልገዋል፤ እንዲሁም የተቃጠለ አየር(ካርቦን አክሳይድ) ከሰውነቱ ይወገዳል፣ በየደቂቃው ከ160 ሚሊዮን በላይ ቀይ የደም ሰሎች በሰውነታችን ውስጥ ይፈጠራሉ፤ የዚያህኑ ያህልም ይሞታሉ፤ እንደ ብረት ጠንካራ የሆነ የሰው ልጅ አጥንት የራሱ ደም ሥርና ነርቭ ያለው ሲሆን ራሱን በራሱ እንዲያድስ ተደርጎ ነው የተፈጠረው፤ የአዋቂ ሰው አጥንት በየዓመቱ ከ10 በመቶ ያህል ራሱን ይተካል፡፡*[86] ይህ ታላቅና ድንቅ አሠራር የክርስቶስ የእጁ ሥራ ውጤት ነው፡፡ ለሰውነታችን ይህን ድንቅ የተሐድሶ መንገድ የፈጠረው ጌታ አካሉ የሆነች ቤተ ክርስቲያንን እንደሚያድሳት ቃሉን መሠረት ያደረገ እውነት በዚህ መጽሐፍ ቀርቧል፡፡ ብሔር፣ ሃይማኖት፣ የትምህርት ደረጃ፣ የፖለቲካ ርዕዮተዓለምና የዕድሜ ልዩነት ሳይገድባቸው ኢትዮጵያውያን ሁሉ ይህን መጽሐፍ ቢያነቡ በብዙ እንደሚጠቀሙ እርግጠኛ ነኝ፡፡

- በአገራችን በተለይ በቤተ ክርስቲያን አካባቢ እንደ ጦር የሚፈራውንና በአፍራሽነት የተፈረጀውን “ተሐድሶ” የሚለውን ቃል፣ ጽንሰ ሐሳቡን ከመጽሐፍ ቅዱስ አንጻር በትክክል ለመረዳት፤ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከእግዚአብሔር ዘንድ አቀጣጫ አመልካች የጊዜው መልዕክት ስለያዘች፣ ቤተ ክርስቲያን በዚህች አገር ታሪክ የተጫወተችውን አዎንታዊና አሉታዊ ሚና ለይቶ ለመረዳት፣
- በአውሮፓ ከተነሣው የፕሮቴስታንት ተሐድሶ ጥያቄ ቀድሞ በኢትዮጵያ የተነሣው ተመሳሳይ የተሐድሶ ጥያቄ በአሰቃቂ ግድያ ለጊዜው ቢዳፈንም፣ ዛሬም የተሐድሶ ጥያቄው ከጫፍ እስከ ጫፍ መቀጣጠሉን ለመረዳት፣
- የፕሮቴስታንት ተሐድሶ ለዓለማችን ሁለንተናዊ ዕድገት መሠረት ስለመሆኑ በመረጃ የተደገፈ በታሪክ የተረጋገጠ እውነት ስለሚያቀብለን፣
- የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ የኢትዮጵያ ሁለንተናዊ ሕዳሴ መሠረት ስለሆነ፣ ተሐድሶ የግድ መሆኑን ስለሚናገር፣
- ትውልድ ዘለቅ አሉታዊ ንዝረቶችንና ዛሬም እያሰቃዩን ያሉ ታሪካዊ የበደል እርሾን በአንድነት በንስሐ ለማስወገድ፣

የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ባለቤትና የቤተ ክርስቲያን ራስ የሆነው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፤ እርሱ ቤቱን የሚያድሰው በቃሉ፣ በመንፈሱና በሚታዘዙለት ልጆቹ ነው፡፡ ማርቲን ሉተር ኪንግ *“ለውጥ አይቀሬ በሆነው ሽክርክር ላይ ሳይሆን ቀጣይነት ባለው ትግል የሚገኝ ነው”* እንዳለት የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ የእግዚአብሔር ፈቃድ ቢሆንም ብርቱ መስጠትና በቃሉ

[86] Fran Stork (Dr.), Reader Digest- Sptember 2013

ቆሞ እውነት መሳይ ሐሰትን በብርቱ መጋፈጥን ይጠይቃል። የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ጥያቄ በአገራችን ላለፉት ስምንት ምዕተ ዓመታት የቀደሙ የእምነት አባቶቻችን ብዙ የእንባና የደም ዋጋ አስከፍሏል። ዛሬም የአባቶችን ፈለግ በመከተል በእግዚአብሔር ቃል ላይ ቆመው ቤተ ክርስቲያናችን መታደስ አለባት እያሉ ያሉትንም ውድ ዋጋ እየጠየቀ ነው። ታሪክ ስላለፈው ጊዜ መረጃ ላይ ተደግፎ መረጃውን እርስ በርሱ በማረጋገጥ የሚጻፍ ሐተታ እንደመሆኑ መጠን ይህ መጽሐፍ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የተሐድሶ ጥያቄ ሰፊው ታሪካዊ መረጃዎችን በማሰባሰብ በቃሉ ብርሃን ይተነትናል። መጽሐፉ ነባሩን መረጃዎች በማሰባሰብ ስለ ተሐድሶ አዲስ አመለካከት፣ አዲስ ራእይና እርምጃ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አስፈላጊነቱን ያመለክታል። ይህ መጽሐፍ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በእግዚአብሔር ቃል እውነት ላይ ታንጻ አገራዊና ዓለም አቀፋዊ ተጽዕኖ በማምጣት ከፍ ብላ እንዲትገለጥ የግድ ይላል፤ ካረጀው አሠራር፣ ከአገራዊ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ የትውፊት ሰንሰለት፣ ከሰዋዊ አስተምህሮ፣ ከምድር ተኮር ወንጌልና የብዙ አገልጋዮች መለያ እየሆነ ከመጣው "ገቢያ መር" የአገልግሎት ፍልስፍና ጋር አጣልቶን ለተሻለው ግጭት ውስጥ ያስገባናል። ሪክ ዋረን *"ዓላማ መር ሕይወት"* በሚለው መጽሐፋቸው እንዳሉት፡- *ማስታረቅ ግጭትን መሸሽ አይደለም። ከችግር መሸሽ፣ የሌለ ማስመሰል፣ ወይም ስለ ችግሩ ለመናገር አለመድፈር ፈሪነት ነው። የሰላም ልዑል ኢየሱስ ግጭትን ፈጽሞ አልፈራም። አንዳንድ ጊዜ ለሁሉም ይበጅ ዘንድ አለመግባባትን ቀስቅሷል። አንዳንዴ ግጭትን መፍጠር፣ አንዳንዴ ደግሞ ማስታረቅ ያስፈልገናል።...ሰላምን መፍጠር ላልተግባባነው ሰው የፈለገውን ማድረግ አይደለም።* ማለት ነው።

ይህ መጽሐፍ ስለ ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ሙሉ መልስ ባይኖረውም የመንደርደሪያ አሳብ እንደሚያቀብል እርግጠኛ ነኝ። በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ላይ የተዘጋጀው መጽሐፍ በሁለት ቅጽ የተከፈለ ሲሆን ይህ የመጀመሪያው መጽሐፍ ነው። ሁለተኛውም መጽሐፍ *"የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ - ቅጽ ሁለት"* በሚል ከዚህ መጽሐፍ ይከተላል። ቅጽ አንድ መጽሐፍ በዓይነቱ ልዩ የሚያደርገው፣ በቤተ ክርስቲያን መታደስ የሚያስፈልጋቸውን ነገሮች በቃሉና በጠንካራ መረጃ አስደግፎ በነቅስ በማመልከት፣ ለኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት በሙሉ ግልጽ የተሐድሶ ጥሪ ማቅረቡ ነው። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለተሐድሶ ካልተዘጋጀች ለሁለንተናዊ ዕድገትና በረከት ፋና ወጊ አትሆንም፤ እንደሚገባ የሰማይ መንግሥት ወኪልም መሆን አትችልም፤ የእስታትስቲካዊ ግዝፈት፣ የድርጅታዊ ጥንካሬና የቁሳቁስ ሀብታም ሆና መንፈሳዊ ሙት ትሆናለች።

**ቅጽ 1** መጽሐፍ በሁለት ክፍሎች የተከፈሉ አሥራ ሁለት ምዕራፎችን ይዟል። የመጀመሪያው ክፍል ***"የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ታሪክ"*** በሚል ዋና አሳብ ሥር ስድስት ምዕራፎች ተካተዋል። **ምዕራፍ አንድ፡-** የቤተ ክርስቲያንና የተሐድሶን ምንነት በሰፊው ይተነትናል፤ በተለይ የኢትዮጵያ የኦርቶዶክስና የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት ተጨባጭ ገጽታዎችን አሳይቶ ካልታደሱ ምርጫቸው ሞት እንደሆነ መራራ

እውነት ይናገራል:: **ምዕራፍ ሁለት:-** ከማርቲን ሉተር አስቀድሞ ተመሳሳይ የተሐድሶ ጥያቄ በአገራችን በነማን፣ የት እንደተነሣ በማመልከት የከፈሉትን የደም ዋጋ በመረጃ አስደግፎ ያስቃኛል:: **ምዕራፍ ሦስት:-** የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን የተሐድሶ ጥያቄ ያመከነና የተሐድሶ ጥያቄ ያነሡ ቀደምት አባቶችን በጭካኔ ያስጨፈጨፈ የዐፄ ዘርዓ ያዕቆብን ማንነት በሰፊው ይዳስሳል:: **ምዕራፍ አራት:-** ከኢትዮጵያ ቀዳሚ ምሁራን አንዱ የተባሉ አለቃ ታዬ እምነታቸውን፣ ለአገር የነበራቸው ግልጽ ራእይ፣ አስደናቂ ሥራዎቹን በማሳየት የተሐድሶን ጥያቄ በማንሣታቸውና ስለ እምነታቸው:- ለእንግልት፣ ለእሥራት፣ ለስደት፣ ለውግዘትና ለሞት የበቁበትን አሳዛኝ ታሪክ ይዟል:: **ምዕራፍ አምስት:-** በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የተሐድሶ የጥያቄ *"የሞትና ሕይወት"* ጉዳይ ሆኖ ብዙዎች መስዋዕት እንደሆኑና የተሐድሶ ጥላቻ በዘመናችንም የባሰበት ቢሆንም ዛሬም የተሐድሶ ጥያቄ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከመቼውም ጊዜ ይልቅ ዳብሮና ሰፍቶ የትውልዱን ልብ እንደያዘ ያስቃኛል:: **ምዕራፍ ስድስት:-** አገራችን ክርስትናን በመቀበል በዓለማችን ቀዳሚ ከሆኑት አገሮች አንዷ መሆኗን፤ ያልታደሰው ክርስትናችን የኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ልምምዶች ተጠቂ እንዴት እንደሆነ ያሳያል::

የቅጽ አንድ መጽሐፍ ሁለተኛው ክፍል ***"ዓለምን የለወጠው የፕሮቴስታንት ተሐድሶ"*** በሚለው አሳብ ሥር ስድስት ምዕራፎች አሉ:- **ምዕራፍ ሰባት:-** የፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ፋና ወጊዎችን ራእይ፣ በታላቅ ተጋድሎና በደም የታተመ የተሐድሶ ሰኬት ይዘረዝራል:: **ምዕራፍ ስምንት:-** የፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ መሠረቱ ምንድነው? ለሚለው ጥያቄ አምስት የፕሮቴስታንት ተሐድሶ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረትና ምሰሶዎችን ይተነትናል:: **ምዕራፍ ዘጠኝ:-** የፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ በዓለም አቀፍ ደረጃ ምን ለውጥና ውጤት አመጣ? ለሚለው ጥያቄ በጠንካራ ጥናት የተደገፈና በታሪክ የተረጋገጠ ሙሉ መልስ ይዟል:: ከዚያም በ**ምዕራፍ አሥር:-** የፕሮቴስታንት ተሐድሶ ክርስትና በደቡብ ኮሪያ፣ በምዕራቡ ዓለምና በቻይና ሁለንተናዊ ዕድገት የተጫወተውን ዐቢይ ሚና በምሳሌነት ይጠቅሳል:: በዚሁ ክፍል ከሁሉም ቀድመን የተቀበልነው ክርስትና በጕላ መልኩም ባይሆን በተቃራራብ ሁኔታ ለምን እንደ ሌሎች እንዳልጠቀመን ጥያቄ አንሥቶ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያንን ለተሐድሶ ይጣራል:: **ምዕራፍ አሥራ አንድ:-** ቤተ እምነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ባይሆንም እስከ ዛሬ እግዚአብሔር ለራሱ ክብር ተጠቅሞበታል፤ ከዚህ በኋላ የኢትዮጵያ ፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያናት በብዙ ማርጀታቸውን በማሳየት ለተሐድሶ ግልጽ አገራዊ ጥሪ ያቀርባል:: **ምዕራፍ አሥራ ሁለት:-** የቤተ ክርስቲያንን እርጅና፣ ሞትና ተሐድሶ በዝርዝር ያስቃኛል:: በማጠቃለያም የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ መሣሪያ ለመሆን ከእኛ ምን ይጠበቃል ለሚለው ጥያቄ አምስት ቁልፍ ነጥቦችን በማስቀመጥ መጽሐፉ ሐሳቡን ይቋጫል::

**መልካም ንባብ**
**ፀጋአብ በቀለ**
**2006 ዓ.ም**

# ክፍል አንድ

## የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ታሪክ

# ፩

# የቤተ ክርስቲያንና የተሐድሶ ምንነት

## የቤተ ክርስቲያን ምንነት

ቤተ ክርስቲያን 15 እና 50 ሰዎች በስምምነት የሚመሠርቷት የንግድ ማህበር አይደለችም:: ቤተ ክርስቲያን በፓስተርም ሆነ በሊቀ ጳጳስ ወይም በንጉሥ የምትሠራ ምድራዊ ድርጅት አይደለችም:: ቤተ ክርስቲያንን የሚመሠርታት ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሆን ቅዱሳን ከእርሱ ጋር ለመሥራት በጸጋው የታደሉ ልጆቹ ናቸው:: የቤተ ክርስቲያን ራስ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ሞት እና ትንሣኤ የተጠራች የቅዱሳን ጉባኤ እንጂ ግዑዝ ሕንፃ አይደለችም:: ቤተ ክርስቲያን የጸሎት ቦታ ሳትሆን የሚጸልዩ ቅዱሳን ናት:: ቤተ ክርስቲያን ቦታ ሳትሆን በቦታ ላይ የሚኖሩ የክርስቶስ ልጆች አንድነት ናት:: ቤተ ክርስቲያን የሚሰገድላት ግኡዝ ሕንፃ ሳትሆን በእውነትና በመንፈስ ለእግዚአብሔር የሚሰግዱ ቅዱሳን ሕብረት ናት:: ቤተ ክርስቲያን በድንጋይ፣ በሲሚንቶ፣ በእንጨት፣ በብረት ሳይሆን በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ፣ በቃሉና በጸጋው የተገነባች መለኮታዊ አካል ናት::

ዶክተር መልሳቸው መስፍን "ቤተ ክርስቲያን" በሚል መጽሐፋቸው፡- "ቤተ ክርስቲያን" የሚለው ቃል(ሐረግ) በአማርኛ የሚሰጠው ቀጥተኛ ፍቺ *"የክርስቲያን ቤት"* የሚል ሲሆን ቤተ መንግሥት፣ ቤተ ክህነት፣ ቤተ መዘክር እንደሚሉት ሐረጎች ሁሉ ትርጉም የሚያጎላው ቦታውንና ያም ቦታ ወይም ቤት ለምን አገልግሎት እንደሚውል ነው::[86] የእንግሊዘኛው ቃል "ቸርች" የሚለው ደግሞ *"ኩሪያክስ"* ከሚል የግሪክ ቃል የተገኘ ሲሆን ትርጉሙም የጌታ የሆነ ማለት ነው:: ሆኖም ቤተ ክርስቲያን ለሚለው መጠሪያ የግሪክ ስርወ-ቃሉ "ኤክለሽያ"[87] ሆኖ ከግሪኩ ቃል በመመሥረት የእንግሊዝኛ ቀጥተኛ ትርጉም *"ኤክሌሲያስቲካል"* ነው፤ ብለዋል:: ይህም ማለት ስብስብ ማኅበር ወይም ጉባኤ ማለት ነው:: ስለሆነም ቤተ ክርስቲያን ማለት መሠረታዊ ትርጉሙ የቅዱሳን ጉባኤ ወይም ማኅበር ማለት ነው::[88]

አባ መልከጼዴቅ ሊቀ ጳጳስ *"የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ትምህርት"* በሚለው መጽሐፋቸው ቤተ ክርስቲያን ቦታና ሕንፃ ሳትሆን የቅዱሳን አንድነት እንደሆነች ሲገልጹ፡- *...ሕንፃውን ግንቡን ቤተ ክርስቲያን እንላለን እንጂ ቤተ ክርስቲያን ማለት ክርስቶስ በደሙ የዋጃት የመሠረታት እንዲሁም እርሱ ራስ የሆነላት የምዕመናን አንድነት ማለት ነው:: ...ቤተ ክርስቲያን የተባልን እኛ ስንሆን የቤተ ክርስቲያንም ራስ ክርስቶስ ነውና*[89] በማለት መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት አስቀምጠዋል:: ሮጀር ካውሊ ቤተ ክርስቲያን *"ትርጉሙ እምብዛም ወደ ሰው እንጂ ወደ ሕንፃ አይደለም::"*[90] ሲሉ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን መባሉ በልማድና በዘይቤ እንጂ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት እንደሌለው አሳታውቀዋል::

በኒቅያ ጉባኤ (325 ዓ.ም)፣ (የሃይማኖት አንቀጽ) በቁስጥንጥንያ ጉባኤ (381 ዓ.ም) አንቀጽ ሃይማኖት ውስጥ ቤተ ክርስቲያንን በሚመለከት የተጻፈው አንቀጽ እንዲህ ይላል፡- *"በሁሉ ባለች በሐዋርያዊት ጉባኤ በአንዲት ቤተ ክርስቲያን እናምናለን"* የሚለው ፍሬ አሳብ አማኞችን እንጂ ሕንፃን አያመለክትም:: ዛሬ ቤተ ክርስቲያን የሚለው ስም በማገልገል ላይ የሚገኘው ለቅዱሳን አንድነት ወይንስ ለግዑዝ ሕንፃ? ከሁሉ በፊት አንዱ በቃሉ መታደስ መለወጥ ያለበት ይህ ዘመን ዘለቅ ስህተት ነው:: የቅዱሳን ሕብረት ቤተ ክርስቲያን ናቸው እንጂ ቤተ ክርስቲያን አይሄዱም::

---

[86] *መልሳቸው መስፍን (ዶ/ር)(1979 ዓ.ም)፤ቤተ ክርስቲያን፣ ሮኖቦት ማተሚያ ቤት፣* ገጽ 17

[87] ekklesia (ek-klay-see-ah) Strong Exhaustive Concordance of the Bile defines as follows:- ekklesia: a calling out. i.e a popular meeting, especially a religious congregation; assembly. ለምሳሌ:- በሐዋ 7:38 ይህ ሰው በሲና ተራራ ከተናገረው መልአክና ከአባቶቻችን ጋር በምድረ በዳ በማህበሩ ውስጥ የነበረ ነው በሚለው ማህበር ለሚለው ቃል የተሰጠው የግሪክ ekklesia ነው:: ይህ ቃል King James and Standard Versions Church ሲሉት New International Version Congergation ይሉዋል::

[88] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 18

[89] አባ መልከጼዴቅ (ሊቀ ጳጳስ)(1994 ዓ.ም.)፤*የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ትምህርት*፤ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ ገጽ 242-243

[90] ሮጀር ካውሊ.(*1963 ዓ.ም) ጸድቀ ሃይማኖት፣ የቤተ ክርስቲያን ሃይማኖት ውሳኔዎች*፣ብ.ሰ.ቀ.ኃ.ሥ.ማ. ቤት፣ ገጽ 66

# የተሐድሶ ምንነት

## የተሐድሶ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት

*መጽሐፍ ቅዱስ የተሐድሶ/ Reformation /*[91] *መጽሐፍ* ነው:: ብሉይ ኪዳን በእግዚአብሔር የተፈጠረው ፍጹም ሰው፣ ከመውደቁ የተነሣ፣ ፍጥረተ ዓለሙ በኃጢአትና በሰይጣን ግዞት ውስጥ ያሳለፋትን መራራ፣ ጨለማና ያረጀ የቀድሞ ሕይወት ይወክላል:: አዲስ ኪዳን ደግሞ በሰይጣን መታለል ወድቆ የኃጢአት ግዞተኛ የሆነውን የሰው ልጅና ፍጥረተ ዓለሙን ሊያድስ ትልቅ የሕይወት ዋጋ ስለከፈለው ስለ ኢየሱስ ይተርካል::

በኖኅ ዘመን የሰው ልጅ በኃጢአትና በክፋት ዓለምን በሞላ ጊዜ እግዚአብሔር *"ክፋት በምድር ላይ እንደ በዛ የልቡ አሳብና ምኞትም ሁልጊዜ ፈጽሞ ክፉ እንደሆነ አየ፤ ...እግዚአብሔርም:- የፈጠርሁትን ሰው ከምድር ላይ አጠፋለሁ:...አለ"* (ዘፍ.6:5-7):: በዚህ ክፍል እግዚአብሔር በኖኅ መርከብ ካሉት በቀር በኃጢአት የተበከለውን ፍጥረተ ዓለም በማጥፋት ተሐድሶን በምድር ላይ ሲያመጣ እንመለከታለን:: እግዚአብሔር የኪዳን የሆኑ የእስራኤል ነገሥታትና ሕዝቡ ቃሉን በመተላለፍ የኮረብታ መስገጃዎችን ሲተክሉና የማምለኪያ አፀዶችን ሲገነቡ አዳሾችን ያስነሣ ነበር:: ተሐድሶው የእግዚአብሔር ያልሆነውን በማፍረስ ይገለጥ ነበር:: ተሐድሶን ከመሩ ነገሥታት መካከል ሕዝቅያስ አንዱ ነበር:: *(2ነገ.10: 27፤ 11: 18፤ 23: 7)::* በስም የእግዚአብሔር በግብር ግን ጣዖት ሲያመልክ የተገኘው ሕዝብ እግዚአብሔር በተሐድሶ ቃል ባመጣ ጊዜ ባይመቸውም የኮረብታ መስገጃዎችን ሲያፈርስ፣ የሐሰተኛ አማልክቱን ሲጥል፣ የማምለኪያ አጸዶቹን ሁሉ ሲቈራርጥ እንደነበር መጽሐፍ ቅዱስ በብዙ ቦታ ይናገራል:: *(መሳ.6:28-30፤ 1ነገ.13:1-2፤ 22:43፤ 23:67)::* ይህ የእግዚአብሔር የሆነውን በማደስ የእግዚአብሔር ያልሆነውን ሁሉ በማፍረስ የተገለጠ ተሐድሶ ነበር::

ከተሐድሶ መሪዎች አንዱ የነበረው ሕዝቅያስ ለቤተ መቅደስ አገልጋዮች ባደረገው ንግግር:- *"ሌዋውያን ሆይ ስሙኝ ተቀደሱ፤ የአባቶቻችሁንም አምላክ የእግዚአብሔርን ቤት ቀድሱ፤ ርኩሱን ነገር ሁሉ ከመቅደስ አስወግዱ" (2ዜና 29:5)::* በዚህ ክፍል ተሐድሶ ከራስ መጀመር

---

[91] ተሐድሶ በሚባለው ቃል ፍቺ የእንግሊዝኛ ሐሳብ እንዳለ ይዞ ቀርቧል::*The Reformation sought to "reform" Christianity by returning it to original beliefs based solely on reference to the Bible, eliminating later additions which accumulated in tradition. Word origin - "improvement, alteration for the better," early 15c.,* በተጨማሪ የሚከተለውን ድረ ገጽ ይመልከቱ:: *http://atheism.about.com/library/glossary/western/bldef_reformation.htm*

እንዳለበት አመልክቷል። መጽሐፍ ቅዱስ የሌዋውያንን አስደናቂ እርምጃ እንዲህ ገልጾታል፦ *"ያነጹት ዘንድ ወደ እግዚአብሔር ቤት ወደ ውስጡ ገቡ፤ በእግዚአብሔርም መቅደስ ያገኙትን ርኩስ ነገር ሁሉ ወደ እግዚአብሔር ቤት አደባባይ አወጡት። ሌዋውያንም ወስደው ወደ ሜዳ ወደ ቄድሮን ወንዝ ጣሉት" (2ዜና.29:16)። በሙሴ ዘመን በእግዚአብሔር ትዕዛዝ ለአንድ ጊዜ* ከእባብ ንክሻ ሕዝቡን እንዲያድን ከነሐስ የተሠራ የእባብ ምልክት ተሰጣቸው። ከዚያም በኋላ ሕዝቡ ከእግዚአብሔር ዓይኑን በማንሣት ከነሐስ የተሠራ የእባብ ምልክት ያመልክ ነበር። ይህን የተጣመመና አገርን ሁሉ አስቶ የነበረውን፤ የተሐድሶ ሰው የነበረው ንጉሥ ሕዝቅያስ፦ *"የእስራኤልም ልጆች እስከዚህ ዘመን ድረስ ያጥኑለት ነበርና ሙሴ የሠራውን የናሱን እባብ ሰባበረ፤ስሙንም ነሑሽታን ብሎ ጠራው"(2ነገ. 18፡ 4) ይላል።*

ዛሬ ዘመን ዘለቅ፣ ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተሸገሩ የመጡ እንደ ነሐሱ የእባብ ምልክት መወገድ ያላበቸው የብዙሃኑን እይታና ልቡና የያዙ አስተምህሮዎችና ልምምዶች በቤተ ክርስቲያን የሉም ወይ? ካሉ በቃሉና በመንፈሱ ላይ ቆመን እንደ ሕዝቅያስ ማስወገድ ይገባናል። እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ለሕዝቡ የተሐድሶ ዓላማ እንደነበረው በነብዩ ኢሳይያስ በኩል ሲናገር፦ "*እግዚአብሔርን በመተማመን የሚጠባበቁ ግን ኃይላቸውን <u>ያድሳሉ</u>*" (ኢሳ.40:31) ይላል።

ወንጌል የተሐድሶ መልዕክት ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ዓላማውን ስቶ በኃጢአት ውስጥ ለወደቀው ሰው፣ እንደገና ወደ ተፈጠረበት መለኮታዊ ዓላማ አድሶ በክብር ለመመለስ፣ የሰው ሥጋ ለብሶ ተወልዶ፣ በፍጡር እጅ ሞቶ፣ ሞትን ድል አድርጎ የተነሣ የተሐድሶ ፋና ወጊ ነው። *"በዙፋኑ የተቀመጠው ሁሉን አዲስ አደርጋለሁ አለ"* (ራእ. 21፡ 5)። ከዚህም የተነሣ መጽሐፍ ቅዱስ በእርሱ አሮጌ ነገር ሁሉ አልፎ ሁሉም አዲስ እንደሆነ መስክሯል፦ *"ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፣ እነሆ ሁሉም አዲስ ሆኖአል" (2ቆሮ.5:17)።* ሐዋርያት በነፍሳቸው ተወራርደው በመውጣት፣ እየሰበኩ የሞቱት ይህን የተሐድሶ ዜና ነው።

ተሐድሶ ባያስፈልግ ኖሮ በሮሜ ላሉት ቅዱሳን ታላቁ ሐዋርያ ሲጽፍ *"በልባችሁ <u>መታደስ</u> ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ" (ሮሜ.12:2)* የሚለውን ቁልፍ ትዕዛዝ ባልሰጣቸው፤ እንዲሁም ሐዋርያው ጴጥሮስ ቀናዒ ለነበሩ አይሁዶች *"እንግዲህ ንስሐ ግቡ፣ ከመንገዳችሁም ተመለሱ ከጌታም ዘንድ <u>የመታደስ</u> ዘመን ይመጣላችኋል"* (ሐዋ.3:19)። *(አዲሱ መደበኛ ትርጉም)* ብለው አይናገሩም ነበር። ዛሬም በኪዳናቸው ላይ ቆመው የሕይወትን መታደስ የሚጠባበቁትን ጌታ ያድሳቸዋል።

- ተሐድሶ የሕያውነት ምልክት ነው፣
- ተሐድሶ የልጅነት ኪዳን ነው፣
- ተሐድሶ በሰው ድካም የእግዚአብሔር ኃይል የሚገለጥበት መንገድ ነው፣
- ተሐድሶ የዶግማ (የእግዚአብሔር ቃል) መለወጥ ሳይሆን ሰዋዊና እንደ ቃሉ ያልሆኑ አደናቃፊ ቀኖና (ሰዋዊ ሥርዓት) መለወጥ ነው:: ተሐድሶ ሰው ያለመቻሉን ለፈጣሪው በማሳወቅ ትዕቢቱን የሚሽርበት መንገድ ነው፣
- ተሐድሶ አሮጌ ነገራችን በአዲስ የሚተካበት ድንቅ ሂደት ነው፣
- ተሐድሶ የመክበር እንጂ የመዋረድ ምልክት አይደለም፣
- ተሐድሶ የእግዚአብሔርን ትክክለኝነት የሰውን ስህተተኝነት የሚያመለክት ሚዛን ነው::
- በዓለማችን ላይ ተሐድሶ የማያስፈልጋት የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን የለችም::
- ተሐድሶ የብሉይና የአዲስ ኪዳን ቁልፍ ትምህርት ነው:: እንደገና ካልተሠራን እንደገና መሥራት አንችልም::

እውነተኛ ተሐድሶ ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዳይመጣ የምንከላከለው አደጋ ሳይሆን እግዚአብሔር ሊያነቃን ሲፈልግ የሚያመጣልን ታላቅ ጸጋ ነው:: ተሐድሶ ለሕያው እንጂ ለሙት "ቤተ ክርስቲያን" አያስፈልግም:: የሞተ ነገር የሕይወትን ዑደት ጨርሶ ወደሌላ ስለተለወጠ ትንሣኤ እንጂ ተሐድሶን አይፈልግም:: ከዛሬ 41 ዓመት በፊት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ፓትርያርክ ሆነው ሲሾሙ ተሐድሶ እንደሚያመጡ በብዙዎች እንደሚጠበቁ የዛሬዪቷ ኢትዮጵያ የተሰኘው አንጋፋው ጋዜጣ እንዲህ ብሎ ነበር:-

> *የሌሎች አገሮች አብያተ ክርስቲያናት እንደ ታደሱ ሁሉ የእኛም እንደ ዘመኑ መራመድ ይኖርባታል:: የአሥራ አምስተኛው ክፍለ ዘመን ሰዎች አስተሳሰብና የሃያኛው ክፍለ ዘመን ፍልስፍና በጣም የተራራቀና የተለየ ስለሆነ ሊያሳምን በሚችለው በአዲስ ዘዴ መቅረቡ የተሻለ ውጤት ያስገኛል:: ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ ይህን ሁሉ በማመዛዘን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በመንፈስ፣ በአሠራር፣ በአስተሳሰብና በአፈጻጸም የታደሰችና የዘመኑን ሥርዓት የተከተለች እንደሚያደርጓት ከፍተኛ ኃላፊነት ይጠብቃቸዋል::*[92] በማለት ለተሐድሶ ያላቸውን ረሃብ ገልጸው ነበር::

[92] *የዛሬይቷ ኢትዮጵያ፣ ሚያዝያ 2፣ 1963 ዓ.ም*

ተሐድሶ ራሳችንን፣ አገልግሎታችንንና ቤተ ክርስቲያንን በእግዚአብሔር ቃልና መንፈስ የምንመዝንበት ዕድል እንጂ እርስ በርስ የምንካሰስበት ችሎት አይደለም። በአገራችን ሰዎች በተሐድሶ ስም የሚካሰሱበትና የሚወገዙበት አንዱ ምክንያት የተሐድሶን አጀንዳ የሰዎች አጀንዳ አድርገው ስለቆጠሩ ነው። የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ ስንመለከት የተሐድሶን አጀንዳ እግዚአብሔር በልጆቹ በኩል ለቤቱ ያቀብላል እንጂ ልጆቹ የተሐድሶን አጀንዳ አያመነጩም። ቅዱሳን የተሐድሶ መንገዶች እንጂ ምክንያቶች አይደሉም። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ተሐድሶን ስንቃወም የእግዚአብሔርን እንጂ የሰውን ሐሳብ አልተቃወምንም። ተሐድሶ ስለ ትክክለኝነታችን የምንመጻደቅበት መድረክ ሳይሆን በእግዚአብሔር ቃልና በመንፈሱ ውስጣችን የሚፈተሽበት መንገድ ነው። ትሁታን እንጂ ስለ ትክክለኝነታቸው የሚመጻደቁና የሚሰብኩ በፍጹም አይታደሱም።

ተሐድሶ አዲስ ሀሳብ ማፍለቅ ሳይሆን የቀደመውንና የቆየውን መለኮታዊ ሐሳብ ከኋላ መጥቶ የጋረደና የተካ የሰውን አዲስ ሃሳብ አስወግዶ ወደ ቀደመው የእግዚአብሔር ሃሳብ ለመመለስ አዲስ እርምጃ መውሰድ ነው። ፕሮፌሰር ሮበርት ሲናገር:- *የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ መሪዎች የሰበኩት በራሳቸው የፈጠሩት "አዲስ" ወንጌል ሳይሆን በብሉይና በአዲስ ኪዳናት ያገኙትና የተቀበሉት "አሮጌ" ወንጌል ነው*[93] ብሏል። ተሐድሶ አዲስ ወንጌል ሳይሆን የቀደመውንና የጥንቱን የክርስቶስ ወንጌል የጋረዱና የተቀላቀሉ የሰዎችን ትምህርትና ቀኖና በቃሉ አበጥሮ ሐዋርያት ወደ ሰበኩት የጠራና የጠለለ የወንጌል እውነት መመለስ ነው።

## ተሐድሶ የሚለውን ቃል በትክክል እንረዳ

ተሐድሶ የሚባለው ቃል፣ በተለይ በቤተ ክርስቲያን አካባቢ እጅግ የተለመደና የታወቀ ቃል ነው። ተሐድሶ የሚባለው ቃል ከቤተ ክርስቲያን ጋር ተያይዞ ሲነሣ፣ ምን ጊዜም አፍራሽ ሳይሆን፣ ለተሻለውና ለሚበልጠው ነገር ነው።[94] *"ተሐድሶ"* የሚል ቃል ጽንሰ ሐሳብ ትርጉሙ ምድንነው? ለሚለው ጥያቄ የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖረን፣ ሰፋ አድርገን ብንመለከት መልካም ነው። ተሐድሶ የሚለው ቃል የግእዝ ቃል ሲሆን፣ የአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ መዝገበ ቃላት ተሐድሶን በገቢር ግስ (ሐደሰ) ሲፈታው:- *ማደስ፣ መለወጥ፣ ሐዲስ ማድረግ፣ ማጥናት፣ ማበረታታት፣ መሥራት፣ መጠገን፣* በተጨማሪም "አዲስ ነገር ማውጣት፣ መፍጠር ነው።" ይላል (ገጽ 435)

---

[93] Robert Mcafee Berwon, (1961)', *The Spirit of Protestantism*, New York Oxford University Press p16

[94] *ተሐድሶ የተሰኘው መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ግን ምንጊዜም አፍራሽ ሳይሆን ገንቢ፣ አጥፊ ሳይሆን አልሚ ተግባር የሚገለጽበት በመሆኑ፣ ከመንፈሳዊው ዓለም ባሻገር በሥጋዊው ዓለምም በጥቅም ላይ ውሏል። በአገራችን እንኳ ቃሉ በደርግ፣ በኢሕአዴግም መንግሥታት፣ አሮጌንና የተበላሸን ነገር ከማሻሻል፣ ከማስተካከልና ከማስወገድ ጋር በተያያዘ ጥቅም ላይ እንደ ዋለ ይታወቃል። ከመቼውም ጊዜ ይልቅ አገራችን በሁሉም መስክ የተሐድሶ (ሕዳሴን) ድምፅ እያስተጋባች ትገኛለች። መምህር በቃሉ ታመነ (2004 ዓ.ም)፣ ማህበረ ቅዱሳን የቤተ ክህነት ዕዳ፣ ገጽ 33*

*ትርጉሙም የተበላሸውንና የተመሰቃቀለውን ነገር በትክክለኛ ቦታ ሥርዓት አስይዞ ማስቀመጥን፣ ወደ ቀድሞ ይዞቱ መመለስን፣ የቀድሞውን ፈር የለቀቀውን፣ አዲስ ሥርዓት ማስያዝን ያመለክታል::*[98]

2. ***Re-newal:-*** *ማደስ፣ የቀድሞ መልክና ውበትን መመለስ፤ የዚህ ቃል መሠረት አናካይኖ (Anakaino) የሚል የግሪክ ቃል ሲሆን፣ ትርጉሙም አዲስ ማድረግ ማለት ነው:: ያረጀውን ነገር ወደ ቀድሞ ሁኔታ መመለስ፣ የደከመውን የሰውነት ክፍላችንን እንደገና ኃይል ማግኘትን ያመለክታል:: በዚህ አውድ መሠረት የቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ሕይወት ተሐድሶ እንደሚያስፈልገው እንገነዘባለን::*[99]

3. ***Re-storation:-*** *ወደ ቀድሞ ሥፍራ ወይም ባለቤት መመለስ:: ይህ ቃል አካታስታቶስ (Akatastatos) ከሚለው የግሪክ ቃል የመጣ ሲሆን፣ ስፍራውን የለቀቀውን፣ የተሰረቀውን፣ የተወሰደውን ወደ ሥፍራው መመለስን ያመለክታል:: ዶክተር ኢ.ያሱ ተሐድሶ የሚለውን ሲያብራሉ፣ ተሐድሶ ማለት የተበላሸውንና የተመሰቃቀለውን ማስተካከል፣ ማሻሻል፣ መለወጥ፣ ያረጀውንና የፈረሰውን እንደገና በማደስ፣ እንደነበረው ማድረግ፣ የጠፋውንና ሥፍራ የለቀቀውን ወደ ቀድሞ ሥፍራው መመለስ ነው::*[100] በማለት አብራርተዋል::

በ16ኛው ክፍለ ዘመን፣ እግዚአብሔር የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ መንገድ አድርጎ የተጠቀመበት ማርቲን ሉተር በሰው ሥርዓትና ወግ ወንጌልን የለወጠችና ከመንግሥት ጋር ጋብቻ ፈጽማ የስማይ ሙሽራ በሆነችው ቤተ ክርስቲያን ላይ የተጫነባትን ሸክም በቃሉና በመንፈሱ አራግፎ ወደ ቀድሞ ከመመለስ ያለፈ ለቃሉ ባዕድና አዲስ የሆነ ነገር ያደረገው አንዳችም አልነበረም:: የሉተር ድርጊት ከቃሉ ለወጣች ቤተ ክርስቲያን እንጂ ለቃሉ ባዕድና አዲስ አልነበረም:: ዛሬም በቤተ ክርስቲያን ከቃሉ ጋር የሚቃረኑና የሚጣረሱ ዘመን ዘለቅ ልምምዶችንና አስተምህሮዎችን እንደ እግዚአብሔር ቃል የሚቆጥሩ ሰዎች ለተሐድሶ አዎንታዊ አመለካከት የላቸውም:: የሮም ቤተ ክርስቲያን፣ ማርቲን ሉተርን የእግዚአብሔርን ቃል ይዞ ሲነሣ እስከ ሞት እንዳሳደደችው፣ ዛሬም የተሐድሶን ዓላማ አንግበው የሚነሡትን በብርቱ የሚያሳድዱና ለቤተ ክርስቲያን እንደቀነ የሚናገሩ ሰዎች እጅግ ብዙ ናቸው:: ስለዚህም የተሐድሶ መንገድ አልጋ በአልጋ ሳይሆን፣ ብርቱ ትግል፣ ተቃውሞ፣ ስም የማጥፋት ዘመቻ፣ የማጠልሸት አካሄዶች የተሞላ እንደሆነ ታሪክ ያስተምረናል::

ሰይጣን በቃሉና በመንፈሱ ታድሳ የክርስቶስን ውበት በገሃድ የምታሳይ ቤተ ክርስቲያን በዓለም በፍጹም እንድትገለጥ አይፈልግም:: እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንን ለማደስ በእርሱ በሚያምኑ ልጆቹ ሲጠቀም ሰይጣንም ቤተ ክርስቲያን እንዳትታደስ የእርሱን አጀንዳ በሚያስፈጽሙ

[98] *ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 1*
[99] *ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 3*
[100] *ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 4*

ከጠረቀው 95 ነጥቦች መካከል አንዱ:- *"ለክርስቶስ ሕዝብ ሰላም ሳይሆን 'ሰላም ሰላም' (ኤር.6:14) የሚሉ ነቢያት ሁሉ ይወገዱ"*[102] ብሎ እንደተነሣው መነቀል ያለበትን ከቤቱ የሚነቅሉና መተከል ያለበትን የሚተክሉ የተሐድሶ ነቢያት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በኃይል ይገለጣሉ:: ከእንግዲህ በወንጌል ስም የሚነግዱ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቦታ የላቸውም:: ከላይ በተለያዩ ምሁራንና የእግዚአብሔር ቤት አገልጋዮች የተጠቀሱት የተሐድሶ ትርጉሞች እንዳሉ ሆነው፤ የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ የተሐድሶን ትርጉም እንዲህ ያስቀምጣል:- **የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ አዲስ ሃይማኖት ሳይሆን፣ ሁሌ አዲስ በሆነው የእግዚአብሔር ቃል መነጽር በማየት በቤተ ክርስቲያን ሕይወትና አገልግሎት ውስጥ ሰርጎ የገባውን ሥጋዊ፣ አጋንንታዊና ዓለማዊ አሠራሮችን፣ ትውፊቶችን፣ አስተምህሮዎችንና ልምምዶችን በቃሉ ነቅሶ በማስወገድ፣ ቤተ ክርስቲያንን ወደ ቀድሞ ክብሯ ለመመለስ እግዚአብሔር በልጆቹ የሚሠራው ታላቅ ሥራ ነው::**

የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ መሣሪያ የእግዚአብሔር ቃል ነው:: ቃሉ ዒላማ አድርጎ የሚነሣው የቀደመውንና ነባር የሆነውን የቃሉ እውነት ከኋላ መጥቶ ለመሸፈን ወይም ለመናድ በሚታገሉት ልምምድ፣ ትውፊት፣ ሥርዓት፣ ድርሳናትና አስተምህሮ ላይ ነው:: የእግዚአብሔር ቃል በቤተ ክርስቲያን የሚካሄደውን እያንዳንዱን ጉዳይ ይዳኛል፣ ይፈትሻል፣ ይሞርዳል፣ ይቀርጻል፣ እውነትን ያፀድቃል፣ ውሸትን ይጥላል፣ መፍረስ ያለበትን ያፈርሳል፣ ያረጀውን ያድሳል፣ መተከል ያለበትን ይተክላል፣ እንዲሁም መነቀል ያለበትን ይነቅላል::

የትኛውም የቤተ ክርስቲያን ትውፊት፣ ድርሳናት፣ ገድላት፣ ልምምዶች፣ አስተምህሮዎችና ቀኖና በመጽሐፍ ቅዱስ ይፈተሻሉ እንጂ ሁላቸውም አንድ ላይ ተጨፍልቀው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሰውን አንድ ቃል መፈተሽ አይችሉም:: *"በመጀመሪያ ቃል ነበረ"* (ዮሐ.1:1) የሚለው እውነት፣ የእግዚአብሔር ቃል የሁሉ ቀዳሚ፣ የሁሉ መገኛ፣ የሁሉ ምንጭ፣ የሁሉ ፈጣሪ፣ የሁሉ መሠረትና ሚዛን መሆኑን ያሳያል:: ቃሉም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው::

## የመነቃቃት ምንነት

መነቃቃት ተሐድሶ አይደለም፤ ተሐድሶም መነቃቃት አይደለም:: በተለምዶ ብዙውን ጊዜ እነዚህ ሁለት የተለያዩ ጽንሰ አሳቦች እንደ አንድ አሳብ ሲቀርቡ ይታያሉ:: ሁለቱ አሳቦች ተደጋጋፊና ለቤተ ክርስቲያን እጅግ በጣም አስፈላጊ ሲሆኑ ልዩነታቸውን ማወቅ ግን የግድ ይላል:: መነቃቃት

[102] Harold G. Grimm(ed) (1957), *The Ninety-Five Theses ot the Disputation Concering the value of Indulgences: Luther's Works*, Fortress Press Vol.31 USA

የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ ዞር ብለን ስንመለት የቤተ ክርስቲያን ዕድገትና የወንጌል ስርጭት በዓለም ላይ እኛ መነቃቃት ብለን በምናስበው መንገድ ብቻ አልተካሄደም፤ አይካሄድምም። ለምሳሌ፡- በዓለማችን በወንጌል ታላቅ ተጽዕኖ በማምጣት ተጠቃሾች የሆኑ እንደ ማርቲን ሉተር፣ ጆን ዊክሊፍ፣ ጆን ሑስ፣ ዊሊያም ኬር፣ ዴቭድ ሊቨንግስተን፣ ወደ አፍሪካና ወደ ኢትዮጵያ ወንጌልን ይዘው የመጡ ታላላቅ የወንጌል ሚሲዮናውያን ዛሬ እኛ ያለ መንፈሳዊ መነቃቃት (ልዩ ትንቢት፣ መገለጥ፣ ድንቅና ተምራት፣ መሳት፣ በልሳን መናገር ወዘተ...) ምንም መሆን አንችልም፤ ብለን በምናስበው መንገድ የተገለጡ አልነበሩም።

እንዲሁም በአገራችንም ቀደሚት የወንጌል አርበኞች መካከል አባ እስጢፋኖስ፣ አለቃ ታዬ፣ በ1880ዎቹ ዓ.ም ከኤርትራ ወደ ወለጋ በመዝለቅ በቦጂ የመጀመሪያ የመካነ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን መሠረት ከጣሉት አንዱ የሆኑ ቄስ ገብረስታትዎስ፣ በዚያው ወቅት ወንጌልን አንግበው ከምጽዋ ጅማ ለመድረስ ሰባት ዓመት የፈጀባቸው የአባጂፋር ጸሐፊ በመሆን ወንጌልን በትልቅ ጫናና ተጽዕኖ ሥር ሆነው የሰበኩ ንጉሤ ታሹ፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ተነሥተው ትልቅ የወንጌልን ሥራ ሲሠሩ እየታሰሩ፣ እየተደበደቡ፣ እየተወገዙ በብዙ መቶ ሺዎች የሚገመቱ ነፍሳትን የማረኩና የዛሬ የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያንን መሠረት ከጣሉት አበው መካከል ዳና መጃ መዳሮ፣ አቶ ሹጉጤ ዳዳ፣ አባ ጎሌ ነነሞ ተጠቃሾች ሲሆኑ እነዚህ ሁሉ ሕይወታቸውን የለወጠውን የወንጌል ቃል በመታዘዝ በወሰዱት የእምነት እርምጃ አሁን ላለንበት ታላቅ መንፈሳዊ መነቃቃት ምክንያት ሆነዋል። እኛ ዛሬ የምናጣጥመው መነቃቃት ዓይነት ለእነርሱ ባዕድ ነበር። ቢሆንም አንፀባራቂና ታላላቅ ሥራዎችን ለቃሉና ለመንፈሱ በመታዘዝ ሠርተዋል። የፈጠሩት የጽድቅ ተጽዕኖ ከጫካ እስከ ቤተ ክህነትና ቤተ መንግሥት በኃይል ተሰምቶ ነበር። ለእኛም የበረከት መንገድ ሆነዋል። ከእነርሱ ጋር የነበረውና ከእኛ ጋር ዛሬ ያለው ጌታ ያው ቢሆንም አሠራሩ ልዩ ልዩ ነው። በብዙ መነቃቃት የታጀበው፣ የድምፁን ያህል ተጽዕኖ ፈጣሪ መሆን ያቃተው፣ ለራሱ ድሎት እንጂ ስለሌላው ደንታ ቢስነት ጎልቶ የሚታይበት፣ ቃል ሳይሆን ገበያ ተኮር የአገልግሎት ዘይቤ ግራ ያጋባው የዘመናችን ክርስትና የመንፈሳዊ ጉልበትና የሕይወት ጥንካሬ በዚህ ምድር እንደ ተነሡ ቀደምት አበው እንዳልሆነ ብዙዎች ይስማማሉ።

በእግዚአብሔር ህልዎት ውስጥ የሚኖር፣ የእግዚአብሔር የቃሉ እውነትና የመንፈሱ እሳት በልቡ ላይ የሚቀጣጠል አማኝ የመነቃቃት ምክንያት ለመሆን ይገለጣል እንጂ መነቃቃትን አይጠብቅም። ትናንት ውሃን በማናወጥ ይፈውስ የነበረው ጌታ ዛሬ ቃል ብቻ በመላክ የውሃውን መናወጥ ለዘመናት ይጠብቁ የነበሩ ብዙዎችን እየፈወሰ ነው። ዛሬ በዓለማችን ታላቅ መነቃቃት እየተካሄደባቸው ካሉት አገሮች አንዷ ኢትዮጵያ እንደሆነች ብዙዎች ይስማማሉ። ከዚህም የተነሣ ታላላቅ የአምልኮ አዳራሾች ጠበውን የመንግሥት ትልልቅ የስብሰባ ማዕከላት፣ አደባባዮችና ስታዲየሞች በመነቃቂያ ኮንፍራንሶችና በመዝሙር ፌስቲቫል ተሳታፊዎች ተጨናንቀዋል። የድሮ ጸሎት ቤት ሕንፃዎች ስለጠበቡን በዓይነቱ ልዩና

ታላላቅ ዘመናዊ ሕንፃዎች በውድ ዋጋ በአገራችን በከተማና ገጠር በመገንባት ላይ ተጠምደናል። እንደሚገባው ወንጌልን ማሮጥ ቢያቅተንም ሕንፃዎችን በመገንባት ትልቅ ወድድር ላይ ያለን እንመስላለን። ሕንፃን መገንባት ምንም ስህተት ባይኖረውም የዳነትን ደቀመዝሙር ከማድረግና ወንጌልን ይዘን የምንወጣበት አቅማችንን ከገታ አደገኛ ነው።

በእግዚአብሔር ቃል እንደሚገባ ያልተሠሩ ሰዎች *"ለእግዚአብሔር ቤት"* በመሥራት ሥራ ላይ የተጠመዱ ይመስላሉ። አሳዛኙ ነገር ጌታ በሞት በትንሣኤው የተሠራው የቅዱሳን አንድነት ፈርሶ በእኛ እጅ የተሠራውን ቤት የማይቀበል መሆኑ ነው። መቅደም ለሚገባው ቅድሚያ እንስጥ። አሁን በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት የሚያስፈልገው ሌላ መነቃቃትን ቁጭ ብሎ መጠበቅ ሳይሆን ባለፉት ሃያ ዓመታት መነቃቃት ወደ ቤተ ክርስቲያን መጥተው በአባልነት ላይ ብቻ የተገቱ አባላትን ደቀ መዝሙር የማድረግ ተሐድሶ ነው። በገጠርና በከተማ በቤተ ክርስቲያን ያለው አብዛኛው ሕዝብ ለዛሬ ምኞቱ ፈጣንና አቋራጭ መፍትሔ ሰጪ መሳይ "መገለጥ"ና "ትንቢት" ካልሆነ በስተቀር የእግዚአብሔርን ቃል እንደሚገባው መማርና ማስተማር *"የመንፈሳዊ ኋላ ቀሮች"* የዱሮ ሥራ መስሏል። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በተለይ ወንጌላውያኑ በአፋጣኝ በቃሉ ወደ እውነተኛና ሥር ነቀል ተሐድሶ ካልተመለሱ ሕልውናቸው በአደጋ ላይ ነው። አሁን የሚያስፈልገንን ተሐድሶ የሚያመጣ ቃሉ እንጂ ከቃሉ አፈንጋጮች የሚያደርገን "መነቃቃት" አይደለም። ያረጁና ያፈጁ አሠራሮችን ለማስወገድ ተሐድሶ ብቸኛ መልስ ነው። በቃሉ የታነፀ ለትውልዱ ደራሽና ተደራሽ አሠራሮችን ለመቀመር በመንፈሳዊ ዕውቀት የተገሩ፣ ባሕሪያቸውና ስጦታቸው ያልተፋታ፣ ደባል ስብዕና የማይታይባቸው፣ በቃሉና በመንፈሱ ታደሰው ተሐድሶን የመምራት እምነትና ድፍረት ያላቸው መሪዎች መቅደም አለባቸው። *"በጥሪ ሳይሆን በጥረት"* የአገልግሎት ቢሮዎችን የመውረር አካሄዶችን በተጠሩ፣ በታጠቁ፣ በተቀቡና በተማሩ ሰዎች የመተካት ተሐድሶ ይጠይቃል። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የራሳቸውን ኪስ ለማደለብ፣ በጸጋ ስጦታ ስም ሆዳቸውን ለመሙላትና ዝናቸውን ለማስራጨት የሚራኮቱትን ወደ ቃሉ መንገድ የመመለስ ተሐድሶ ያስፈልጋታል። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከብዙዎች ቀድማ የተቀበለችውን የወንጌል መልዕክት ለአፍሪካና ለዓለም ለማቀበል መንፈሳዊ አቅም አላት።

ሁለንተናዊ ተጽዕኖ የምታመጣ ቤተ ክርስቲያን ሆና ለመገለጥ የአመለካከት፣ የአቋምና የተግባራዊነት ተሐድሶ ይጠይቃል። እውነተኛ ተሐድሶ ወደ እውነተኛ መነቃቃት ይመራናል። የነገረ መለኮት ምሁራን መነቃቃት በፈለግነው ጊዜ የምናመጣው ጉዳይ ሳይሆን የእግዚአብሔር ሉዓላዊ ሥራ ውጤት እንደሆነ ይስማማሉ። የወንጌል አደራ እግዚአብሔር በፈለገው ጊዜ በሉአላዊ አሠራር በሚያደርገው መነቃቃት ብቻ ላይ የተመሠረተ ሳይሆን በተሰጠን የልጅነት ሥልጣን፣ በጸጋው፣ በኃይሉ፣





በቃሉና በመንፈሱ ጉልበት ሁሌም እንድንፈጽመው የተሰጠን አንገብጋቢና ጊዜ የማይሰጥ ተልዕኮ እንደሆነ መዘንጋት የለበትም። ከእኛ የሚጠበቀው መታዘዝ ነው። ክርስቶስ ባለበት ሕይወት ውስጥ ሁሌም መነቃቃት አለ። በተገለጠላቸው የቃሉ እውነት ላይ ቆመው ተሐድሶን ለማምጣት በራሳቸው ጨክነው የሚወጡ ቅዱሳን ለዘመናት እየጠበቅነው ወዳለነው ታላቅ መነቃቃት ያስገቡናል ብዬ አምናለሁ።

## የመነቃቃትና የተሐድሶ ልዩነት በንፅፅር

ቦቢ ግልያም እንዲህ አስቀምጠዋል፡-

*ቤተ ክርስቲያን አካል እንደሆነች አስቡ፤ በዚህም መሠረት መነቃቃት ለልብና ለአዕምሮ ሕይወትና መታደስን እንደሚያመጣ ነው። ተሐድሶ ደግሞ የአካል አጥንቶችን የሚገጣጥም ነው። መነቃቃት የእምነትን፣ እሴቶችንና ውሳኔዎችን ለውጥ ያስገኛል። ተሐድሶ ደግሞ የባሕሪ፣ የአወቃቀርና የትጥቅ ለውጥ ያመጣል። መነቃቃት ንጹህ ውኃ ወደ ውኃ ጉድጓድ መጨመር ነው። ተሐድሶ ደግሞ በውኃው ጉድጓድ ላይ ያሉትን ቀዳዳዎች መድፈን ነው። ይሁን እንጂ በመነቃቃትና በተሐድሶ መካከል ያሉትን ሁለት ዋነኛ ልዩነቶች ማብራራት ሰፊ ጊዜ ይወስዳል። በመነቃቃትና በተሐድሶ መካከል ያለው የመጀመሪያ ልዩነት መነቃቃት በግለሰብ ደረጃ ሊጀምር የሚችል ሲሆን ውጤታማ ተሐድሶ ግን ከላይኛው የሥልጣን መዋቅር፣ ከቤተ ክርስቲያን አመራር ወይም ከአንድ ቤተ እምነት ይጀምራል።*[106]

| መነቃቃት | ተሐድሶ |
|---|---|
| በልብ፣በአዕምሮና ሕይወት ላይ ያተኩራል | በሰውነት አጥንት ላይ ያተኩራል |
| በእምነት እሴቶች ላይ መወሰን | ባሕርይንና መዋቅርን ይመለከታል። |
| በውኃ ጉድጓድ ንፁህ ውኃ መጨመር | በውኃ ጉድጓድ ውስጥ ያሉ ቀዳዳዎችን መድፈን |
| በግለሰብ ደረጃ ይጀምራል | ከሥልጣን መዋቅር አናት ላይ ቢጀምር ውጤታማ ይሆናል |

*ምንጭ፡- ቲኔት ኢንተርናሽናል ኮርስ 1 መጽሐፍ*[107]

[106] ዝኒ ከማሁ ገጽ 64
[107] ዝኒ ከማሁ ገጽ 64

# ተሐድሶ ወይም ሞት!

ተሐድሶ ወይም ሞት! አንዲት ቤተ ክርስቲያን የቃሉንና የመንፈሱን ተሐድሶ እንቢ ካለች ሞትን መርጣለች:: የሞተች ቤተ ክርስቲያን ደግሞ የሕያው አምላክ ወኪል መሆን አትችልም ማለት ነው:: እርሱ በኃይሉ እንደገና በቃሉና በመንፈሱ ትንሣኤን ካልሰጣት በስተቀር:: በቃሉና በመንፈሱ የማትታደስ ቤተ ክርስቲያን ሕያው ብትመስልም ሙት ናት:: የቤተ ክርስቲያን አዳኝ የቤቱ ራስ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሆን፣ ቅዱሳን ከእርሱ ጋር አብረው ይሠራሉ:: ያለመታደስም ሆነ ተሐድሶ ለቤተ ክርስቲያን ባዕድ አይደለም:: ሁለቱም በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ይታወቃሉ::

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ልሳን የሆነው ዜና ቤተ ክርስቲያን ጋዜጣ፣ ከ1960ዎቹ መጨረሻ አንሥቶ እስከ መስከረም 1982 ዓ.ም ድረስ ግለሰቦች አስተያየታቸውን የሚያንጸባርቁበት *"የተሐድሶ ዐምድ ለውይይት"* እና *"የተሐድሶ ዐምድ ለውይይትና ለትምህርት"* በሚሉ ተለዋዋጭ ስያሜዎች የሚጠራ የተሐድሶ ዐምድ ነበረው::[108]

# ተሐድሶ ጠሪ የኢትዮጵያ የቤተ ክርስቲያን ነባራዊ ሁኔታ

በዚህ መጽሐፍ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሚለው ስያሜ በኢትዮጵያ ያሉ አብያተ ክርስቲያናትን ሁሉ ያጠቃልላል:: ከዚህ በታች በአገራችን በብዛት የሚገኙ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንና የኢትዮጵያ ፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት ያሉበትን ተሐድሶ ጠሪ ገጽታዎችን ከመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ጋር እያስተያየን ዛሬ ያሉበትን ሁኔታ እንመለከታለን::

> *"መጽሐፍ ቅዱሳችንን ከፍተን ባነበብን*
> *ቁጥር፣ ተሐድሶ በልባችን ይካሄዳል::" ጆርጅ ጆን*

ክርስትና ለአውሮፓ የመንፈሳዊ ሕይወት ለውጥ ምክንያት ከመሆን ባሻገር ለኢንዱስትሪው አብዮት፣ ለሥራ ፈጣሪዎች የአዕምሮ ልማትና *"የዲሞክራሲ መመንደግ"*[109] ዐቢይ ምክንያት እንደሆነ በተጨባጫ ጥናት ከተረጋገጠ ምዕተ ዓመታት ተቆጥረዋል:: ኮች የተባለው ምሁር ስለዚህ

[108] ዝኒ ከማሁ 64

[109] ዊሊያም ተምፕል የተባለ የእንግሊዝ ብሔር ሰው በእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን ለዲሞክራሲ ማበብ መሠረት እንደነበረች ሲናገሩ:- *"church meetings of the dissenting groups were a fruitfull training ground for democratic procedures"* Temple, Christianity and Social Order, S.C.M. Press, p 67 *በአሜሪካም የዲሞክራሲ ማበብ ቤተ ክርስቲያን መሠረት ነበረች:- "town church meetings and thus a chif source of democratic pratice in America"* Pauck, The Heritage of the Reformation, p 213





ሲናገር:- *"ክርስትና የምዕራባውያን ሥልጣኔ አቅጣጫ አመልካች የሆኑ የፍልስፍና፣ የሳይንስና የጥበብ መሠረት ነው"*[110] በማለት እማኝነቱን ሰጥቷል:: 6ኛው የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ጆን ኩዊንስ አዳምስ /1825 – 1829/ የአሜሪካ መንግሥት መሠረት ከክርስትና ጋር ያለውን ቁርኝት ሲገልጽ:- *"የአሜሪካ መንግሥትና የክርስትና መሠረተ-ሐሳቦች በማይፈታ ቋጠሮ ተሳስረዋል:: በፍጹም አይለያዩም:: እኛ ያገኘነውም ትልቁ ድል ይህ ነው"* ብሏል:: በታሪክ የተረጋገጠው ሁለንተናዊው የአውሮፓ የለውጥና የዕድገት ምክንያቶች አንዱ የ16ኛው ክፍለ ዘመን የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ እንደ ሆነ የታሪክ ምሁራን ይናገራሉ:: ይህም የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ለአንድ አገር ሁለንተናዊ ዕድገትና ለውጥ ወሳኝ መሆኑን ያመልክታል:: በአገራችን በተቃራኒው በተለይ በቤተ ክርስቲያን አካባቢ "ተሐድሶ" የሚለው ቃል በአሉታዊነት መፈረጁ ለለውጥ ያለንን ጥላቻና ጫፍ የነካ ፍርሃት ተጠቂ እንደሆንን ያመለክታል:: ይህም በታሪክ ፊተኞች የነበርነውን የኋለኞች ሁሉ ኋላ አድርጎናል::

ደቡብ ኮሪያ ከዛሬ መቶ ዓመት በፊት ከድህነቷ የተነሣ *"የአይጥ ጉድጓድ"* የሚል አሉታዊ ስም ዛሬ *"የነብር ኢኮኖሚ"* በሚለው ተለውጧል:: ክርስትና አዕምሮአቸውን ብሩህ ከማድረግ አልፎ ባለራእይ እንዲሆኑ፣ በኅብረተሰባቸው ሁለንተናዊ ለውጥ በማምጣት ረገድ የአንበሳውን ድርሻ እንደ ያዘ ኮሪያውያን በገሃድ መስክረዋል:: እ.ኤ.አ በ2003 ሮበርት ባሮ እና ራሄል ማክክሊሪ የተባሉ የታወቁ የሀርቨርድ ዩኒቨርሲቲ የኢኮኖሚ ሊቆች የደቡብ ኮሪያ ዓለምን ያነጋገረ ሕልም መሳይ የኢኮኖሚ ፍንዳታ ለማጥናት ሰፊ ጊዜ ከወሰዱ በኋላ በመጨረሻው:- *"ክርስትና በደቡብ ኮሪያ የኢኮኖሚ ዕድገት ቀዳሚ ሚና ተጫውቷል"* *"Christianity has played a major role in South Korea's economic success."*[111] በማለት በአንዳንድ ኢኮኖሚስቶች ዘንድ ያስተቻቸውን ምስክርነት ለመስጠት ተገደዋል::

የቻይና ኮሚኒስት መንግሥት የኢኮኖሚ አማካሪና የኢኮኖሚክስ ፕሮፌሰር ዞሀ ቺአ የምዕራባውያንን የኢኮኖሚ ምጥቀት ምስጢር እንዲያጠና በቻይና መንግሥት በታዘዘው መሠረት ጥናቱን ሲቋጭ:- *"2000 ዓመታት በዓለማችን ላይ የተገኘው ዐቢይ ለውጥና ዕድገት ምክንያት ኢየሱስ ክርስቶስ ነው"*[112] በማለት ጥናቱን ይፋ አድርጓል:: በዚህም በኢአምላካዊ ፍልስፍና ተወልዶ ያደገው፣ ከዛሬ 60 ዓመታት በፊት የወንጌል ሚሲዮናውያንን ከአገር ያባረረ፣ ቅዱሳንን ወደ ወህኒ በማውረድ አብያተ ክርስቲያናትን በገሃድ የዘጋው ኮሚንስት የቻይና መንግሥት ከራሱ ያራቀው ኢየሱስ ለምዕራባውያን የዕድገታቸው መሠረት እንደሆነ በጥናት የተደገፈ እውነት በራሱ ምሁር ሲነገረው ዱብ ዕዳ እንደሆነበት ይነገራል::

[110] *Koch, Carl(1994), The Catholic Church: Journey, Wisdom, and Mission. Early Middle Ages: St. Mary's Press*

[111] *http://www.economics.harvard.edu/faculty/barro*

[112] *Beyond Economy China's Transformation with the Cross Dr. Peter Zhao Xiao _ TimSchraeder.com htm*

የኮሚኒዝም ርዕዮተ ዓለም መናኸሪያና መሪ የነበረች ሶቪዬት ኅበረት እንደ ቅርጫ ከ15 አገሮች በላይ የተበጣጠሰችው እና ለ70 ዓመታት የሕልም እንጀራ ዓለምን ሲያበላ የቆየው የኮሚኒዝም ርዕዮተዓለም የወደቀው በዓይናችን ፊት ነበር:: ኮሚኒዝም በዓለማችን ከሁለት ቢሊዮን *(ከመቶ 40%)* በላይ የሰዎች ልብ ከመማረክም አልፎ መመሪያቸው ቢሆንም የተከታዮች ብዛት ከሞት አልታደገውም:: ኮሚኒዝም ወድቆዋል ዓለም ከኮሚኒዝም የአመለካከት ተጽዕኖ ገና ነፃ አልወጣችም:: የሶቪዬት ኅብረት ባለሥልጣናት በኮሚኒዝም ውድቀት ማግስት በአምላክ የለሽ ፍልስፍና የተጠመቀው የሶቪዬት ሕዝብ የሞራል እሴት በማጣት እንደጠፋ በገሃድ ተናግረው ነበር::[113] ይህም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክርስትና ለአገርና ለአገር መሪዎች አስፈላጊነቱን ያመለክታል::

## የተቀየጠ ክርስትናችን

ወደ አገራችን ስንመጣ *"ክርስትናችን"* ሃይማኖተኞች አደረገን እንጂ ሕይወታችንን አልለወጠም:: ክርስትናችን አሉታዊ የረሃብና እርስ በርስ የጦርነት ታሪካችንን፣ ለዘመናት ሲዋዥቅ የኖረውን ፖለቲካችንን፣ ዝንተ ዓለም ታማሚ ሆኖ የዘለቀ ኢኮኖሚያችንንና ለእርስ በርሳችን ያለንን የተንሻፈፈ አመለካከቶቻችንን አልሞረደም:: ምክንያቱም በአብዛኛው የክርስትናን ስም እንጂ ወደ ልባችን ክርስቶስ እንዲገባ አልፈቀድንለትምና:: ከመጽሐፍ ቅዱሳዊነት ይልቅ እንደ አገራዊ ባሕል የሚወሰድ "ክርስትናችን" የዕድሜውን ያህል ለምድሩም ሆነ ለሰማዩ እንደሚገባው አልጠቀመንም:: ወደ ቃሉ ክርስትና ለመመለስ ካልፈቀድን ከእንግዲህም አይጠቅመንም:: ክርስትና በኢትዮጵያ ያረጀ ቢሆንም አላደገም:: ሌሎች በመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ላይ ብቻ ክርስትናቸውን መሥርተው ተለውጠው ዓለምን ሲለውጡ የኛ *"ክርስትና"* በአዋልድ፣ በገድላት፣ በድርሳናትና በኦሪታዊ መልኩ በዓለም አቀፋዊ ደረጃ አነጋጋሪ መሆኑ ጥያቄን በውስጣችን ማጫር ሲገባው መጽሐፍ ቅዱስ በማይደግፈን ልዩ መሆን የሃይማኖት ትምክህተኞች ያደረገን ይመስላል::

ክርስትናችን ከአገር በቀል ባሕላዊ የአምልኮ ሥርዓትና ፍልስፍና ጋር ተቀይጦብናል:: እስራኤላውያን ቅይጥ አምልኮ በማካሄድ እግዚአብሔርን ያሳዘኑ እንደነበር ማለት ነው:: *"እግዚአብሔርንም ይፈሩ ነበር ከመካከላቸውም ለኮረብታ መስገጃዎች ካህናት አደረጉ:: በኮረብታውም መስገጃዎች ይሠው ነበር:: እግዚአብሔርንም ሲፈሩ ከመካከላቸው እንደፈለሱት እንደ አሕዛብ ልማድ አምላካቸውን ያመልኩ ነበር" (2ነገ.17:32-33)* ይላል:: በዚህም እግዚአብሔርም በሕዝቡ ድርጊት አዝኖ ሲመክር:- *"ከእናንተም ጋር ያደርግሁትን ቃል ኪዳን አትርሱ፤ሌሎችንም አማልክት አትፍሩ:: አምላካችሁን እግዚአብሔርን ፍሩ፤ እርሱም ከጠላቶቻችሁ ሁሉ እጅ ያድናችኋል"* (2ነገ.17:38-39) ሲል እንመለከታለን:: ሕዝቡ እግዚአብሔርን አልሰሙትም ቅይጥ ሃይማኖታቸውንም አላቆሙም (2ነገ.17:40):: እግዚአብሔርም ለዚህም ይቀጣቸው ዘንድ ለ70 ዓመት ምርኮ አሳልፎ ሰጣቸው:: ሕዝቡ በዙሪያቸው የነበሩ የአረማውያን የአምልኮ ባሕል ይከተሉ እንደነበር ቃሉ ይናገራል (ኤር.25:5-11):: ቅይጥነት በእስራኤላውያን ላይ የእግዚአብሔርን ቁጣ እንዳመጣ እኛም ዛሬ ከተለያየ አገራዊ፣ መንደራዊና ባሕላዊ አመለካከቶችና ሥርዓቶች ጋር ክርስትናን በመቀየጣችን በምድራችን ትልቅ መንፈሳዊ ግራ መጋባት ለምዕተ ዓመታት ተንሰራፍቶ የጨለማና የጥፋት መሠረቱን አጠንክሯል::

ዊልበር አዶናቫን የአፍሪካ ክርስትና ትልቁ ችግር ቅይጥነት እንደሆነ አመልክቶ ይህም የሆነበት ምክንያት ሲገልጹ:- በአፍሪካ ባሕልና ሃይማኖት ስለ ተቆራኙ የአፍሪካ ክርስትናን ከነባሩ ባሕላዊ እሴት ጋር የመቀየጥ ባሕርይ ጎልቶ እንደሚታይበት በጥናታቸው አመልክተዋል:: በመጨረሻም:- *"ቅይጥነት (syncretism) ኃጢአት ነው"*[114] ብለዋል:: ለመሆኑ የአገራችን ክርስትና ከስንት ነገር ጋር ተቀይጦ ይሆን? የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ከአዋልድ፣ ከአገራዊ ትውፊት፣ ከድርሳናትና ከገድላት ጋር ተቀይጦብናል:: በተአምርና በተረቶች ላይ ተመሥርቶ ነገሥታቶችን ለማወደስ በግብዓውያን አርቃቂነት በደብተራዎቻችን የተዘጋጀው የኢትዮጵያ ዐዔዎች ታሪክ ከእሥራኤላዊነት ታሪክ ጋር ተቀይጦብናል:: ይህም ትክክለኛ ማንነታችንን በመረዳት ላይ ትልቅ ግራ መጋባትን ፈጥሮብን ኢትዮጵያውያን የነበሩ ነገሥታቶቻችን የእስራኤላውያን እንደሆኑ በታሪካዊ ጥናት ያልተረጋገጠውን "የንግሥተ ሳባን"[115],[116] ተረት ፈጥረው ሲያውጁ እኛም የእነርሱን ውሸት እንደ ገደል ማሚቶ ሲናስተጋባ ኖረናል:: ይህም በራሱ ማንነት የማኮራ ሕዝብ አድርጎናል:: ከዚህም የተነሣ እውነት መሳይ መላምታዊ አገራዊ

---

[113] Pat Robertson (1990) The New Millennium, USA, p.5

[114] ግርማዊ ቡሽ(ተርጓም) (1996)፣ *መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክርስትና በአፍሪካውያን ዕይታ*፣ ኤስ. አይ. ኤም ማተሚያ ድርጅት፣ ገጽ 364

[115] *ማማን ሙሳ አዳሙ ከመቀሌ ዩኒቨርሲቲ ያቀረቡት ጥናት በከፊል እንዲህ ይነበባል:-* **"The claims of the legend of Queen Sheba do not help us to concretely** understand the foundation of the Ethiopian ruling house because it cannot beproven historically. The legend seemed to have been used to legitimize theclaims by the ruling house to be descendants of Abraham, the chosen people,in order to remain in power in perpetuity. This has affected the identity of theruling house and the entire people of Ethiopia, their heritage, politicalstanding in Africa as well as their being the probable evolutionary home ofthe whole of mankind." Mamman Musa Adamu (*2009)*, Africa Research Review, The Legend of Queen Sheba, the Solomonic, *Dynasty and Ethiopian History: An Analysis An International Multi-Disciplinary Journal Vol. 3 (1), p.480*

[116] *የፕሮፌሰር ታደሰ ታምራት በእንግሊዝኛ ስለ ንግሥተ ሳባ ተረት እንዲህ ቀርቧል*:-"Like all legends they serve the question of establishing an identity, very strong identity. I myself believe this is a post Christian legend... it developed only after the Ethiopians started to have direct contact with the books of the Bible, from about the middle of the 6th Century... And then it became a very important constitutional device and an act of faith. I cannot publicly speak against it in front of the patriarch of the orthodox church, for example, because then he would say, you are no longer an Orthodox Christian. In the days of Emperor Haile Selassie you couldn't speak against the tradition because it would be treasonable to talk against it." *http://www.bbc.co.uk/worldservice/africa/features/storyofafrica/8chapter2.shtml*

ውሸት ፈጥረን ማውራት መለያችን ሆኖ የቀረ ይመስላል። ዛሬም የንግሥተ ሳባ ተረት በታሪካዊ ጥናት መሠረት የለሽ መሆኑን የአገራችን ታሪክ ምሁራን ሳይቀሩ ደጋግመው ጥናታቸውን እየነገሩን የተቀየጠውና የተሳሳተው ታሪክ ዛሬም በብዙዎች እንደ እውነት ይቆጠራል። ወንጌልና ጥቅም፣ ክርስትናና ሃይማኖት፣ ባሕልና ክርስትና፣ ሆድና ወንጌል፣ የወንጌል ሰባኪና በወንጌል የሚነግድ ተቀይጦብናል። መጽሐፍ ቅዱስ ከዘፍጥረት እስከ ራእይ ብቸኛ ቤዛና አዳኝ የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ በግልጽ እየተናገረ በአገራችን ተቀይጦብን ቤዛና አዳኝ *"ማርያም"*[117]፣ *"ሚካኤልም"*[118] ወይም ሌሎችም ሊሆኑ እንደሚችሉ አገራዊ መጽሐፎቻችን ያለ አንዳች እፍረት ይሰብኩናል። በእጃችን ያለው መጽሐፍ ቅዱስ እውነቱን በግልጽ ቢናገርም ቃሉ ላይ ቆመን የተቀየጠውን ለማጥራት አቅም ያለን አይመስልም። ለምሳሌ፡-

# አስማት በክርስትና ጥላ ሥር

በአገራችን በእግዚአብሔር ቃል ፈጽሞ የተወገዙ አስማት፣ ድግምትና ጥንቆላን የሚያስፋፉ ድርሳናት "አገልጋዮች" በቤተ ክርስቲያን አካባቢ እንዳሉ የአደባባይ ምስጢር ነው። ከብዙዎቹ መካከል ድርሳነ ጊዮርጊስ የቅዱሱ የእግዚአብሔር መልአክ ጊዮርጊስ በአስማት ኃይል ስለ ሠራው ሥራ ሲናገር፡-

> *አንተ ቅዱስ ጊዮርጊስ ሆይ በእነዚህ <u>አስማት</u> ኃይል ሰባ ነገሥታትን በዱድያኖስ ፊት እንደ ደመሰስካቸው የእኔንም ጠላቶች እንደ እነርሱ ደምስሳቸው (ቱሳዳን ዘቅዳሜ ገጽ 183)* ለመሆኑ ጊዮርጊስ በአስማት ኃይል ሰባ ነገሥታትን እንደገደለ መጽሐፍ ቅዱስ ጽፎታል እንዴ? የቅዱሱ እግዚአብሔር መላእክና አስማትን ምን አገናኘ? የእግዚአብሔርን መልአክ ሰዎች ጠላቶቻችንን ደምስሳቸው ብለው መላክ ይችላሉ እንዴ? ይህ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ አሳብ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ በአስማት ስለመሥራቱ፡-

> *እነዚህን <u>አስማቶች</u> ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሚካኤል ክንፍ ላይ ጻፋቸው፤ በእነዚህም አስማቶች ዲያብሎስ ከነሠራዊቱ ጨለማን ተጎናጽፎ ወደቀ* (ድርሳነ ሚካኤል ገጽ 62)፣

መጽሐፍ ቅዱስ ዲያብሎስ በልቡ ትዕቢት እንደወደቀና ከሚካኤል ጋር ጦርነት ገጥሞ ተሸንፎ ከሰማይ ወደ ምድር እንደ ተጣለ እንጂ በአስማት እንደወደቀ አይናገርም (ራእ.12:7-10)። ኢየሱስንና አስማትን ምን አገናኘ?

---

[117] ማርያም አዳኝ እንደሆነች በመጽሐፍ ቅዱስ አንድ ቃል የሌለ ሲሆን በተአምረ ማርያም ለመቁጠር የማያዳግቱ ጥቅሶች የማርያምን አዳኝነት በገሃድ ይናገራሉ። ወንጌልና ተአምረ ማርያም ተቀይጦብናል።
[118] የመስከረም ሚካኤል ዚቅ፡- "መላዕክት፣ ጻድቃንና ሰማዕታት ካላከበርናቸው ዋስ ጠበቃና ቤዛ ሊኖረን እንማይችል ይናገራል" ማክበር የተገባ ሆኖ ሳለ በደሙ የገዛንና የዋጀን የሞተልን ቤዛችን ኢየሱስ የት ሄዶ ነው እነርሱ ቤዛ የሚሆኑልን?



*መልአኩ ገብርኤል ወደ ማርያም በተላከ ጊዜ ማርያም እንዳትደነግጥ የሚያደርግ አስማት ተጠቅሞ እንደነበር ድርሳን ይናገራል፡-*

**ግዕዝ፡-** *"መድንኤል፣ ሕያውታኤል፣ አውካኤል፣ ተርቡታኤል፣ ግኤል፣ ዝኤል፣ ቡኤል እሉንተ ቃላት ዘነገሮ እግዚአብሔር ለቅዱስ ገብርኤል ሊቀ መላዕክት አመ ተጻብአ ለዲያቢሎስ ወአመ አብሰራ ለቅድስት ድንግል ማርያም ከመ ኢትደንግጽ..." (መጽሐፈ ቱሳዳን ገጽ 196)።*

**ትርጉም፡-** *"ገብርኤል ዲያብሎስን በተጣላ ጊዜና (ዳን.10:10-21) ማርያምን ባበሰረ ሰዓት(ሉቃ.1:26-36) እግዚአብሔር እነዚህን አስማቶች ለቅዱስ ገብሬኤል ነገረው"*[119]

**ግዕዝ፡-** *"ኦ ኢዮብ ሀበኒ ሀብተ ወሚመተ ወከሥት ንግደትየ ወአርትዕ ፍኖትየ" (መል.ኢዮብ ገጽ 29)*

**ትርጉም፡-** *"ኢዮብ ሆይ ሀብት ስጠኝ ንግዴን ግለጥ መንገዴንም አቅና"*

> *"አቤቱ በዚህ ስምህ በዚህ አስማት ኃይል ፍጥረት ሁሉ የኔን ፈቃድ ብቻ ይፈጽሙ ዘንድ ልቦናቸውን ምታው፣ አቅልጠው፣ ግደለው"(መጽሐፈ ቱሳዳን ገጽ 3-8)* ይህ ሰይጣናዊ እንጂ የክርስትና ትምህርት እንዳይደለ ልቡ የበራና የእግዚአብሔርን ቃል በትክክል የተረዳ ሰው ሁሉ ያውቀዋል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በአስማት፣ በድግምት፣ በጥንቆላ በፍጹም እንደማታምን የታወቀ ነው። ይህን የምንለው መሠረቷ የእግዚአብሔር ቃል ስለ ሆነ ነው። ከላይ እንደተመለከትነው በዘመን ብዛትና ቆይታ በውስጧ ያሉ አንዳንድ ድርሳናት፣ ካህናት፣ ደብተራዎች፣ መሪጌቶች በእግዚአብሔር ቃል የተወገዙና በቤተ ክርስቲያኒቷም ተቀባይነት የሌላቸውን አስማት፣ ድግምት፣ ጥንቆላና መስተፋቅር በስፋት እንደሚያራምዱ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ቀሲስ ደረጀ ገዙ በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ተወለዶ እንዳደገ፣ በገዳም እንዳሳለፈ፣ የዲቁናንና የቅስና ማዕረግ እንደተቀበለ፣ በቤተ ክርስቲያኒቷ ሥርዓት ጋብቻውን እንደፈጸመ፣ በአንድ ትልቅ ገዳም የስብከተ ወንጌል ዋና ኃላፊና አስተማሪ ሆኖ እንዳገለገለ፣ በዘመናዊ ትምህርትም ከባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ተመርቆ በወሎ ዩኒቨርሲቲ መምህር ሆኖ እንደነበር ግለ ታሪኩ ያወሳል። ቀሲስ ደረጀ ገዙ በኦርቶዶክስ በአገልጋዮች ዘንድ ስለተንሰራፋው ጥንቆላ ሲናገር፡-

> *የተንኮል ትምህርት ማለት ጥንቆላ ወይም መጻሐፍ ገለጣ፣ ኮከብ ቆጠራ፣ ሥር መማስና ቅጠል መበጠስ በዚያ አጠራር ጥበብ ...እንደ ግዴታም ነው፤ ምክንያቱም እርስ በርስ ጠብ ይኖራል ያን ጊዜ እራስህን ለመከላከልም ሆነ ያለፈ ነገር ለማደረግ ለመርታት ትንሽም እንኳ እንዳልተማርክ ከተሰማ መጫወቻ ያደርጉሀል፤ በተቃራኒው ከታወቀ ትከበራለህ። ለድርድርና በቀላሉ ወደ እርቅ ትገባለህ ስለዚህ ሁኔታው አስገዳጃጅ ነው ለመማር፤*[120] ብለዋል።

---

[119] ዝኒ ከማሁ፣ገጽ 96
[120] ቢሻሮን ቅጽ 1 ቁጥር 2 ጥር-የካቲት 2004 ገጽ 5

ክርስትና ሌሎችን ማኅበረሰባቸውንና አገራቸውን እንዲለውጡ የሥራ ፈጣሪ ሲያደርጋቸው "ክርስትናችን" በአብዛኛው ሥራን እንደ እርግማን አስቆጥሮን ረሃብ እየጠበሰን በዓል አክባሪዎች ብቻ አድርጎናል:: ይህም ዕድገታችን እረፍት የሚነሣቸው ግብፃውያን ለራሳቸው የማይመሩበትን ዘመን ዘለቅ የሃይማኖት መሪነታቸውን ተጠቅመው እውነትን በተረት ቀይጠው ያቀበሉንና እስከዛሬም እንደ ልዩ መገለጥ የሚታሰቡ ድርሳናት ውጤት እንደሆነ የተረጋገጠ ቢሆንም ከዚህ ቅይጥነት ለመውጣት ዛሬም አልነቃንም:: *"ድርሳነ ሚካኤል የተባለ መጽሐፍ ባለበት አገር ረሃብ፣ ቸነፈርና በሽታ አይኖርም"*[129] የሚል አደገኛና ገዳይ መርዝ ስላመንን የድርሳናት ኅተራ ቢኾንም ችግራችንን አወሳስበው ግራ ከማጋባት ያለፈ አንዳች አልፈየዱልንም:: በዓለም ላይ የስልጣኔ ማዕከልና ቀዳሚ በሆነች አገር እየኖርን ዛሬም መታወቂያችን ረሃብ፣ ድህነት፣ በሽታ፣ ስደት፣ ጥላቻና መንደርተኝነት ነው:: ይህ ሁሉ ሆኖ ልብ ሰባሪው ጉዳይ ዛሬም በኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ድርሳናትና ገድላት የተማረከው ልባችን ጠያቂ ለመሆን ያለመፍቀዱ ነው::

ዶክተር በቀለ ሻንቆ ለትራንስፎርሜሽናል መሪነት በቤክ ዩኒቨርሲቲ የፒ.ኤች.ዲ ማሟያ ባቀረቡት ጥናታቸው:-

> *የኢትዮጵያ ክርስትና ከፍተኛና አስደናቂ የቁጥር ብዛት ቢያስመዘግብም እንደሌሎቹ በአገሪቷ ማህበረሰብና ኢኮኖሚ ላይ ተጠቃሽ ውጤት አላስመዘገበም*[130] ብለዋል::

*"ሰው ምራቁንና ሃይማኖቱን ይወዳል"* እንድ የአገሬ አዋቂ እንዳሉት ስሙን እንጂ ውስጡን በትክክል ለማናውቀው አገር በቀል *"የክርስትና"* ሃይማኖታችን ጥብቅና ለመቆም መቁረጣችን መልካም ሆኖ ሳለ አስደንጋጭ የሚሆነው ክርስትናችን በመጽሐፍ ቅዱስ ከተገለጠው የክርስቶስ ትምህርት ጋር በብዙ መጣረሱ ነው:: ያልታደሰውና በብዙ አስተምህሮዎች ከመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ጋር ፊት ለፊት የሚላተመው አገር በቀል ክርስትናችን፣ የዚህች ታላቅ ጥንታዊ አገር ውድቀት አንዱ ምክንያት ነው:: ይህን የምለው ላለፈው ታሪካችን እንድንቆጭ ወይም ሌላ ሰጥ-አገባ ለመጫር ሳይሆን የክርስትናችን ማዕከል የክርስቶስን ቃል በማድረግ ለተሐድሶ እጅ ለእጅ ተያይዘን በመቆም ለአገራችን ሁለንተናዊ ለውጥ የበኩላችንን አንፀባራቂ ሚና በአንድነት ለመጫወት እንደገና እንድንነሣ ነው:: ለዚህ ግራ መጋባትና ዘመን ዘለቅ ቀውስ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ተሐድሶ መልስ ነው:: በኢትዮጵያ ያሉት ቤተ እምነቶች በሙሉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ተሐድሶ የግድ ያስፈልጋቸዋል:: ቤተ ክርስቲያን በእግዚአብሔር ቃልና መንፈስ ታድሳ የሁለንተናዊ ተሐድሶ ፋና ወጊ ካልሆነች እንቅፋት መሆኗ ይቀጥላል::

[129] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 89

[130] Bekele Shanko Mamiru,*(2012), Emerging Leader Initiative (ELI), A Manual for Developing Transformational Leaders in the Ethiopia Context A Final Project Submitted to* ***The*** *Faculty in Candidacy For The Degree of Doctor of Transformational Leadership* p viii





## የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በዓለም ላይ በጥንታዊነት ከሚታወቁት አብያተ ክርስቲያናት መካከል አንዷ ናት፤ በቀዳሚነቷም በአገር ውስጥ ላሉት አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ እንደ እናት የምትጠቀስና የኢትዮጵያ ታሪክ አካል የሆነች ትልቅ ቤተ ክርስቲያን ናት:: ስለ ኢትዮጵያ ታሪክ ለማጥናት የሚነሣ የትኛውም አካል ከመንግሥት ጋር በጥምረት ለብዙ ምዕተ ዓመታት አገርን ትገዛ ስለነበረችው ስለዚህች ቤተ ክርስቲያን ለመጥቀስ ብቻ ሳይሆን ለማጥናት ግዴታ ውስጥ ይገባል::

ያለ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ የኢትዮጵያ ታሪክ ብቻውን ሙሉዕና ትርጉም ያለው አይሆንም:: የቀደምት ሥልጣኔ ባለቤት የሆነችው አገራችን የራስዋ ፊደል፣ ቁጥርና የዘመን ቀመር ባለቤት ያደረጓት የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቀደምት አበው እንደሆኑ ታሪክ ምስክር ነው:: ለዚህ ድንቅ ሥራ አድናቆትና ክብር ልንቸራት ይገባል:: ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ ስላሉ የተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት ለመናገር ስንፈልግ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መጀመር የግድ ይለናል:: እንደ አክሱም ሐውልት፣ እንደ ላሊበላና የዐፄ ፋሲል ግንቦች የጸና ታሪክ ባለቤትና የአገር ኩራት ስለሆነችው ስለዚህች ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ:: እግዚአብሔር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ይባርካት፤ በማለት ለእርሷ ያለኝን ትልቅ ፍቅርና አክብሮት ስገልጽ ራሴን እንደ ዕድለኛ በመቁጠር ነው::

በዚህ መጽሐፍ ከ4ኛው እስከ 21ኛው ክፍለ ዘመን የዘለቀና የአስደናቂ ታሪክ ባለቤት የሆነችውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንና ከእርሷም በኋላ በዚህ ምድር የተገለጡ አብያተ ክርስቲያናትን በስሜት ላይ በመንተራስ ሳይሆን በእግዚአብሔር ቃል፣ በምክንያታዊነትና በጥናት የተደገፈ መረጃን በማቅረብ በቃሉና በመንፈሱ እንዲታደሱ መለኮታዊ ጥሪ ቀርቧል:: ተሐድሶ ለምን? ለሚለው ጥያቄ መልሱ በምድራችን ያሉት አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ በተሐድሶ ጠሪ ተጨባጭ ሁኔታ ውስጥ መገኘታቸው ነው::

## የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ዛሬ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በተሐድሶ ጠሪ ሁኔታ ውስጥ እንዳለች መነገር ከተጀመረ ምዕተ ዓመታት እንደተቆጠሩ ድርሳናት ያወሳሉ:: በቤተ ክርስቲያን የእውነት ሚዛኑ የሰዎች ድጋፍና ተቃውሞ እንዳልሆነ ሁሉ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንም ተሐድሶ እንደሚያስፈልጋት ወይም እንደማያስፈልጋት ወሳኙ የቤቱ ባለቤት የሆነ ቃሉና ቤተ ክርስቲያኒቷ ያለችበት ተጨባጭ ሁኔታ እንጂ የችሎት ውሳኔ፣ የክርክርና የእጅ ብልጫ ነው ብዬ አላምንም:: ቤተ ክርስቲያን በሰዎች ክርክርና በችሎት ውሳኔ አልተመሠረተችም፤ አትመራም፤ አትታደስም::

ቤተ ክርስቲያኒቷ ተሐድሶ እንደሚያስፈልጋት ለማረጋገጥ የትናንት ታሪኳና ዛሬ ያለችበት ተጨባጭ ሁኔታ ምን ይመስላል? በብዙ ተጋድሎ ከአንድ ሚሊኒየም ተኩል በላይ ሃይማኖቷን ጠብቃ ረዥም ዕድሜን ባስቆጠረች ቤተ ክርስቲያን በውስጧ ምን እየተካሄደ ነው? ለሚሉ ጥያቄዎች በቤተ ክርስቲያኒቷ ተወልደው፣ አድገው፣ ተምረውና ለአገልግሎት የበቁ አገልጋዮች ከጻፉት የመንደርደሪያ ሐሳቦች እዚህ ጋ ብጠቅስ መልካም ነው:: ቀሲስ መዘምር ወልደ ሩፋኤል የአቃቂ መንበረ ሕይወት መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን የስብከት ወንጌል ክፍል ኃላፊ[131] *"ፈውስ ለቤተ ክርስቲያን"* በሚል መጽሐፉ:-

> *በጣም የሚገርመው ነገር፣ በዓለማችን አሠራሮች ሁሉ በፍጥነት እየተቀየሩና እየተለወጡ ባሉበት ዘመን ላይ ሆነን፣ የእኛ ቤት ሰዎች ግን በአረጀ አስተሳሰብ ተጠፍረው፣ ቤተ ክርስቲያኒቱ ከዘመን ጋር እንዳትራመድ አድርገዋታል[132] እኛ ትናንት በቁጥር ብዙ ነበርን፣ ዛሬ ብዙ ወገኖቻችን አንድ አንድ እያሉ ፊታቸውን ወደ ሌሎች የእምነት ተቋማት አዙረዋል:: በቅርቡ ይፋ በሆነ መረጃ እንኳ፣ የምዕመናኖቻችን ቁጥር 7,000.000 (ሰባት ሚሊዮን) ቀንሷል::[133] ሥልጣንን በሞኖፖል አንቆ በመያዝና የእከከኝ ልከክልህ አሠራር በቤተ ክርስቲያናችን የቆየና የተለመደ ነው:: እንዲህ ዓይነቱ የአረጀ አሠራር ካልተቀየረ ደግሞ፣ ለውጥና ዕድገት በተአምር አይመጣም[134] ከዲቁና እስከ ጵጵስና ያሉት መንፈሳዊ ክንውኖች ሁሉ፣ ያለ ሙስና የማይታሰቡ እየሆኑ መምጣታቸውን በዚህ መንገድ ያለፉ ሁሉ እንደበታቸውን ሞልተው እየተናገሩ ነው[135] በዘረኝነት መንፈስ የሚናጡ አብያተ ክርስቲያናት ቁጥር ቀላል አይደለም:: ...ከአለቃው (አስተዳዳሪው) ይጀምርና ቀስ እያለ ወደታች (ወደ ካህኑ) ይሠርፃል:: 'ሸዋ፣ ወሎ፣ ጎጃም፣ ጎንደር፣ ትግራይ...' ተብሎ በስምና በአካባቢ ያልተፈረጀ አይኖርም:: እንደተባለውም ዘረኝነትን የሚያራግቡ መንደርተኞች ጥቂት አይደሉም:: በየተዛውሩበት ደብር ሁሉ የአገር ሰው ብቻ የሚጎትቱ፣ ሌላውን አገልጋይ በጥርጣሬና በሥጋት የሚያዩ፣ የቤተ ክርስቲያን ዕዳዎች ሞልተዋል::[136]* በማለት ቤተ ክርስቲያናቸውን የገጠማትን ውስጣዊ ተግዳሮቶች ይፋ አድርገዋል::

አባላት ከኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ወደ ፕሮቴስታንት ለምን ይፈልሳሉ? ለሚለው ጥያቄ የሁለት የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች መልሳቸውን ብጠቅስ መልካም ይመስለኛል:- ሊቀ ማእምራን ዲበ ኩሉ *"የቃሉን እውነት ካለማስተማራችን የተነሣ ሕዝባችን ወደ ፕሮቴስታንቱ እየፈለሰ ነው"*[137] ብሎ ምክንያቱን ካቀረበ በኋላ ቤተ ክርስቲያኒቷ ተሐድሶን የማትፈቅድ ከሆነ ሕልውና የማጣት አደጋ ከፊት ለፊቷ

[131] *መዘምር ወ/ሩፋኤል (ቀሲስ) (2005 ዓ.ም) ፣ ፈውስ ለቤተ ክርስቲያን፣. ገጽ 29*
[132] *ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 29*
[133] *ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 72*
[134] *ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 31*
[135] *ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 35*
[136] *ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 55*
[137] ሎ-ፌ, 2005 ዓ.ም ገጽ 84



እንደተጋረጠባት:- *"አሁን ባለው ፍጥነት ከቀጠለና ተሐድሶን አንቀበልም የሚል ግትር አቋም ከያዝን በጥቂት ዓመታት ውስጥ ቤተ ክርስቲያናችን ሕልውናዋን ማጣቷ አይቀሬ ነው"*[138] በማለት ከመቶ ዘጠና አምስቱ ሕዝባቸው ክርስቲያኖች የነበሩና የታላላቅ ዓለም አቀፍ ተጽዕኖ ፈጣሪ ቀደምት የነገረ መለኮት ምሁራን ያፈለቁ ግብፅና ሊቢያ የመሳሰሉ አገራት በሌላ ሃይማኖት እንደተወረሱ ካልነቃን ለእኛም አይቀርልንም በማለት ፍርሃቱን ይፋ አድርጓል::

መምህር ብሩክ ገብረ ሊባኖስ ተስፋዬ ከሕፃንነቱ ጀምሮ ዕድገቱ በቆሎ /አብነት/ ትምህርት ቤት እንደሆነ፣ የቅዱስ ያሬድን ጸዋትወ-ዜማዎች፣ አቋቋምና ቅኔን እንዳጠናቀቀ፣ በመጨረሻም በቅዱስ ጳውሎስ መንፈሳዊ ኮሌጅ የሚሰጠውን የትርጓሜ መጻሕፍትና ባሕረ ሐሳብ አጠናቆ በ1991 እንደተመረቀ በመጽሐፉ ተጠቅሷል:: በአገልግሎትም በአዲስ አበባ ውስጥ በተለያዩ አድባራትና ገዳማት የስብከተ ወንጌል ኃላፊ ሆኖ ዘጠኝ ዓመት እንዳገለገለና አሁንም በአውስትራሊያ ቤተ ክርስቲያኒቷን በማገልገል ላይ እንዳለ ይገልጻል:: መምህሩ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን ወደ ሌላ እምነት ለምን ይሄዳሉ? ለሚለው ጥያቄ መልሱን ጥያቄያዊ አድርጎ መልሶአል:-

> *አሁንም ሐቁን እናውጣና ሰዎች ኦርቶዶክስን ጥለው ወደ ሌላ በረት የሚሄዱት ምክንያት ወደድንም ጠላንም ችግሩ ከላይ እስከ ታች ባለን የቤተ ክርስቲያኒቱ አገልጋዮችና ሠራተኞች ችግር ምክንያት ነው:: ምክንያቱ ምንድነው? ቢባል*

- *ሰባኪዎች የተባልነው የሕይወት ምግብ የሆነውን የእግዚአብሔርን ቃል በስፋትና በጥራት እንዲመገቡ ባለማድረጋችን አይደለም?*
- *የማያጠግብና ሕይወትን የማይለውጥ ተረታ-ተረት እንዲመገቡ በማድረጋችንስ አይደለም?*
- *ብዙዎቻችን በቃላችን እንጂ በሕይወታችን ማስተማር ስላልቻልን አይደለምን?*
- *የንስሐ አባቶች የተባሉት ብዙዎቹ ዕውቀታቸው በቂ ባለመሆኑ ስለመጽሐፍ ቅዱስ ሲጠየቁ ተገቢ መልስ መስጠት አለመቻላቸው እውነት አይደለምን?*
- *ዘረኝነትን በወንጌል ማጥፋት ሲገባን የዘረኝነቱ ዋና፣ መሪና ተዋናይ ሆነን ሕዝቡን በጐሣና በብሔር መለያየታችን እውነት አይደለምን?*
- *ምዕመናን በተለያዩ ድግሳ-ድግሶች ሆዳችንን ስለሚሞሉን ሲያጠፉና ሲሳሳቱ ከማረምና ከመገሠጽ ይልቅ 'እንደ እናንተ ያለ ክርስቲያን የለም! እያልን የምንሸነግላቸው አይደለምን?*
- *ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በማመን የሚገኘውን ዘላለማዊ ደኅንነትና ዕረፍት እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ሐሳብ ገልጠን ባለማስተማራችን አይደለምን?*

[138] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 84

- *የሰላምና የፍቅር ሰዎች መሆን ስገባን ሰላምን፣ ፍቅርን፣ አንድነትን የምናደፈርስ ሰውን የምናስበረግግ አይደለምን? በእነዚህና በመሳሰሉት ችግሮቻችን ምክንያት ሕዝባችን ለፍልሰት ተዳርጓል፤ ስለሆነም ተጠያቂዎቹ እኛው ራሳችን የቤተ ክህነት ሰዎች ነን፤*[139] ብለዋል::

ከላይ የተዘረዘሩ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አባላት የፍልሰት ምክንያቶች ከሆኑ ተሐድሶ ለዚህች የአገር ኩራትና እናት ለሆነች ቤተ ክርስቲያን አያስፈልግም ማለት እንዴት ይቻላል? ተሐድሶ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሞትና ሕይወት ጉዳይ እንደሆነ ከላይ ያሉ ተጨባጭ ሁኔታዎች ያመለክታሉ ። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ያለመታደስ ለቀለመ ብዙ አገራዊ ችግሮች መሠረት መሆኑን አንዘንጋ::

# ኢመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮዎች

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በዓለማችን በዕድሜ ጠገብነቷ ብቻ ሳይሆን ለአሥራ ስድስት ምዕተ ዓመታት የራሷንና የዚህችን አገር ታሪክ ከነገሥታት ጋር እጅና ጓንት ሆና እንዳቆየች ይታወቃል:: ይህ ትልቅ ነገር ነው:: በተቃራኒው ደግሞ ግልጽነት የሚጎድላቸውና ከመጽሐፍ ቅዱስ በተለይ ከአዲስ ኪዳን አስተምህሮ ጋር በፍጹም የማይሄዱ፣ ባዕድ ልምምዶችንና አስተምህሮዎችን እንደ ተሸከመች በእርሷ ውስጥ ተወልደው ያደጉና ለአገልግሎት የበቁ "ቤተ*ክርስቲያናችን ወደ ቃሉ ተመልሳ መታደስ አለባት" ብለው* ድምፃቸውን ማሰማት ከጀመሩ ምዕተ ዓመታት ተቆጥረዋል:: ከመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ጋር በቀጥታ የሚጋጩና መታደስ እንዳለባቸው ከተነሡ አሳቦች መካከል ሁለቱን እዚህ ላንሳ:-

## የተለጠጠ የነገረ ማርያም

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፈ ቅዳሴ ስለ ማርያም መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት ያዘለ ሐሳብ እንዲህ ይነበባል:- *"...ከሴቶች ሁሉ ተለይተሽ አንቺ የተባረክሽ ነሽ የማህፀንሽ ፍሬ የተባረከ ነው:: ጸጋን የተሞላሽ ሆይ! ደስ ይበልሽ፤ እግዚአብሔር ካንቺ ጋር ነውና..."*[140] እንደሚለው ብፅዕት የሆነችው ማርያም በታዋን ያወቀችና ጌታን በታማኝነት አገልግላ ያለፈች ታላቅ ሴት ናት:: እርሷ የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ እናት፣ ከሐዋርያቱም ጋር የነበረች፣ በእምነቷ፣ በቅድስናዋ፣ በብፅዕናዋና በመታዘዝዋ ለቅዱሳን ሁሉ ታላቅ ምሳሌ ናት:: ከዚህም የተነሳ ልትወደድ፣ ልትደነቅ፣ ልትመሰገን የሚገባት ከሴቶች መካከል ሞገስ ያገኘች ልዩ ሴት በመሆኗ ክብር ይገባታል:: *"ክብር ለሚገባው ክብር ስጡ" (ሮሜ.13:7)* ያለው ቃሉ ነውና:: ማርያም እግዚአብሔርን በመታዘዝ ለሁላችንም ትልቅ ምሳሌነትና በመሥዋዕትነት ጌታን ካገለገሉት ቅዱሳን መካከል ቀዳሚ ተጠቃሽ ናት:: እንወዳታለን፤ እናከብራታለን ማለቱ የተገባ ሲሆን ያለቦታዋ በግድ እንዳናስገባት ግን እንጠንቀቅ:: *"ከተጻፈው አትለፍ"* (1ቆሮ.4:6) የሚለውን ቃል እናስተውል::[141]

ቀደሰ ዓለማየሁ ሞገስ ደረሰ ስለማርያም በአገራችን ጫፍ የነካ የማርያም አስትምህሮ የተናገሩትን ከመጥቀሴ በፊት ስለማንነታቸው ያሉትን ልጥቀስ:- *"እኔ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በዘራቸው በሃይማኖታቸው፣ በብቃታቸው፣ በትንቢታቸው፣ ከታወቁ ቤተሰቦች ተወልጄ ያደግሁ"* ካሉ በኋላ ስለ አገልግሎታቸውና የሕይወት ልምዳቸው:- *"የቅኔ መምህር ሆነው መጻሕፍት ሐዲስን እንዳጠኑ፣ ዘጠኝ የተለያዩ ቋንቋዎችን አቀላጥፈው ይናገሩ እንደነበር፤ ወደ ዩኒቨርሲቲም ዘልቀው ታሪክና ቋንቋን አጥንተው እዚያው መምህር ለመሆን የበቁ ሊቅ እንደነበሩ"*[142] ገልጸዋል:: ይህ ታላቅ ሰው በእግዚአብሔር ቃል ላይ ቆመው ቤተ ክርስቲያናቸው ወደ ቃሉ እንድትመለስ እና በሌሎች አብያተ ክርስቲያናትም ላይ የሚታዩ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ አካሄዶችን በመሞገት ይታወቃሉ:: ቀደሰ ዓለማየሁ *"ሁሉም ሁሉን ይወቅ"* በሚለው መጽሐፋቸው ማርያም በትውልድ ሁሉ ምስጋና እንደሚገባት ከገለጹ በኋላ በቤተ ክርስቲያናቸው ስለ ማርያም የተለጠጠና ወንጌልን ስለ ጋረደው አስትምህሮ ሲናገሩ:-

> *ለማርያም የታዘዘው ምስጋና ከአምስት አንድ ነው:: በእኛ ቤተ ክርስቲያን ግን በጣም በዛና ወንጌል እንዳትሰበክ ከለከለ:: በሰዓታቱ፣ በማሕሌቱ፣ በኪዳኑ በቅዳሴው ሁሉ እሷ ናት፤ ወንጌል እናንብ የተባለ እንደሆነ ታምሯ ሳለች ይባልና የወንጌሉ ነገር ይረሳል:: ስለዚህ የእኛ ቄሶች ከተአምረ ማርያም ውጭ በማሕሌት ኪዳን በሰዓታት ተወጥረው ስለተያዙ ይሁን የጠቀስነውን ኪያዙ ስለሃይማኖት ባያውቁ አይፈረድባቸውም:: መልሳቸውም ከቅዱሳት መጻሕፍት ጋራ የማይስማማው ገድላገድልና ተአምረ ማርያም ነው:: የእኛ ማርያም ወዳጆች ማርያም በሥላሴ ላይ መፈንቀለ መንግሥት ያደረገች አስመስለው ሥላሴን አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስን ትተው ቅዱሳት መጻሕፍት እንዳይሰበኩ ማድረጋቸው ነው እንጂ*[143] ብለዋል::

ኢየሱስ አገልግሎቱን አሀዱ ብሎ ሲጀምር *"የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ"(ማቴ. 4:17)* በሚል ግልጽ ስብከት እንጂ የእናቱ ስም በማወጅ አልነበረም፤ ሐዋርያትም ስሟን በየቀኑ መስበክ እንዳለባቸው አላዘዛቸውም:: ሐዋርያት በስብከታቸው፣ በትምህርታቸውና

[139] መምህር ብሩክ ገበረ ሊባኖስ ተስፋዬ *(2005 ዓ.ም)* ፣ *የሰው ያለህ*፣ ገጽ 435-336

[140] የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፈ ቅዳሴ፣ ፊደል አሳታሚ፣(ዓ.ም) የለውም፣ ገጽ 104

[141] ፀጋአብ በቀለ (2005 ዓ.ም) *ባለራእይነት ኢትዮጵያ ግን ለምን? ርዋቦት አታሚዎች*

[142] ዓለማየሁ ሞገስ ደረሰ(ቀደሲ) (1987 ዓ.ም)፣ *ሁሉም ሁሉን ይወቅ*፣ ገጽ 10

[143] ዝኒ ከማሁ ገጽ 155

በመጽሐፋቸው ትኩረታቸው በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ እንጂ በማርያም ላይ በፍጹም አልነበረም:: ኢየሱስ ሐዋርያትን ሲልካቸው:- *"ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ለፍጥረት ሁሉ ወንጌልን ስበኩ" (ማር.16:15)* በማለት ወንጌል መስበክ/ማወጅ እንዳለባቸው በግልጽ ተናግሯል:: ሐዋርያው ጳውሎስ ስለዚህ ሲናገር:- *"እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን"* (1ቆሮ.1:23) ካለ በኋላ ከዚህ ውጭ የሰማይ መላዕክት እንኳ ቢሆኑ *"ሌላ ወንጌል የሚሰብካችሁ የተረገመ ይሁን" (ገላ.1:8-9)* በማለት ቤተ ክርስቲያን ወንጌልን ትታ ሌላ ነገር የምትሰብክ ከሆነ የሚጠብቃት እርግማን እንጂ በረከት እንዳልሆነ በግልጽ አስቀምጧል:: በአገራችን በግልጽ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የሚጋጩ፣ ለማርያም የሥላሴን ቦታ የሰጡና በቅርብ ጊዜ እንደ ወንጌል በአንዳንድ ቡድኖች ያለ ክልካይ እየተሰበኩ ያሉ አሳዛኝና አስደንጋጭ አሳቦች መካከል:-

## ሀ. "ያለ እመቤታችን ዓለም አይድንም"

ይህ የእግዚአብሔርን ቃል ካለመረዳት አንዳንዶች የሚያውጁት የተሳሳተ አሳብ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስን አንብቦ የተረዳ ማንም ሰው ያውቀዋል:: ማርያም የዓለም መድኃኒት የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ዓለም የመጣበት መንገድ እንጂ መድኃኒት እንደሆነች፣ እርሷም አልተናገረችም፣ ኢየሱስም ስለ እርሷ እናትነት እንጂ መድኃኒትነት በፍጹም አልገለጸም፤ ሐዋርያትና የቤተ ክርስቲያን አበው ይህን በፍጹም አልሰበኩም፤ አልጻፉም:: የማርያም እጮኛ ለነበረው ዮሴፍ መልአክ በሕልም ተገልጦለት ከማርያም የሚወለደው ልጇ እንጂ እርሷ መድኃኒት እንደሆነች አልተናገረም:- *"ልጅ ትወልዳለች እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ"(ማቴ.1:21)*:: ሳምራውያን ኢየሱስን ካዩት በኋላ:- *"በእውነት ክርስቶስ የዓለም መድኃኒት እንደሆነ እናውቃለን"* (ዮሐ.4:42) በማለት መስክረዋል:: የዓለም አዳኝ በማርያም በኩል ወደ ዓለም የመጣው እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ እንጂ ማርያም እንደሆነች መጽሐፍ ቅዱስ አይናገርም::

## ለ. "ያለ እመቤታችን ሥላሴ አይታወቅም"

ልዑሉ እግዚአብሔር (አሐዱ-ሥላሴ) በፈለገው መንገድ ራሱን ካልገለጠ በስተቀር ማንም ሊያውቀው አይችልም:: ያለ እግዚአብሔርና እርሱ ከፈቀደው መንገድ በስተቀር እግዚአብሔርን በትክክልና በሙላት የሚገልጥ አካልም ሆነ መንገድ በምድር አልነበረም፣ የለም ወደፊትም አይኖርም:: ኢየሱስ ሲናገር *"...ከአብ በቀር ወልድን የሚያውቅ የለም፤ ከወልድም በቀር፡ ወልድም ሊገለጥለት ከሚፈቅድ በቀር አብን የሚያውቅ የለም"(ማቴ.11:27)* በማለት የአብ ገላጭ ወልድ እንደሆነ የወልድም ገላጭ አብ እንደሆነ በግልጽ ተናግሯል:: ስለ ሥላሴ ስንነጋገር መዘንጋት የሌለብን ወልድ ባለበት አብና መንፈስ ቅዱስም መኖሩ ነው:: ያለ ማርያም ሥላሴ





እንደማይታወቅ የእኛ እንጂ የሥላሴ ቃል አይናገርም:: ዋናው መንገዱ ሳይሆን መገለጡ ነው:: መንገዱን የሚመርጠው ደግሞ የመገለጡ ባለቤት የሆነው እግዚአብሔር ብቻ ነው:: እግዚአብሔር ሉዓላዊና ውስን ያልሆነ አምላክ ስለሆነ ውስንና ደካማ ለሆነ ለሰው ልጅ በፈለገው መንገድ የመገለጥ ሙሉዕ ብቃትና ምርጫ ያለው አምላክ ነው:: ስለሆነም *"ያለ እመቤታችን ሥላሴ አይታወቅም"* ማለት ቃሉን በትክክል ያለመረዳታችንንና አምላክን እንደራሳችን የመገደብ ደካማ ሙከራችንን ያሳያል:: እግዚአብሔር ራሱን የሚገልጥ አምላክ ነው:: ራሱን በሰው ሕሊና፣ በተፈጥሮና በቃሉ ገልጧል:: በመጨረሻም ከድንግል ማርያም በተወለደው ልጁ ራሱን ገልጧል:: ማርያም ወልድ ሥጋን ለብሶ ወደ ዓለም የገባበት መንገድ እንጂ የሥላሴ ማሳወቂያ ብቸኛ መንገድ እንደሆነች መጽሐፍ ቅዱስ በፍጹም አይናገርም:: ማርያም እግዚአብሔር ልጁን ወደ ዓለም ያመጣበት መንገድ እንጂ የሥላሴ ማሳወቂያ መንገድ አልነበረችም፣ አይደለችም እንዲሁም መሆን አትችልም:: ማርያምን የምናከብራት በእግዚአብሔር ቃል ያልተባለላትን በማለት መሆን የለበትም::

## ሐ. "ሁሉ በእርሷ (በድንግል) ሆነ"

*ቃሉ ያለው:- "ሁሉ በእርሱ ሆነ ከሆነውም አንዳችም ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም" (ዮሐ.1:2)* የተባለለት የሥላሴ አንዱ አካል ለሆነውና በዚህ ክፍል "ቃል" ለተባለው ለእግዚአብሔር ወልድ ነው:: ይህን ቃል በመግፋት ሁሉ "በእርሷ"(በማርያም) ሆነ በማለት "በእርሱ" (ክርስቶስ) የተደረገውንና በቃሉ የተጻፈውን እውነት እንዳለ ከማመን ተደናገሮ ማደናገር ለምን አስፈለገ? የተባለውን ማመን እንጂ ለእኛ እንደሚመቸን አድርገን አስተካክለን መጻፍ፣ መናገርና ማመን ከእግዚአብሔር በላይ አዋቂነታችንን ለመግለጥ ብርቱ መሻት እንዳለን ቢያመለክትም ገሃድ የሚታየው ግን ያላዋቂነታችን ነው::

## መ. "የእመቤታችንን ስም የሚጠራ አያፍርም"

*መጽሐፍ ቅዱስ:- "እነሆ የተመረጠና የከበረን የማዕዘን ራስ በጽዮን አኖራለሁ <u>በእርሱ የሚያምን አያፍርም"</u>* (1ጴጥ.2:6) ያለውን *"በእርሷ የሚያምን አያፍርም"* ብሎ መለወጥ በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተደረገ የድፍረት ኃጢአት ነው::

## ሠ. "ቤዛዊተ ዓለም፤ ቤዛዊት ኩሉ"

ይህ ለማርያም የተሰጣት ስም ኢየሱስ ክርስቶስ ብቸኛ የዓለም ቤዛ መሆኑን ለመተካት የወጣ ስም እንደሆነ ለማንም ግልጽ ነው:: ኢየሱስ ብቸኛ የዓለም ቤዛ ነው(ማቴ.20:28):: ማርያም የዓለም ቤዛ ከሆነች ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለም ቤዛ ሆኖ መምጣት ለምን አስፈለገው? ዓለም አንድ እንጂ

ቅዱስ ዐቢይና ብቸኛ ስለሆነው የኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ እንዲሁም የቤዛነት ሥራው ሳይሆን ስለ ማርያም፣ ስለ መላዕክት፣ ስለ ዝክር፣ ስለ ታቦት፣ ስለ ባሕታዊነት፣ ስለ በዓላት ከድነት ጋር በማያያዝ ያለገደብ ያወራሉ፡፡ ይህም በምድራችን የተዛባ ነገረ ድነት ምን ያህል ሥር የሰደደ መሆኑንና ልባችን ያለበትን ቦታ ያመለክታል፡፡ ማስተማራችን ባልከፋ አሳዛኙ ነገር ከእግዚአብሔር ጋር እንዳለን በኩራት ታሪክን እያጣቀስን እያወራን በእጃችን ካለው ከቃሉ ርቀን መገኘታችን ነው፡፡

በአገራችን ከወንጌል ይልቅ ማርያምን እንደ ፈጣሪ የመቁጠር፣ የማምለክና የፈጣሪን ስግደት እንደሚገባት የሚናገሩ ኢክርስትናዊ ትምህርቶች የተለመዱ ብቻ ሳይሆን የሕዝባችንን ልብ ሰርቀዋል፡፡ ጥንት ግን እንዲህ አልነበረም፡- *"15ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ ለድንግል ማርያም መገዛት፣ መስገድ፣ ስለ እርሷ መዘመርና ልዩ ልዩ በዓላቷ የሚባሉትን ማክበር በስሚም መለመንና መንግሥተ ሰማያት ለመግባት ተስፋ ማድረግ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ፈጽሞ አልነበረም"*[151]

## ተአምረ ማርያም-የተዛባ የነገረ ማርያም መሠረት ነው

ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊና ጫፍ የነካ የነገረ ማርያም ትምህርት በምድራችን በከፍተኛ ሁኔታ የተስፋፋው "ተአምረ ማርያም" በሚባለው መጽሐፍ በኩል እንደሆነ መዛግብቶች ያወሳሉ፡፡ *ተአምረ ማርያም መጽሐፍ ስለራሱ ሲመሰክር ከአረብኛ ቋንቋ ወደ ግዕዝ በንጉሥ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመን ተተረጎምሁ በማለት ለራሱ ምስክርነቱን ሰጥቷል፡፡*[152] የኢየሱስ ክርስቶስን አዳኝነት፣ የወንጌልን እውነት በግልጽ የሚቃወሙ፣ በጳጳሳትና በነገሥታት ስምምነት በቤተ ክርስቲያን ቦታ የተሰጠው ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ መጻሕፍት መካከል አንዱ በሆነው ተአምረ ማርያም ውስጥ የተጻፉና ከመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ጋር በግልጽ የሚጋጩ አሳቦች ጥቂቱን እንመልከት፡-

- *ለኃጢአን መድኃኒታችሁ ስለ ሆነች (መቅድም ገጽ 4 ቁጥር 33፤ ገጽ 5 ቁጥር 34)*
- *ከኃጢአት ታነጻዋለች (ተአምር 12 ገጽ 48 ቁጥር 54፣ 56፣ 62)*
- *በርሷ ላመኑት ድነታቸው ነች (ተአምረ ማርያም 63 ገጽ 198 ቁጥር 13:37)*
- *ባንቺ ድነት አገኘን (ተአ 12 ገጽ 44 ቁጥር 13*

[151] ከሣቴ ብርሃን መጽሔት፣ ሴነ 2002 ዓ.ም ገጽ 13
[152] ዝኒ ከማሁ ገጽ 20






- *እመቤታችንን የዓለም መድኃኒት እንዳደረጋት እውቁ (ተአምረ ማርያም 12 ቁጥር 62)*
- *የዓለም ሁሉ መድኃኒት ሆይ (ተአምር ማርያም 83 ቁጥር 25 ተአ. 84 ቁጥር 11)*
- *"እንደ እኔ ያላችሁ ኃጢአን ወንድሞቼ ሆይ ከእንግዲህ ወዲህ 16ቱን ሕግጋት/10ሩ የኦሪት ሕግጋት ዘፀ. 20:1 እና 6ቱን የአዲስ ኪዳን ህግጋት ማቴ.5:21-48/ ለመፈፀምና የእግዚአብሔር ባሮች መሆንን አንፈልግ/ ይልቁንም የማርያም ባሮች ለመሆን ፈጽመን እንሽቀዳደም ብዬ እነግራችኋለሁ"*[153]

በማለት የእግዚአብሔርን ቃል በመተላለፍና በማርያም ኪዳን ከእግዚአብሔር የዘላለም ቁጣ ማምለጥ እንደሚቻል ተስፋ ይሰጣል፡፡ የእግዚአብሔርን ቃል ጥላችሁ እኔን ለመታዘዝ ተሽቀዳደሙ የምትል የኢየሱስ ክርስቶስ እናት የሆነች ማርያም በፍጹም ልትሆን አትችልም፡፡ ማርያምን ለመታዘዝ የእግዚአብሔርን ቃል የግድ መጣስ አለብን ወይ? ይህ አደገኛ የኑፋቄ ትምህርት ነው፡፡ መጋቤ ጥበቤ ሰሎሞን በመጽሐፋ በዚህ ጥቅስ ላይ ተሞርኩዞ ሲናገሩ፡-

> *እንግዲህ ይህ በመቃብር ተገኘ የተባለው ቃል ኪዳን የኃጢአት ተባባሪ ከሆነና ማርያም ይህ ሁኔታ ስለባሕሪዋ ተስማሚ ሆኖላት ከተባበረች እንዲሁም እግዚአብሔር ሕጉንና በኃጢአት ላይ የሚያወርደውን ቁጣ ከተወው መንግሥተ ሰማያትም የአመፀኞችና የብልጣብልጦች መኖሪያ ሆነች ምን ዓይነት ማርያም፤ ምን ዓይነት ቅዱስ እግዚአብሔር፤ ምን ዓይነትስ የምትናፍቅ መንግሥተ ሰማያት ልትሆን ትችላለች?*[154]
> ብለዋል፡፡

*መጽሐፍ ቅዱስ "አትሳቱ እግዚአብሔር አይዘበትበትም፡፡ ሰው የሚዘራን ሁሉ ያንኑ ደግሞ ያጭዳል፡፡ በገዛው ሥጋው የሚዘራ በሥጋ መበስበስን ያጭዳል" (ገላ.6:7-9)* ይላል፡፡ *"እመቤታችንን አናመልካትም፤ አዳኝችንም አንላትም"*[155] የሚለው ነገረ ሃይማኖት(ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ) መጽሐፍና ከላይ በተአምረ ማርያም የተዘረዘሩ አሳቦች እርስ በርሳቸው አይጣረሱም ወይ? ከሁለቱ መጻሕፍት አሳቦች የቤተ ክርስቲያኒቷን የእምነት አቋም የሚገልጠው የትኛው ነው? የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የእምነት አቋሟን የማይገልጡ የእርሷ ያልሆኑ አሳቦችን አስተምህሮዎችን እንደእሷ አስተምህሮ ተደርገው የሚሠራጩትን የእርሷ አስተምህሮ እንዳልሆኑ ካላሳወቀች ስለ አንድ ነገር እርስ በርስ የሚቃረኑ አሳባች ከአንድ አካባቢ እየወጡ ያሉ ይመስላሉ፡፡ ይህ ተሐድሶ አያስፈልገውም ወይ? ከላይ ከተአምረ ማርያም የተጠቀሱ ክፍሎች ማርያምን ሙሉ በሙሉ በኢየሱስ ምትክ ያስቀምጣሉ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ይህን በፍጹም አያስተምርም፡፡ ይህ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ሙሉ በሙሉ የሚጋጭ፣ ነቢያት፣ ሐዋርያትና

[153] የኢ.ኦ.ተ ቤ/ክ፣ *ተአምረ ማርያም*፣ 3ኛ እትም፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤተ አዲስ አበባ፤ 1989 ዓ.ም ገጽ 47
[154] ጥበቤ ሰሎሞን (መጋቤ)፣ *በውኑ በማርያም ማመን ይገባሃልን?* አዲስ አበባ 2000 ዓ.ም ገጽ 147
[155] *ሳሙኤል ፈቃዱ (2003 ዓ.ም)፤ነገረ ሃይማኖት (ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ)፤ ገጽ 207*

# የመጽሐፍ ቅዱስ ምንነት

በአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ የተሰኘው ይህ ምትክ የለሽና ድንቅ መጽሐፍ በግሪክኛ *"ባይብሉስ"* በሚል ይታወቃል:: የእንግሊዝኛ ተናጋሪዎችም *"ዘ-ባይቢል"* የሚል ስያሜ የሰጡት ለዚህ ነው:: የነገረ መለኮት ሊቅ የነበሩ ዶክተር ሉውስ ስፔር ቼፈር የመጽሐፍ ቅዱስ ልዩ መሆን ሲናገሩ:- *"አስገራሚ ተያያዥነት ያላቸው 66 መጻሕፍት በአንድ ላይ መያዙና የተጻፈው ቃል ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ለመጻፉ ቋሚ ማስረጃ መኖሩ ነው"*[160] ብለዋል:: በመጽሐፍ ቅዱስ ከዘፍጥረት እስከ ራእይ ኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ልጆች ብቸኛ አዳኝ ሆኖ ቀርቧል(ሐዋ.4:12)::

መጽሐፍ ቅዱስ የቤተ ክርስቲያን መሠረት ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ የቤተ ክርስቲያን መመሪያና ውስጠ ደንቧ ነው:: የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል የማይለወጥ (ማቴ.5:17-18)፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በሥልጣን የሚያደርግ (ኢሳ.55:11)፣ ልብን ሁሉ የሚመረምር (ዕብ.4:12)፣ የሚፈውስ (መዝ.107:20)፣ የሚቀድስ (ዮሐ.17:17) ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ እስትንፋስ እግዚአብሔር እንዳለበት በነቢያት፣ በሐዋርያት፣ በቤተ ክርስቲያን አበውና በነገረ መለኮታውያን የተረጋገጠና የካኖን መመዘኛ ያለፉት 66 መጻሕፍትን በአንድነት አቅፎ የያዘ መለኮታዊ ቤተ መጻሕፍት ነው::

# የአማርኛና የኦሮምኛ መጽሐፍ ቅዱስ አጭር ታሪክ

በአገራችን ቅዱስ መጽሐፍ ለመጀመሪያ ጊዜ በ4ኛው ክፍለ ዘመን በፍሬምናጦስ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ቀጥሎም በ5ኛው ምእተ ዓመት በዘጠኙ ቅዱሳን በግሪክኛ ከተዘጋጀው ከሰባ ሊቃናት ወደ ግዕዝ ተተርጉሞአል:: የሕዝብና የቤተ ክርስቲያን መገልገያ በነበረው የግዕዝ ቋንቋ የተዘጋጀው መጽሐፍ ቅዱስ እየተነበበና እየተብራራ እስከ 17ኛው ክፍለ ዘመን ቆይቶአል:: እንደ እነ ፒተር ሄይሊንግ አንዳንድ ሚሲዮናውያን በ17ኛው ክፍለ ዘመን ለመጀመሪያ ጊዜ አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን ወደ አማርኛ ለመተርጐም ያደረጉት ጥረት በታሪክ አይዘነጋም:: ሥራቸው ለአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም በር ከፋች ሆኗል::

የፈረንሣይ ኤምባሲ ምክትል ቆንስላ በነበረው አስሊን ዕርዳታ *"አባ አብርሃም"*[161] ሙሉ መጽሐፍ ቅዱስን በግብፅ ለአሥር ዓመት ቁጭ ብለው ወደ አማርኛ የተረጐሙት ኢትዮጵያዊ ሲሆኑ እርሳቸው በመጋቢት በ1811 ዓ.ም ከሞቱ በኋላ የተረጐሙት ሙሉ መጽሐፍ ቅዱስ በአማርኛ በ1832 ዓ.ም በለንደን ታተመ:: የተሻሻለ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በ1923 ዓ.ም ትዕዛዝ ተሰጥቶ በኢትዮጵያ ሊቃውንት ብቻ ከግዕዝ ወደ አማርኛ የተተረጐመ መጽሐፍ ቅዱስ ከ1928-1934 ዓ.ም ታተመ:: እንደገናም በየካቲት 27 ቀን 1939 ዓ.ም ሰባት ኢትዮጵያውያንና ሦስት የውጭ አገር ሊቃውንት ያሉበት ጉባኤ በንጉሡ ትዕዛዝ ተሰይሞ አባ አብርሃም የተረጎሙትን መጽሐፍ ቅዱስ ከዕብራይስጥና ከፅርዕ ጋር በማነጻጸር የተሻሻለ ትርጉም በ1944 ዓ.ም ታተመ::[162] ይኸው ትርጉም በ1953 ዓ.ም በአገራችን በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት 66 መጻሕፍት የያዘው መጽሐፍ ቅዱስ ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስን ጨምሮ በኦርቶዶክስ ሊቃውንት ብርቱ ጥንቃቄ ተተርጉሞ እንደተዘጋጀ ይታወቃል:: ይህ የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ለሁሉም የኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት መንፈሳዊ ሃብትና መመሪያ ሆኖ ሲያገለግል ቆይቷል::

ሌላው ታላቁ ባለራእይና የኦሮምኛ መጽሐፍ ቅዱስ የተረጐሙት የተከበሩ ቄስ አናሲሞስ ነሲብ (አባ ጋማቺስ) ሲሆኑ አስቴር ገኖ የቅርብ ረዳታቸው ነበረች:: ስዊድናውያን የቅርብ አማካሪዎቻቸው የነበሩ ሲሆን በ1886 ዓ.ም የኦሮምኛ አዲስ ኪዳን ታትሞአል:: በ1891 ዓ.ም ሙሉው የኦሮምኛ መጽሐፍ ቅዱስ ታትሞአል:: የአባ ጋማቺስ ታላቅና ፋና ወጊ ሥራ የኦሮምኛ ሥነ ጽሑፍ በር ከፋችና መሠረት እንደሆነ በብዙዎች ይጠቀሳል:: ይህም በብዙዎቻችን እጅ የሚገኙና በአገራችን ቀድመው የታተሙ የአማርኛና የኦሮምኛ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች እንድናገኝ ያደረጉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን፣ በግብፅ የፈረንሣይ ቆንስላ የነበሩ አስሊን፣ አባ አብርሃም፣ የኦርቶዶክስ ሊቃውንቶች፣ ንጉሥ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ፣ አባ ጋማቺስ፣ አስቴር ገኖና የስዊድን አማካሪዎች ትልቅ ምስጋና ልንቸራቸው የሚገባ የኢትዮጵያ ባለውለታዎች ናቸው:: ከላይ በተጠቀሱት ሰዎች የተተረጐመው መጽሐፍ ቅዱስ 66 መጻሕፍት የያዘ እንደነበር መዘንጋት የለበትም:: አሁን ግን የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የመጽሐፍ ቅዱሷን ከ66 መጻሕፍት ወደ 81 አሳድጋለች::*"ለመሆኑ ይህን 1953 ዓ.ም የታተመ መጽሐፍ ቅዱስ መለወጥ ለምን አስፈለገ? ያዘጋጁትስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳውያን አባቶች በቂ መንፈሳዊ ዕውቀትና መልካም ሕይወት አልነበራቸውምን? ከግማሽ ምዕተ ዓመት በላይ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን ሲገለገሉበት የኖሩት መጽሐፍ ቅዱስ የተሳሳተ ነበርን?"*[163]

# ስደት የጠገበ መጽሐፍ

በዓለማችን በነገሥታት፣ በህቡዕ የክህደት ርዕዮተዓለም፣ በ"ክርስቲያኖች" በሰይጣን በ"ቤተ ክርስቲያን" ወዘተ... ትልቅ የተቃውሞ፣ የእገዳ፣ የውግዘት፣ የማጥፋትና የማቃጠል አዋጆችን ሁሉ አልፎ በብዛት

[160] ተክሉ መንገሻ(ተርጓሚ) *(2003 ዓ.ም)* ፤ *የመጽሐፍ ቅዱስ ዋና ዋና ጭብጦች*፣ አዲስ አበባ የላፕሲሲ ብሩክስ ፋውንደሽን፣ ገጽ 19

[161] *ጉስታቭ አሬን፣ ቀደምት ወንጌላውያን በኢትዮጵያ፣ ገጽ 42-44* በሚለው መጽሐፋቸው ስለ አባ አብርሃም ሲናገሩ:- "አባ አብርሃም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ካህን የሆኑ መነኩሴ ነበሩ:: ምድረ ሙላዳቸውም ጐጃም ገልጸዋል:: አባ አብርሃም በዐረብኛው አጠራር:- *"አቡሂም፣ አቡሩሀ፣ አቢሩሚ"* እየተባሉ ይጠሩ ነበር:: ሁሉም አብርሃም ማለት ነው::"



[162] ሞገስ ብርሃን፣ ጥር 2006 ዓ.ም ገጽ 13-23 *"የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ሐምሌ 18 እና 19 ባዘጋጀው ሲምፖዚየም ላይ በምሥራች አገልግሎት ሥራ መሪ ከቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ የተወሰደ"*

[163] በንስሐ የመታደስ አገልግሎት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን፣(2002 ዓ.ም)፤ አዲስ አበባ፣ ገጽ 60

በመታተምና በመሰራጨት ቅድሚያ የያዘ አንድ መጽሐፍ ቢኖር እርሱም መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ለምሳሌ፡- በ305ዓ.ም የተነሣው ዲዮቅልጥያኖስ አብያተ ክርስቲያናት ይዘጉ፣ አብያተ ጣኦታት ይከፈቱ በማለት ሲያውጅ በጊዜው የተገኙ መጽሐፍ ቅዱሶች እንዲቃጠሉ ካደረገ በኋላ በተቃጠለው ቅዱስ መጻሕፍት አመድ ላይ ቆሞ ፎክሮዋል። በአገራችን ኢትዮጵያ ለእግዚአብሔር እንደቀኑ የሚነገርላቸው በዐፄ ዮሐንስ የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ተሰብስቦ እንዲቃጠል አዋጅ አውጥተው እንደነበር ድርሳናት ያወሳሉ። አባ ጋማቺስ በኦሮምኛ የተረጎሙትን መጽሐፍ ቅዱስ ለሕዝብ እንዳይሰራጭ ከአንዳንድ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ትልቅ ተቃውሞና እገዳ እንደደረሰበት ታሪክ ሕያው ምስክር ነው። በደርግ ዘመን የአብዮቱ ካድሬዎች በተለይ የወንጌላውያንን አብያተ ክርስቲያናት የመዝጋትና መዝረፍ፣ መሪዎችን ማሰር፣ ቅዱሳንን ማሳደድና መጽሐፍ ቅዱስን ሰብስቦ ማቃጠል እንደ ትልቅ ጀብዱ ይቆጥሩ እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው።

በርናርድ ራም የተባለ ሰው በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ስለደረሰው ሲናገር፡- *"ሺህ ጊዜ መጽሐፉ እንደሞተ ተለፍፏል፣ የቀብር ሥነ ሥርዓቱ ተካሂዷል፣ መቃብሩ ላይ ማስታወሻ ተጽፏል የሕይወት ታሪኩ ተነቧል ዳሩ ግን ሬሳው ጉድጓድ ውስጥ ቆይቶ አያውቅም"* በማለት በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የደረሰውን ታላቅ ጫናና ብርቱ ድል ለመግለጽ ጥረት አድርጓል። በታሪክ ለመጽሐፍ ቅዱስ ሕልውናና መልዕክት ብርቱ አደጋ ሆና የዘለቀችው በእንደቤቷ ቃሉን በልቧ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ የሰው ፍልስፍናና ድርሳናትን የምታራምድ "ቤተ ክርስቲያን" እንደ ሆነች ይጠቀሳል።

መጋቤ ሰሎሞን ጥበብ ስለዚህ ሲናገር፡-

> *...መጽሐፍ ቅዱስ በስሙ ተመስርቻለሁ የምትለው ቤተ ክርስቲያን ሳትቀር ገፍታዋለች። በአደባባይ አቃጥላው ታውቃለች። በዛሬ ዘመን እንኳ ሳይቀር መጽሐፍ ቅዱስን በማንበባቸውና የሕይወታቸው መመሪያ ያደረጉትንና በእውነት የሰበኩትን ሰዎች ታሳድዳለች አሳዳለችም። ከማህበራዊ ሕይወታቸው እንዲገለሉ የተፈረደባቸው ታሪክና ቤቱ ይቁጠራቸው።አንዳንዶች መጽሐፍ ቅዱስን ይዘው ኢመጽሐፍ ቅዱስን የሚሰብኩ የተባለውን ትተው ያልተባለውን፣ በልባቸው የቋጠሩትን ሲወርድና ሲዋረድ የመጣላቸውን ሲያስኛቸው የሚመስለውን ካላስኬደም ትውፊት ከሚል ዋሻ አልያም ደግሞ ከባሕልና ከምድር ከሚያያቸው በዕድሜ የገፉ በሥልጣን የላቁ ጊዜ የገጠማቸውን የሰዎችን ተረትና አባባል እየጠቃቀሱ መጽሐፍ ቅዱስን ይቃወማሉ* [164]

"የንስሐ የመታደስ አገልግሎት" መጽሐፍ አዘጋጅ፡-

> *በቤተ ክርስቲያናችን መጽሐፍ ቅዱስ ተገቢውን ክብር ያላገኘ እንደሆነ በግልጽ ይታያል። የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት የሚጻረሩ የፍጡራን ድርሰቶች በየዐውድ ምሕረቱ ይነበባሉ፤ ይሰበካሉ። በአንዳንድ ክብረ በዓሎችም አንዳንድ ሰባኪዎች መጽሐፍ ቅዱስን የሚቃረኑ ተረቶቻቸውን በስብከት ስም ያለ ምንም ከልካይ ይለፍፋሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ምን እንደሆነ የማያውቁ ካህናት ጥቂት አይደሉም*[165] ብሏል።

[164] ጥበብ ሰሎሞን(መጋቤ)፣ 2000 ዓ.ም (መግቢያ) ገጽ 10

[165] *የንስሐ የመታደስ አገልግሎት፣ 2003 ዓ.ም*





## "ሰማንያ አሐዱ- በቃሉ ሲመዘን"

ቴዎድሮስ ደመላሽ *"ሰማንያ አሐዱ በእግዚአብሔር ቃል ሲመዘን"* በሚል ርዕስ በጻፉት መጽሐፍ መግቢያ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የታተመ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጽሐፍ ቅዱስን መቅድም ዋቢ በማድረግ በቤተ ክርስቲያናቸው ስላለው የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት ቁጥር እንዲህ ብሏል፡-

> *የመጽሐፍ ቅዱስን ቁጥር በተመለከተ አብዛኛው ዓለም የእግዚአብሔር ቃል ብሎ 66 መጻሕፍትን ይዞ ሲገኝ የእኛ ቤተ ክርስቲያን ግን 81 መጻሕፍትን ይዛለች፤ ቅዱሳት መጻሕፍትም 81 እንደሆኑ ታስተምራለች።*[166]

ቴዎድሮስ በ66ቱ መጻሕፍት ላይ የተጨመሩ 15 መጻሕፍት ከቃሉ ጋር ሰፊ ሚዘና ካደረገ በኋላ በመጽሐፉ ማጠቃለያ ሲሰጥ፡-

> *ቅዱሳት የምንላቸው መጻሕፍቶቻችን ሆኑ አስተምህሮዎቻችን እንደ ቅዱስ መጽሐፍ ካልሆኑ የተሰጣቸው የቅድስና ስም ቅዱስ ሊያደርጋቸው አይችልም። ቤተ ክርስቲያናችን "ቅዱሳት" እና የእኔ ብላ የያዘቻቸውና ምእመናንንም የእናንተ ነው ልትላቸው እየሞከረች ያለውን የመጽሐፍ ቅዱሷን ቅዱስነት ብትፈትሸው ከእምነቷ ጋር ፈጽሞ የማይጣጣም መሆኑን መመልከት በቻለች ነበር። እምነታችን ወንጌልን ያማከለ ነው፤ አስተምሯችንም ከሐዋርያት የወረስነው ነው እየተባለ የወንጌልን እውነት የሚፃረርና የሐዋርያትን ትምህርት የሚቃወም ኑፋቄ ትምህርት ይዞ መገኘቱ ለምን ይሆን? እንደ እውነቱ ከሆነ በዚህች መጽሐፍ ለመመርመር እንደ ተሞከረው በተጨማሪዎቹ መጻሕፍት ውስጥ የሚገኙ ፀረ ወንጌልና ፀረ ክርስትና ምክሮችን የያዘው መጽሐፍ የእኛ ሊሆን በፍጹም አይገባውም።* [167]... ካሉ በኋላ *"እስካሁን ከተመለከትነው አንጻር "መጽሐፋችን 66 ሳይሆን 81 ነው" ማለቱ ብዙ የሚያዋጣ አይደለም።* በማለት የጥናታቸውን ውጤት ደምድመዋል።

## "ገመና ዘ፹፩ዱ"

ቀሲስ ደረጀ ገ. *"ገመና ዘ፹፩ዱ"* በሚለው መጽሐፉ ስለ ሰማንያ አንዱ የኢትዮጵያ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስ፡- *በ1980 ዓ.ም ለኦርቶዶክስ የታተመው 81ዱ መጽሐፍ ከ1954/62/ ዓ.ም ከታተመው 66ቱ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ አሳቦችን በመቆራረጥ በሃይማኖታዊ ቃልና ሀረግ ፍቶ በመተካት ከፍተኛ የሆነ የማጭበርበር /foreign/ ሥራ ተሠርቶበታል። እንዲህም ሆኖ ያልረኩት ደብተሮች በ2ሺ ዓ.ም ብሉይ ኪዳኑን ከእናት ቋንቋው ከዕብራይስጥ፤ አዲስ ኪዳኑን ከግሪኩ በሚቃረን መልኩ የእግዚአብሔርን ቃል ሰርዘውና ደልዘው*

[166] ቴዎድሮስ ደመላሽ *(2004 ዓ.ም)፣ ሰማንያ አሐዱ በእግዚአብሔር ቃል ሲመዘን፣*አዲስ አበባ፣ ገጽ 11

[167] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 135

የዚያን ጊዜ የነገረ መለኮት ተማሪዎች የነበሩ ዛሬ ብዙዎቹ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንደሆኑ አንዘንጋ:: ዘራቸውን ከክርስትናቸው በላይ የሚመለከቱ የትላንት ተማሪዎች የዛሬ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከሁሉ በላይ የሆነውን ክርስቶስን እንዴት መስበክ ይችላሉ? ክርስትናችን ከቋንቋችንና ከብሔራችን አልፈን እንድናይ ካላደረገን ዋጋ የለውም:: ሌላው ይህ አብያተ ክርስቲያናትን በብዙ ያሽመደመደው አደገኛ የጠባብ ብሔርተኝነት መንፈስ ወደ ወንጌላውያን የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችም በከፍተኛ ሁኔታ እየተዛመተ መሆኑን ነው:: ተማሪዎች ባለራእዮች ሆነው ለቤተ ክርስቲያንና ለአገር ጠቃሚ እንዲሆኑና የጊዜውን የእግዚአብሔርን አሳብ ተረድተው አዲስ የታሪክ ምዕራፍ እንድከፍቱ ሳይሆን ወደ ጎጣዊ የአመለካከት ዋሻ ለማስገባት በመንፈሳዊ አገልግሎት ስም የሚታገሉ ግለሰቦችና የተደራጁ *"መንፈሳዊ ድርጅቶች"* ብዙ ናቸው:: እያንዳንዱ ቤተ እምነት የራሱን ተማሪ ተከታትሎ የማገልገል ትጋታቸውን ባደንቅም የብዙዎቹ እርምጃ ከተለያየ ቤተ እምነት፣ ባሕል፣ አካባቢ፣ ቋንቋና ልምድ የመጡና ለቤተ ክርስቲያን፣ ለአገርና ለዓለም የለውጥና የዕድገት ኃይል የሆኑትን በቃሉ ከማስታጠቅና ታላላቅ ባለራእዮች እንዲሆኑ ከማሳደግ ይልቅ በቤተ እምነታዊ ብሔርተኝነትና በቋንቋ በመበታተን አንድነትንና ፍቅርን ጥያቄ ውስጥ ማስገባት በየትኛውም ሚዛን መንፈሳዊነት አይደለም:: በዚህ አካሄድ ከራሱ ይልቅ የሚኖርለት ትልቅ የመኖር ዓላማ ያለው ትውልድ እንዳይነሳ እንቅፋት መሆናችንን ያመለክታል:: ለራሱ ተሰናክሎ ትውልድን ለሚያሰናክል ለዚያ ሰው ወዮለት!!

በየአጥቢያዎቻችን ሠርቶ ልዩነትን ያላመጠው የአገልግሎት ዘይቤያችን የራስን ስም ለማስጠበቅና የተማሪዎችን መንፈሳዊ ዕድገት ከማቀጨጭ ውጭ ልዩ ተአምር ያመጣል ብዬ አልጠብቅም:: ለዚህ ሁሉ ተሐድሶ ያስፈልጋል:: ይህን ክፍል ስጽፍ ወደ አንድ ዩኒቨርሲት ለአገልግሎት ተጋብዤ ሄጀ ነበር:: ከ2000 በላይ የዩኒቨርሲቲ ክርስቲያን ተማሪዎች ሕብረት መሪ ሆኖ የሚያገለግል ወጣት ምሳ አብረን እየበላን ሳለ በጣም እያዘነ ፍርሃቱን እንዲህ ብሎ ተናገረ:-

> *የዩኒቨርሲት ክርስቲያን ተማሪዎች ሕብረት የመበታተን ትልቅ አደጋ ተጋርጦበታል:: አደጋውን ያመጡት ለእኛ የሚያስቡና የማገልገል ሸክምና ልብ እንዳላቸው የሚናገሩና የአብያተ ክርስቲያን እውቅናም የተሰጣቸው ቢሆኑም ትልቁ ችግራቸው ዘመኑን፣ ትውልዱን፣ የእግዚአብሔርን የጊዜው አጀንዳ ያልተረዱና ጠባብነት ጎልቶ የሚታይባቸው መሆናቸው ነው:: እነዚህ አካላት የተለያየ ስም እየሰጡን እኛን በተለያየ ስም በታትነው የባለቤትነትን ሰሌዳ በእኛ ላይ በመለጠፍ ስማቸውን ከማስጠራት ያለፈ ለቤተ ክርስቲያን፣ ለተማሪዎች ለአሁኑና መጻኢ ሕይወት አልፎም ለእግዚአብሔር መንግሥት ምንም እዚህ ግባ የሚባል ራእይ እንደሌላቸው የታወቀ ነው:: ብሏል::*





ጳውሎስ ፈቃዱ በቤተ ክርስቲያን ስለ ተንሰራፋው የዘር አባዜ ሲናገር:-

> *ወንዛዊነት ሥር ሰዶ፣ ክልልተኝነት ተንሰራፍቶ፣ ዘረኝነታቸውን በክርስትና ጭንብል የሸፈኑ ሰዎች ስለ በዙ በእግዚአብሔር ቤት ሁሉም የራሱን ሰውና የራሱን ጎጥ ብቻ ለይቶ ለመጥቀም፣ ቋንቋውን ለማግነን ይውተረተራል:: ጌታ ኢየሱስ ሲመጣ ምን ይለን ይሆን?*[189] በማለት ሃሳቡን በጥያቄ ደምድሟል::

በዚህ በ21ኛው ክፍለ ዘመን ዓለም ***"ኢትዮጵያውያን ወንጌልን ይዘው ወደ እኛ ይመጣሉ"*** ብላ እየጠበቀችና እግዚአብሔርም የመጨረሻው ዘመን የመንግሥቱ ዘሮች አድርጎ ሊያስነሣን በፈለገበት በዚህ ወሳኝ ጊዜ ላይ ጎሰኝነትና መንደርተኝነት መንፈሳዊነትን ተላብሰው ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን ያንበረከኩ ቢመስልም እግዚአብሔር ለትውልዱ ያለውን ትልቅ ራእይ ለማፍረስ ጠላት የዘራው ዘር እንደሆነ አንስትም:: ይህን እኩይ መንፈስ የሚያፈራርሱ የተሐድሶ አገልጋዮች በተለይ በኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት መካከል ነበሩ አሁንም በብዛት በልዩ ኃይልና ቅባት ይነሣሉ::

ጠባብነትንና ጎሰኝነትን በቃሉ ላይ ቆመን በገሃድ ካልተቃወመን ውጤቱ ለማንም መልካም አይሆንም:: ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ እኛ ወደ አባቱ ሲጸልይ:- *"እኛም አንድ እንደ ሆንን አንድ ይሆኑ ዘንድ"* (ዮሐ. 17:22) ሲል ታላቁ ሐዋርያ ጳውሎስም የቅዱሳን አንድነት ሲገልጽ:- *"አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም፣ ባሪያ ወይም ጨዋ ሰው የለም፣ ወንድም ሴትም የለም ሁላችሁም በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ አንድ ሰው ናችሁና"* (ገላ.3:29) በማለት ዘመን ዘለቅ እውነት ነግሮናል:: በጌታ ሙሉ ወንጌል፣ መካነ ኢየሱስ፣ ቃለ ሕይወት፣ ሕይወተ ብርሃን፣ 7000 ምርጦች፣...ፕሮቴስታንት፣ ኦርቶዶክስ፣ ካቶሊክ እንደሌሉ ሁሉ እንዲሁም አማራ፣ ኦሮሞ፣ ትግሬ፣ ካንባታ፣ ሃድያ፣ ወላይታ፣ ሱማሌ፣ ሱርሜ፣ ቦረና፣ ቡርጂ፣ ጋብራ፣ ጋሪ ...ወዘተ የለም! ሁሉም በእርሱ አንድ ናቸው:: ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካል ከሆነች ክርስቶስ አንድ እንጂ ብዙ አካሎች የለውም::

ትልቁ ችግራችን ብሔርና ቋንቋ ሳይሆን ብሔርን፣ ቋንቋንና ባሕልን ሽፋን በማድረግ ቅምና በቀልን የተሞላ ልባችን ነው:: ልባችን ለወንጌል እውነት ካልተንበረከከ መዝሙር፣ ስብከታችንና የአገልግሎት ግርግር ሰይጣን እየደገሰልን ካለው የጥፋት አጀንዳ ከሌላ ልሆኑን በፍጹም አይችሉም:: እግዚአብሔር ልባችንን በቃሉና በመንፈሱ ይለውጥ! የእግዚአብሔር መንግሥት ከጎሳ፣ ከቋንቋ፣ ከባሕል፣ ከተለያየ አካባቢ፣ የኑሮ ዘይቤና ንጽሮተ ዓለም ተጠርተን ለጠራን ጌታ የሚንኖርበት ግዛት እንጂ ሁላችንም የቋንቋችንና የባሕላችንን የበላይነትም ሆነ የበታችነት የሚንሰብክበት ቦታ አይደለም:: ቋንቋ፣ ብሔር፣ ባሕል፣ መልካም ልምድና

[189] ጳውሎስ ፈቃዱ (2004 ዓ.ም)፣ *የብርሃን አንጓዎች*፣ ርኆቦት አታሚዎች፣ ገጽ 189

እሴቶቻችን ለዚህ ሕይወት አስፈላጊና ጠቃሚ ሲሆኑ ወንጌል ለዚህ ሕይወትና ለዘላለሙም የበላይና ብቸኛ ተስፋችን ነው:: ይህ እውነት በአማኞች ልብ ሁሉ አሸናፍ ይሆን ዘንድ ተሐድሶ ያስፈልገናል:: የኢትዮጵያ ክርስትና በብሔር ጉዳይ እጅግ ግራ እንደተጋባ ፕሮፌሰር መስፍን አስተውሎታቸውን ሲያስቀምጡ:-

*ክርስትናም በጎሰኝነት እየታመሰ የኢትዮጵያዊነት የክብር ልብሱ እየተቀደደበት ነው፤ እስካሁን ድረስ ጎሰኝነትን ተጋፍጦ በቆራጥነት የተቋቋመው እስልምና ብቻ ነው*[190] ብለዋል:: ለዓለም ጨውና ብርሃን መሆን ያለመቻል ብቻ ሳይሆን ጥላቻን ያለመቀባበልንና ጠባብነትን ማስፋፋታችን እጅግ ያሳዝናል:: ለዚህ ተሐድሶ አያስፈልግም ወይ?

## የነቀዘ አሠራር ዋሻ

ዶክተር ሳምሶን እስጢፋኖስ በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት አሠራር ላይ ባደረጉት ጥናት ላይ:- *"የቀድሞው አሠራር የአሁኑን አሠራር ሊሸከመው አልቻለም፣ ሊፈነዳ ደርሷል"*[191] ካሉ በኋላ፣ በጥናታቸው በኢትዮጵያ ባሉት በ60 የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ላይ የታየውን አሳዛኝ ሁኔታ ሲጠቅሱ:-

*በ60 አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ በሚሊዮን የሚቆጠር የገንዘብ ምዝበራ አይቻለሁ፣ እርስ በርስ እስከ መታከስ የደረሱ አሉ፣ ከሽብርተኞች ጋር የተባበሩና የተደበቁ ሁሉ ተገኝተዋል:: በእኛ ስም ኃጢአት ብቻ ሳይሆን፣ ወንጀል ሁሉ ተሠርቷል:: የወንበዴዎች መደበቂያ ሆነናል*[192] ያሉት ያስደነግጣል::

ዶ/ር ልደቱ ዓለሙ ከፈኔ፣ አንድ የመንግሥትን ባለሥልጣን ንግግር ዋቢ በማድረግ፣ በአንድ አውደ ጥናት ላይ ባቀረቡት ጽሑፍ :-

*እናንተ ቤት መጽሐፍ ቅዱሳችሁ የሰላም መጽሐፍ ነው:: ነገር ግን ሰላምን ያጠፋው ነገር ምንድነው?*[193] ይህን እንዲሉ ያደረጋቸውን ምክንያት ሲገልጹ:- *"እስካሁን ድረስ 3 የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሆነ አቤቱታ ቀርቦልናል፣ 4 ከሙስሊም ቀርቦልናል፣ 245 ከወንጌላውያን ቀርቦልናል::*[194]

ያሉት ያለንበትን አደገኛ ሁኔታና የቆምንበትን መስቀለኛ መንገድ ያመለክታል:: ይህም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ተሐድሶ ለኢትዮጵያ ወንጌላውያን ቤተ ክርስቲያናት በእርግጥ አስፈላጊ መሆኑን ያሳያል:: በአጠቃላይ በዓለም አቀፍ ደረጃ

[190] መስፍን ወልደ ማርያም (2002 ዓ.ም)፣ አገቱኒ ተምረን ወጣን፣ አዲስ አበባ ገጽ 129
[191] ማቴቴስ ግንቦት 2003 ዓ.ም
[192] ዝኒ ከማሁ፣
[193] ልደቱ ዓለሙ ከፈኔ (ዶ/ር) (መጋቢት 2004 ዓ.ም) ፣ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የአመራር ገጽታ: ከመሪነት ጋር የተያያዙ ችግሮችና ሎሌያዊ አመራር የሚሰጠው መፍትሔ፣ በቤተር ላይፍ ሚኒስትሪ በተዘጋጀ ዓውደ ጥናት ለውይይት የቀረበ፣ አዲስ አበባ ፣ ገጽ 9
[194] ዝኒ ከማሁ፣9





የክርስቶስ አካል በሆነችው ቤተ ክርስቲያን እንደ ወረርሽኝ የተንሰራፋው ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮና ልምምድ የተሐድሶ አስፈላጊነትን ያመለክታሉ:: ቤተ ክርስቲያን የኢየሱስ ክርስቶስ አካል እንደመሆኗ መጠን የሚያድሳት እርሱ ራሱ ነው:: እርሱም ሕያው በሆነው ቃሉና በመንፈሱ አካሉን በማደስ በዚህ መጨረሻ ዘመን ላይ የመንግሥቱን ወንጌል በኃይል እንድትሰብክ ያደርጋታል:: ትልቁ ጥያቄ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን ያድሳል ወይ? ሳይሆን፣ ቤተ ክርስቲያን ለመታደስ ትፈቅዳለች ወይ? መሆን አለበት::

## "ተሐድሶ ለቤተ ክርስቲያን አያስፈልጋትም"

ዲያቆን እሱባለው በየነ (ናትናኤል) *"የሚለወጥ ዓለም የማይለወጥ አምላክ ተሐድሶ ለማን?"* በሚል ርዕስ ባሳተመው *መጽሐፍ፣ ተሐድሶ የሚለውን ሐሳብ ማርቲን ሉተር እንደ ጀመረና ያነሣቸው ጥያቄዎች በወቅቱ ተገቢና አሳማኝ ሲሆኑ፣ በመጨረሻ ግን የተነሣበት ግብ በመተው ስሕተት ውስጥ መዘፈቁን፤*[195] እርሱና *ተከታዮቹ (ፕሮቴስታንት) መታረምን እንቢ ብለው ስለነጎዱ በኦርቶዶክስ መናፍቅ የሚል ስም እንደተሰጣቸው*[196] ገልጸዋል:: መሪራስ አማንም *ደግሞ ሉተርና ፈለጉን የተከተሉ ክድነት መንገድ እንደጠፉ ግምቱን ሲናገር:- ሉተርና የሉተር መንፈስ የተሰራጨባቸው ቅዱሳንና ጻድቃንን ሲቃወሙ ስማቸውም እንዳይነሣ ይሰብካሉ ምክንያቱም ለቅዱሳን የተሰጠው ጸጋ በእነርሱ ላይ የለምና ከቅዱሳንና ከጻድቃን ጋር የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመውረስ አልታደሉምና*[197] *ብሏል::*

መሪራስ እንዳሉ ሉተር የተቃወመው ቅዱሳንና ጻድቃንን ሳይሆን የእግዚአብሔርን ቃል የጋረዱ፣ ትውፊት፣ ድርሳናት የጳጳሳት ገደብ የለሽ ሥልጣንና ልቅ የአኗኗር ዘይቤ እንደ ነበር መዛግብት ያወሳሉ:: ዛሬ የሉተርን ፈለግ የሚከተሉ አብያተ ክርስቲያናት ሐዋርያት የሰበኩትን ወንጌል እንጂ የቅዱሳንና ጻድቃን ስሞች አይሰብኩም:: በዓላትን በስማቸው አያከብሩም፤ በስማቸውም ድግስ አይደግሱም፤ እንዲያማልዱላቸውም ልመናቸውን ወደ እነርሱ አያቀርቡም:: ይህን የማያደርጉበት ምክንያት ቅዱሳንና ጻድቃንን ስለሚጠሉና ስለማያከብሩ ሳይሆን መጽሐፍ ቅዱስ እንደዚያ እንዲያደርጉ ስለማያዛቸው ነው:: በወንጌል እውነት የዳነ ሁሉ የቅዱሳንን የሕይወት ምሳሌነት መከተል፣ በመልካም ሥራቸው እነርሱን መምሰል፣ እነርሱ ለጌታና ለወንጌል እንደኖሩ መኖር ይገባቸዋል:: ይህን ሁሉ የሚያደርጉት በእነርሱ ላይ ያለው ጸጋ እንዲያድናቸው ሳይሆን እነርሱ ባመኑት ጌታ ጸጋ አምነው ከዘላለም ሞትና ኩነኔ ስለዳኑ ነው::

[195] ዲ/ን እሱባለው በየነ(ናትናኤል)፣(2004 ዓ.ም)፣የሚለወጥ ዓለም የማይለወጥ አምላክ ተሐድሶ ማን? ገጽ 32
[196] ዝኒ ከማሁ፣ገጽ 35
[197] መሪራስ አማን፣(2001 ዓ.ም) ፣ መጽሐፍ ክብር፣ ገጽ 356

*“የሚለወጥ ዓለም የማይለወጥ አምላክ ተሐድሶ ለማን?”* መጽሐፍ ደራሲ እንዳሉት የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፕሮቴስታንቶችን “መናፍቅ” ትል ይሆን? በአገራችን ብዙዎች መናፍቅ የሚለውን ቃል ጽንሰ ሐሳብ ባለመረዳት ያልተቀበሉትን አገልግሎት ሁሉ መናፍቅ ብሎ መፈረጅ የተለመደ ነው:: በአገራችን በተለይ በቤተ ክርስቲያን አካባቢ የተባለውን ሁሉ ከማመን ውጪ ምክንያታዊነትና በእግዚአብሔር ቃል እውነት ላይ መነጋገር አልተለመደም:: የአንድ ሃይማኖትም ሆነ ርዕዮተዓለም ደጋፊ ካልሆንክ ወዲያው በተቃዋሚነት ትፈረጃለህ:: ውሸት በሰው ልብ ነግሣ እውነት በአደባባይ የተጣለች ትመስላለች:: ከዚህም የተነሣ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ በክርስትና ስም በገሃድ የሚያራምዱ እውነትን በተቃሙት ብዙሃን ሲሞካሹ በቃሉ እውነት እየኖሩ እውነትን በሚሰብኩት የእግዚአብሔር ሰዎች በተቃራኒው የባሕርይ ገደላ ሲካሄድባቸውና በአደባባይ ሲወገዙ ይታያሉ::

ኢየሱስ ሲናገር:-*“...የሚገድላችሁ ሁሉ እግዚአብሔርን እንደሚያገለግል የሚመስልበት ጊዜ ይመጣል”(ዮሐ.16:2)* እንዳለው የእውነተኛ ወንጌል አገልጋዮች መልካም ስምና አገልግሎት ገዳዮች የብርሃን መልአክን መልክ ተላብሰው እየታዩ ናቸው:: ያም ሆኖ በእውነት ላይ ማንም ምንም ሊያደርግ አልቻለም:: እውነት ተናጋሪን መግደል ቢቻልም እውነትን መግደል ግን በፍጹም አይታሰብም:: እውነት ከራሱ ውጪ ሌላ ደጋፊ አይፈልግም:: እውነት ሁሌ አሸናፊ ስለሆነ ለማሸነፍ ትጮሀ አያስፈልገውም፤ ተቃውሞም ምንም ስለማያደርገው አይሸበርም:: ኢየሱስ እውነት ነው:: መምህር ብሩክ ገብረ-ሊባኖስ ተስፋዬ መናፍቅ እያሉ የመፈረጅ ወረርሽኝ በቤተ ክህነት እንዴት እንደተዛመተ እንዲህ ይገልጻል:-

> *እንደ ግለሰቦቹ እምነት እነርሱ ከሰበኩት ውጭ ያለው ስብከት 'ክህደትና ኑፋቄ ነው፤ የእነርሱ አባል ያልሆነ ሰባኪም ' መናፍቅ ተሐድሶ ነው፤ እነርሱ ያልዘመሩት መዝሙር 'ዘፈን ነው::... ግለሰቦቹ ቤተ ክርስቲያን ሰዎችን መናፍቅ ብለው ለማውገዝ ደረጃቸውና ዓቅማቸው ባይፈቀድላቸውም ቤተ ክህነት ውስጥ ደረጃ መዳቢ ባለሥልጣን ስለሌለ እንደ ፈለጉ ስም ያጠፋሉ፤ ይሳደባሉ ይዘልፋሉ፤ ያወግዛሉ፤ ይገዝታሉ::*[205]

የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ እንደሆኑ በመጽሐፉ የገለጹት ሊቀ ማእምራን ዲበ ኩሉ በቤተ ክርስቲያኑ ስለተንሰራፋው የ‹ነውገዝ ሁኔታ እንዲህ ብሏል:-

> *መሪጌታ እገሌ፣ ቄስ እገሌ፣ አቡነ እገሌ መምህር እገሌ ዘማሪ እገሌ ወ.ዘ.ተ ተሐድሶ ናቸው መወገዝና መባረር አለባቸው እየተባለ ቤተ ክርስቲያኗን ምዕመን ብቻ ለማስቀረት ሰይጣን እየተጠቀመባቸው ያሉ ወገኖች አሉ:: እነዚህ ሰዎች ይህንን በማድረጋቸው ንስሐ ሊገቡ ይገባል*[206] *ብለዋል::*

[205] *የሰው ያለህ፣ 2005 ዓ.ም ገጽ 408*

[206] ሊቀ ማእምራን ዲቤ ኩሉ *(2005 ዓ.ም)* ፣ ሎሬ፣ አዲስ አበባ-ኢትዮጵያ፣ ገጽ 85





አሳዛኙ ነገር የክርስትና ደሴት በተባለች አገራችን ነቢያቶች የተነበዩለት፣ በሥጋ የተገለጠው የክርስቶስን ሞትና ትንሣኤ የሚሰብኩ ***“ጴንጤ! ተሐድሶ! መናፍቅ”*** ተብለው ስለሚወገዙ ወንጌልን በገሃድ እንዳይሰብኩ ብዙዎች በፍርሃት ተጠፍንገዋል:: አብዛኛው የስብከትን መድረክ የተቆጣጠሩ ያልተማሩ አስተማሪዎች፣ የወንጌል ስብከት ጥሪም ሆነ ዕውቀቱ ስለሌላቸው መንጋውን በማሳሳት ላይ ይገኛሉ:: ስለዚህም መጋቤ አእላፍ መክብብ ትዝብቱን እንዲህ ብሎ አስፍሮዋል:-

> *አንዳንዶቹማ ያለችሎታቸው በያዙት የስብከት ወንጌል መድረክ ስንቱን ሕዝብ በማሳሳት ግራ ሲያጋቡ ይኖራሉ:: አብዛኛውን ጊዜ ትምህርታቸውም ሆነ ስብከታቸው እግዚአብሔርን ማእከል አያደርግም:: ኢየሱስ ክርስቶስ ብሎ መናገርም በተሐድሶነት ያስጠረጥረናል ብለው በስሙ የሚያፍሩበት ብዙዎች ናቸው::*[207]

ጥቂቶች በነፍሳቸው ተወራርደው ክብራቸውን ጥለው የጌታን ወንጌል በድፍረት ሲሰብኩ ለእውነትና ለቤተ ክርስቲያን ቀኒዓ እንደሆኑ በሚናገሩ ሰዎች *“የተሐድሶ መናፍቅ”* ተብለው የባሕሪይ ገደላ ሲፈጸሚባቸውና እንደ አርዮስ ሲወገዙ ማየት በአገራችን የተለመደ ነው:: ዛሬ በለንደን እንግልዝ መንገድ ላይ ቆሞ ግብረሰዶማዊነትን ትክክለኛ የአኗኗሪ ዘይቤ እንደሆነ ማወጅ የማያስጠይቅና ማንንም የማያስከፋ ሲሆን ኢየሱስ ብቸኛ የዓለም መድኃኒት እንደሆነ በአደባባይ መስበክ ግን ለእሥራትና ለወህኒ ይዳርጋል:: እንደዚሁም በኢትዮጵያ በአንዳንዶች ዘንድ ስለ መላዕክት፣ ስለ ማርያም፣ ስለሰንበት፣ ስለቅዱስ እገሌ አዳኝነት መስበክና መጻፍ የተለመደ ሲሆን የዓለም አዳኝ እንደ ሆነ ነቢያት፣ ሐዋርያትና የቤተ ክርስቲያን አበው የሰበኩት የጠራውን የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል መስበክ ፍርድ ቤት ባያስቆምም መናፍቅ፣ ጴንጤ፣ መጤ፣ የአገር ጠላት፣ ፀረ ማርያም የሚሉ ፍረጃ ተጠቂ ያደርጋል:: ከተሳዳጆች ጋር የሚቆም እግዚአብሔር በእውነት ላይ ቆመው ውሸትን እየሞገቱ ባሉ ጥቂቶች ምድራችንን ለዘመናት ከተጠፈረችበት እውነት መሳይ ውሸት ይፈታታል ብዬ አምናለሁ::

የኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ፣ የኃጢአት ንዛዜና ዳግም በመወለድ በአዲስ ሕይወት ከክርስቶስ ጋር መኖር እንዳለብን የማይሰበክበት “ወንጌል” ማንም ይስበከው፣ የትም ይሰበክ መንፈሳዊ ወንጀል ነው:: በምድር ሕግ ባንጠየቅም የዘላለም ጌታ እያንዳንዳችንን እንደሚጠይቀን ቃሉ ይናገራል:: *“እያንዳንዱ በሥጋው የተሠራውን በብድራት ይቀበል ዘንድ ሁላችን በክርስቶስ በፍርድ ወንበር ፊት ልንቆም ይገባናል” (2ቆሮ.5:10)::* *“እርሱ ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው ያስረክበዋል” (ሮሜ.2:6)::* ወንጌል አጭርና ግለጽ ሲሆን ወንጌል ያልገባቸው *“ሰባቂዎች”* የምድሩንና የሰማዩን ቀይጠው ሲያወሳስቡት ማየት በእኛ ዘመን የተጀመረ ሳይሆን የነበረ ነው:: ወንጌል ግን ሁሉንም ያሸንፋል:: የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ሐዋርያትን ሲልክ የማይለወጠውን ወንጌል ሰጥቷቸው ነበር:- *“...የማይለወጠውን ቅዱስ*

[207] መክብብ አጥናው (መጋቤ እእላፍ) *(2004 ዓ.ም)*፣ አምስተኛው ጉባኤ ዕድሜ ቀጥል፣ ትምህርት ዐዘል የአባቶች ጫዋታ፣ ክፍል አንድ፣ አዲስ አበባ ፣ ገጽ 12

*ወንጌል ከፀሐይ መውጫ እስከ መጥለቂያው ድረስ በእጃቸው ላከ"(ማር.16:8):: "ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ"* ሐዋርያ ጳውሎስ ማንን ይሰብክ እንደነበር ሲናገር:- "እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን" (1ቆሮ. 1:23) ካለ በኋላ ራሱንና እኛንም ሲያስጠነቅቅ *"ወንጌልን ባልሰብክ ወዮልኝ" (1ቆሮ.9:16)::* ብሏል::

## መናፍቅ ማን ነው?

በተለይ በቤተ ክርስቲያን አካባቢ ኑፋቄ፣ መናፍቅ፣ መናፍቅነት የሚሉት መጠሪያዎች ለጆሮአችን አዲስ አይደሉም:: ፍቺው ከሊቃውንቱ መዝገበ ቃላት ሲፈተሽ ደስታ ተክለወልድ (በገጽ 794) ላይ ኑፋቄን (መናፍቅን):- *"ሃይማኖተ ግማሽ"* ሲሉት፣ ከሣቴ ብርሃን ተሰማ የተሰኘው የአማርኛ መዝገበ ቃላት ደግሞ (ገጽ 110) ላይ *"ከእውነተኛ ሃይማኖት መውጣት፤ በፈጣሪ በእግዚአብሔር የማያምን፣ ይልቁን የኢየሱስ መድኃኒትነት፣ የመንፈስ ቅዱስን ሕይወትነት የማያምን የሚክድ"* ነው፤ ብሎ ይፈታዋል:: የሊቃውንቱ ትርጉም ግልጽና ትክክል ነው:: የእግዚአብሔርን ቃል እውነት ሸራርፎ፣ ቆርጦ፣ ገምሶ የሚያስተላልፍና የሚሰብክ ሁሉ በኑፋቄነት ይመደባል::

በተለይ የኢየሱስ ክርስቶስን መድኃኒትነትና የመንፈሱን ሕይወትነት የማይቀበሉ መናፍቃን ሲሆኑ ያፈነገጠና የጉደለ ትምህርት ኑፋቄ ነው:: ሐዋርያ ጳውሎስም ስለዚህ ሲናገር:- *"እኛ ብንሆን ወይም ከሰማይ መልአክ፣ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን ቢሰብክላችሁ፣ የተረገመ ይሁን:: አስቀድመን እንዳልን እንዲሁ አሁን ሁለተኛ እላለሁ፣ ከተቀበላችሁት የተለየውን ማንም ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን" (ገላ.1:6-8 መ.ደ.ት.)::* በማለት ለሰው ልጆች የተሰጠው የመዳን መንገድ የሚያመለክት የወንጌል ቃል የማይደለዝ፣ማስተካከያ የማይፈልግ፣ የማይቀነስና የማይጨመርበት እንደሆነ በግልጽ አስቀምጧል:: ከዚህ የተለየ ሁሉ ኑፋቄ ነው:: ተስፋዬ ሮቤሌ በዐቃብያነ ክርስትና *(Apologetics)* ላይ በዛ ያሉ መጻሕፍት ያቀበለን የነገረ መለኮት ሊቅ ሲሆን፣ "ዐበይት መናፍቃን" በሚል ርዕስ በጻፉት መጽሐፍ፣ ዕውቅ የነገረ መለኮት ምሁራንን ዋቢ በማድረግ መናፍቅ የሚለውን ቃል ምንነት ሲያስረዱ:-

> *ከክርስትና እምነት የወጡ መናፍቃን ራሳቸውን ክርስቲያን ብለው የሚጠሩ፤በመሪዎቻቸው ወይም በድርጅቶቻቸው የተሰጠውን የተወሰነ አስተምህሮአዊ ሥርዓት የሚከተሉ፣ ይህም አስተምህሮአዊ ሥርዓት ከሥልሳ ስድስቱ የመጻሕፍ ቅዱሳን ጽሑፎች የተቀዳውን የክርስትና እምነት መሠረታዊ አስተምህሮ አንድ ወይም ከአንድ በላይ ትምህርት የሚክዱትን መናፍቃን ብለን እንጠራቸዋለን::*[208] ብለዋል::

[208] ተስፋዬ ሮቤሌ *(2001 ዓ.ም) ፣ዐበይት መናፍቃን፣ ገጽ 11*







በመቀጠልም:-

> *መሠረታዊ በሆኑ ክርስቲያናዊ ትምህርቶች ላይ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን፣ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንና የፕሮቴስታንቶች (የወንጌል አማኞች አብያተ ክርስቲያናት) አንድ ዓይነት አቋም አላቸው:: ምናልባት አብያተ ክርስቲያናት ያላቸውን መሠረተ እምነት አማኒያኖቹ ላይረዱት ይችላሉ:: እንዲረዱት ማድረግ ተገቢ ቢሆንም፣ ቤተ ክርስቲያኖቹን እንደ መናፍቅ መቁጠር ግን ፍጹም ስሕተት ነው*[209] ብለዋል::

በዚህ ላይ ሳልጠቅስ የማላልፈውና በጣም ያስገረመኝ አንድ ጉዳይ፣ በዚህ ጥናት ብዙ የአገራችን መጻሕፍትና መረጃዎችን ሳገላብጥ፣ አብዛኛው የኢትዮጵያ የፕሮቴስታንት የነገረ መለኮት ጸሐፍት ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጋር የመሠረተ እምነት አንድነት እንዳላቸው ሲቀበሉ፣ አብዛኛው የኦርቶዶክስ ጸሐፍት ግን ሌላው ቀርቶ የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናትን *"ቤተ ክርስቲያን"* ብለው ለመጥራት እንኳ እንደማይፈልጉና ከአንድነት ይልቅ፣ ያለውን ልዩነት እጅግ ለማጉላት ሲታገሉ መታየታቸው ነው:: አንድነታችን የመጣው ከክርክራችን ሳይሆን መመሪያችን ብለን ከያዝነው በእጃችን ካለው ቃልና የምንጠራው አምላክ አንድ መሆኑ ነው:: አንዳንድ የኦርቶዶክስ ጸሐፍት እንደሚሉት ፕሮቴስታንቶች መናፍቅ ከሆኑ ቤተ ክርስቲያናቸው በአህጉርና በዓለም አቀፍ ደረጃ የአብያተ ክርስቲያናት ማህበር ላይ የመሠረተ እምነታቸውን ተቀብላ "ከመናፍቅ-ፕሮቴስታንቶች"ጋር ለምን ኅብረት መሠረተች? ምናልባትም ይህ አመለካከት የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አቋም ሳይሆን የቃሉን ትርጉም ያልተረዱት አንዳንድ ጸሐፊዎች የሚያካሂዱት መሠረተ የለሽ አሳብ ሊሆን ይችላል:: ጥር 30 ቀን 2001 ዓ.ም፤ በአፍሪካ ኅብረት አዳራሽ ዓላማው በኢትዮጵያ የአብያተ ክርስቲያናት ኅብረት ምሥረታ ላይ ለመመካከር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን፣ የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያንና የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት መሪዎች አንድ ላይ ተቀምጠው ነበር::[210] በዚህ የምክክር ጉባኤ ላይ ጥናታዊ ጽሑፍ ካቀረቡት መካከል በኦርቶዶክሳውያን በኩል የመንበረ ፓትርያርክ ጽ/ቤት ምክትል ሥራ አስኪያጅ የሆኑት ንቡረኢድ ኤልያስ አብርሃ ይገኙበታል:: እሳቸው ለዚህ ጉባኤ ጥናታዊ ጽሑፋቸውን ሲያቀርቡ:-

> *ጥንትም አሁንም ለወደፊቱም የማይለወጠው የእግዚአብሔር ዓላማ፣ ሁሉንም በአንዲት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በክርስቶስ መጠቅለል ነው:: የአሁኑ ትውልድም መሥራት ያለበት፣ ይህንኑ የእግዚአብሔር ዓላማ በመቀበል ነው:: ነገር ግን ወደዚህ ውሕደት እንዴት መምጣት ይቻላል? የሚል ጥያቄ ቢኖር፣ በመጀመሪያ በመከባበር፣ በመተጋገዝና በፍቅር ላይ የተመሠረተ ኅብረት መፍጠር...መፍትሔ ሊሆን ይችላል::*[211]

[209] *ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 15*
[210] *ማኅቶተ መንፈሳዊ መጽሔት፣ ቅጥር 10 መጋቢት 2001 ዓ.ም*
[211] ኤልያስ አብርሃ (ንቡረእድ)፣ *የአብያተ ክርስቲያናት ኅብረት ጥቅም እና የልዩነታቸው ጉዳይ (ጥናታዊ ጽሑፍ፡ ያልታተመ)*

ብለው የተናገሩት ቤተ ክርስቲያናቸው ለሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ያላትን ትልቅ ልብና መጽሐፍ ቅዱሳዊ አቋም በግልጽ ያመለክታል።

*ተሐድሶ የእግዚአብሔርን ቃል የመለወጥ ሂደት ሳይሆን፣ የሰዎችን ያረጀ ሕይወት፣ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ልምምዶችና ለስተምህርዎችን በማይለወጠው ቃሉና መንፈሱ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የመለወጥ ሂደት ነው።*

የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ያልነበረውንና የሌለውን መፍጠር ማለት አይደለም። የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ በክርስትና ሃይማኖት መሠረተ እምነት ላይ ለውጥ ማድረግም አይደለም። የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ የቤተ እምነት ስም የበላይነት የሚሰበክበት ምስባክም አይደለም። የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ኦርቶዶክስን ፕሮቴስታንት ወይም ካቶሊክን ኦርቶዶክስ አሊያም ፕሮቴስታንትን ኦርቶዶክስ የማድረግ ዘመቻ በፍጹም አይደለም። ሊሆንም በፍጹም አይገባም። የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ በቃሉና በመንፈሱ የልብ ለውጥ እንጂ የድርጅት ስም ወይም የታፔላ ለውጥ አይደለም።

ተሐድሶ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያንን እንደ እግዚአብሔር ቃል የማደስ እንጂ አገራዊ ባሕልና እሴቶቻችንን ምዕራባዊ ለማድረግ የምንዋደቅበት ሜዳም አይደለም። የክርስትና መሠረት ክርስቶስ እንጂ የምዕራቡ፣ የምሥራቁ፣ የሰሜኑ፣ የደቡቡ ዓለም ባሕልና እሴት አይደለም። የኢትዮጵያ ባሕልም የክርስትና መሠረት አይሆንም። ክርስትና ከባሕሎች ሁሉ የበላይ የሆነ መለኮታዊ መልዕክት ነው። የክርስትና መሠረት ክርስቶስ ሰማያዊ ሲሆን አካሉ የሆነች ቤተ ክርስቲያንም በምድርና በሰማይ ላሉት አለቆችና ሥልጣናት የተገለጠች ሰማያዊ አካል ናት። ተሐድሶ፡-

- ተሐድሶ የበላይነታችንን የምንሰብክበት ሳይሆን የበላይ ለሆነው የእግዚአብሔር ቃል ዕውቅና በመስጠት ዝቅ በማለት ራሳችንን የምናይበት ሚዛን ነው።
- ተሐድሶ ወደ ስማችን ሰዎችን የምንጠራበት ሜዳ ሳይሆን በቃሉ ብርሃን እየተመራን የጌታን ዱካ የምንከተልበት መንገድ ነው።
- ተሐድሶ ለእያንዳንዱ ክርስቲያንና እውነተኛ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ዋና ጉዳይ እንጂ ተጨማሪ የቤት ሥራ አይደለም። ተሐድሶን መጥላት መንፈሳዊ እርጅና እና ሞትን እንደ መውደድ ነው። የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ በክርስትና መሠረተ እምነት ላይ የተገነቡ ኢ-መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮዎችን፣ ትውፊቶችን፣ ልምዶችንና አሠራሮችን የሚያጠራ ነው።





በሌላ አገላለጽ ተሐድሶ ማለት፡- *ወደ ቀደመው እውነት ወይም አስተምህሮ መመለስ፣ የተቀበረውን ቆፍሮ ማውጣት፣ እንዲሁም የቀደመውን ጤናማ ትምህርት መጠበቅ፣ መያዝ፣ እንደገና መገንባት፣ ወደ ተሻለ ሁኔታ መቀየር፣ የተሳሳቱ ልምምዶችንና አጠቃቀሞችን በማስወገድ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ ጉዳዮችን በአገባቡ ማስተካከል ነው።*[212]

በአገራችን አንዳንዶች ተሐድሶን የሌለ ነገር እንደመፍጠርና እንደ ሹራቅ አድርገው ስለሚያቀርቡ የተሐድሶ ፍርሃት በቤተ ክርስቲያን እጅግ ከመንገሡም አልፎ የተሐድሶን አሳብ አንግበው የተነሡ ሁሉ እንደ ከሃዲ፣ እንደአጥፊ፣ እንደ አፍራሽና እንደሳተ ተቆጥረው በዚህችው ታላቅ አገር ሲሰደዱ፣ ሲታሠሩ፣ ሲወገዙና በኢ-ሰብዓዊ መንገድ ሲገደሉ ምዕተ ዓመታት ተቆጥረዋል። ከዚህም የተነሣ ምድራችን ነፃ የሰዎች አሳብ እንደ ጦር የሚፈራባት፣ የተለየና ብልጫ ያለው አሳብ ያላቸው ዜጎች እንዲኖሩባት በፍጹም የማንፈቅድ ስለሆነ አገራችን በታሪክ ከሁሉም ቀዳሚ ሆና በተግባር የመጨረሻዎቹ መጨረሻ ሆናለች። በየትኛውም ዓለምና ሕብረተሰብ ዘንድ የለውጥ ፍርሃት ያለ ቢሆንም በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አካባቢ ያለው ግን የተለየ ነው። በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የተሐድሶ/የለውጥ/ ፍርሃት እንዲነግሥ አንዱ ዐቢይ ምክንያት የሆነው ለኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትውፊት የተለየ ቦታ መስጠታችን ነው። "ትውፊት"[213] ቅብብሎሽ ነው። ትውፊት የባሕላችን አካል የማንነታችን መገለጫ ነው። ትውፊት ያስፈልገናል። ነገር ግን ከቃሉ እውነት ጋር የሚጋጭና ሁሌ ወደ ኋላ ብቻ እንድንመለከት የሚያደርጉንና ለተገለጠው ለእግዚአብሔር ቃል እንዳንታዘዝ እንቅፋት የሚሆኑብን ትውፊቶች የግድ መፈተሽ አለባቸው።

አባ መልከጼዴቅ ጳጳስ ስለዚህ ሲናገሩ፡-

*በስመ ትውፊት ማንኛውንም መቀበል የለብንም፣ በእውነተኛውና በቅዱሱ ትውፊት መካከል ለዶክተሪናችን፣ ለቅዱስም መጽሐፋችን ተቃራኒ የሚሆኑ ትውፊቶች መስለው የገቡ ሊገኙ ይችላሉና። ቤተ ክርስቲያን ግን ቅዱስ መጽሐፍን ከሐሰተኛ መጽሐፍ ሁሉ ለይታ አጣርታ እንደተቀበለች ጠብቃ አክብራ እንደያዘችው ሁሉ አሁንም እውነተኛውን ትውፊት ለይታ አክብራ መያዝ አለባት። ሐሰተኛ የሆነውን ሰው ሠራሽ የሆነውን ሥርዓት እንደ ትውፊት አድርገውም ቢይዙት ከእግዚአብሔር ሕግ ውጪ ያደርጋል፣ ለቅዱስ መጽሐፍም ተቃራኒ ይሆናል። እንደዚህ ያለውን ሰው ሠራሽ ሥርዓት ፈሪሳውያን እንደ ትውፊት አድርገው ቢይዙት ጌታ እንደተቃወመ እናገኛለን*[214] በማለት ከቃሉ ጋር የማይፋለስና የማይጣረስ ትውፊት አስፈላጊነትንና ሰው ሠራሽ ከሆነ ግን አደገኛ ሊሆን እንደሚችል ገልጸዋል።

---

[212] Chaillot Christian, *(.2002), The Ethiopian Orthodox Church: A Brife introducation to its life and spirituality,* (Paris: inter Orthodox Dialogue 31-32. see also Taddese Tamrate*(1972) , church and state* Oxford: Clarendon., 114

[213] "*...ልማድ፣ ትምህርት፣ ወግ፣ ታሪክ፣ ሃይማኖት፣ ሥርዓት ከጥንት ከአበው ሲያያዝ ሲወርድ ቃላት በቃል ሲነገር የመጣ*" አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፌሌ *በመዝገበ ቃላት ገጽ 396*

[214] አባ መልከጼዴቅ ጳጳስ (1994 ዓ.ም)፣ *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ትምህርት፣ ገጽ 71*

ሪክ ዋረን በትውፊት ስለሚመሩ ቤተ ክርስቲያናት ሲናገር:-

*ትውፊት-መር በሆነ ቤተ ክርስቲያን የተወደደው ሐረግ 'እኛ ሁልጊዜም በዚህ መንገድ ነበር እንሠራ የነበረው' የትውፊት-መር ቤተ ክርስቲያን ግብ ያለፈውን ነገር ማስቀጠል ነው:: ለውጥ ሁልጊዜም ቢሆን በአሉታዊ መልኩ የሚታይ ነው፤ ደግሞም ባሉበት ረግቶ 'አለመንቀሳቀስ መሠረት እንደ መያዝ ነው...በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ትውፊት፣ ሁሉም ነገር፤ የእግዚአብሔር ፈቃድ እንኳ ሁለተኛ የሚደረግበት፣ እንደዚህ ዓይነት አንቀሳቃሽ ኃይል ነው*[215] ብሰዋል::

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነ ትውፊት በቤተ ክርስቲያን የቃሉን ቦታ ከወሰደ፣ ዛሬ ላይ የትናንቱ ባሕልና አሠራር አቀንቃኝ ካደረጋት ዕድገትና ለውጥ አይታሰብም:: የአገራችን ቤተ ክርስቲያን እንደ ቃሉ የሆኑ መልካም ትውፊት መጠብቅ አለባት፤ ቃሉን ከሚጋርድ ትውፊት ግን በቃሉና በመንፈሱ መታደስ አለባት:: የቤቱ ራስ የሆነው ክርስቶስ በቃሉና ለዚህች ቀን በተዘጋጁ ልጆቹ ይህን የዘላለም አጀንዳውን እውን ያደርጋል::

ክርስቶስ አይታደስም፤ መጽሐፍ ቅዱስ አይታደስም *(ለዘመኑ በሚመጥን ቋንቋ አይተርጎምም ማለት ግን አይደለም)*፤ የቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱሳዊና መሠረታዊ ትምህርት (ዶግማ) አይታደስም:: ቤተ ክርስቲያን ማለት የቅዱሳን ኅብረት ስለሆነች ቅዱሳን ደግሞ በሥጋ ስላሉና በወደቀች ዓለም ስለሚመላለሱ ዕለት ዕለት በቃሉና በመንፈሱ መታደስ አለባቸው:: የቤተ ክርስቲያን ቀኖና *(በሰው የተፈጠሩ ሥርዓቶች)* ይታደሳሉ:: ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ፣ ራስን መመርመር፣ በቃሉና በመንፈሱ ራስን ማየት፣ ወደ ቀደመው መንገድ መመለስ፣ ባያስፈልጋት ኖሮ የቤተ ክርስቲያን ሠሪና ራስ የሆነው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ከዛሬ ሁለት ሺ ዓመት በፊት *"እንግዲህ ከወዴት እንደወደቅህ አስብ ንስሐም ግባ የቀደመውንም ሥራህን አድርግ፤ አለዚያ እመጣብሃለሁ ንስሐ ባትገባም መቅረዝህን ከሥፍራው እወስዳለሁ"(ራእ.2:5)::* በማለት የመነሳት ዕድልና ማስጠንቀቂያ ባልሰጣት ነበር:: በሀብቷ፣ በስሟ፣ በሕዝብ ብዛትዋና በዝናዋ ገናና የነበረች፤ በሥርዓትና በወግ ተወጥራ ክርስቶስን ከቤቱ ገፍታ ከውስጧ ላስወጣችና የዘመናችን ቤተ ክርስቲያን ተምሳሌት ለሆነች የሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን *"ከአፌ ልተፋህ ነው" (ራእ.3:14)::* በማለት ባላስጠነቀቃትም ነበር::

## መፍትሔው ምን ይሆን?

ድህረ ዘመናይነትና አንጻራዊነት ላንበረከካት ለምዕራባዊቷና ገድል፣ ድርሳናት፣ የትላንትና ልምድና አሠራር ላስረጃት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መፍትሔው አንድ ሲሆን፣ እርሱም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ተሐድሶ

[215] *ዓላማ መር ቤተ ክርስቲያን (ተርጓሚ የሌስ ላይ ሌም ሥነ ጽሑፍ) 1995 ገጽ 98*





ነው:: መፍትሔው ወደ ቀደመው የቃሉና የመንፈሱ መንገድ መመለስ ነው:: ለመመለስ ደግሞ አሁን ያለንበትን አሮጌ ቀለበት ሰብረን መውጣት አማራጭ የለውም:: ክርስቶስ በግድና በኃይል አላዳነንም በኃይልም አያድሰንም:: ቃሉ ስለ ኤፍሬም ሲናገር:- *"ሽበት ወጣበት፣ እርሱም አላወቀም፤ የእስራኤልም ትዕቢት በፊቱ መሰከረ፣ ወደ አምላካቸው ወደ እግዚአብሔር አልተመለሱም፤ በዚህም ሁሉ አልፈለጉትም"* (ሆሴ 7:8-9):: እንደሚለው ማርጀታችንን ቃሉና ያለንበት ተጨባጭ ሁኔታ እየመሰከሩብን፣ የጥፋትን መንገድ መርጠን እንዳንጠፋ እርሱ ይርዳን::

ኢየሱስ ክርስቶስ በግድ ቤተ ክርስቲያንን የሚያድስ ቢሆን ኖሮ፣ የሎዶቅያን ቤተ ክርስቲያን "ደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ" (ራእ. 3:19):: እያለ በትህትና ውጪ ቆሞ ወደ ውስጥ ገብቶ ለመረዳት ፈቃድዋን ባልጠየቃት ነበር:: እንዲሁም ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ሕያው መስለው ባልሞቱ፤ ትውፊት፣ ድርሳናትና ገድላት የወንጌልን ቦታ ባልወሰዱ ነበር:: የአምልኮ ሕንፃዎች ግንባታ፣ ልበ ክርስቲያን ያልሆነ ሕዝብ የአምልኮ ቦታ ማጣበብና የሰው ብዛት ብቻውን የአንዲት ቤተ ክርስቲያን የሕያውነት ምልክት ሊሆን በፍጹም አይችልም:: ይህማ ቢሆን ኖሮ በሌሎች ዓለማት ያየናቸው ትላንት በቅዱሳን አምልኮና ምስጋና የታወቁ፣ ድንቅና ታምራት የለመዱ መድረኮችና የዘላለም ወንጌል የተሰበከባቸው ታላላቅና ውብ ካቴድራሎች፣ ለምግብና ለጭፈራ ቤትነት ባልተሸጡ ነበር:: በሕዝብ ብዛት ተጨናንቀው የኢየሱስ ወንጌል በገሃድ የማይሰበክባቸውና ሕዝብ አጥተው የተዘጉ አብያተ ክርስቲያናት ሁለቱም አንድ ናቸው::

የቃሉና የመንፈሱ ተሐድሶ፣ ከእግዚአብሔር የጊዜው አጀንዳ ጋር ለሚሄዱ ሲሆን፣ በደጅ ቆሞ እያንኳኳ ያለውን፣ የቤቱን ባለቤት ድምፅ ሰምተው፣ የልባቸውን በር የሚከፍቱ አብያተ ክርስቲያናት ብፁዓን ናቸው:: በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ፣ በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናትም ሆነ በካቶሊክ አብያተ ክርስቲያናት ሥር ለሚገኙ ሁሉም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ተሐድሶ ያስፈልጋቸዋል::

## የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አሸናፊ ሆና ለመገለጥ:-

- በቃሉ ዓለት ላይ መመሥረት፣ የመንፈስ ሰይፍ የሆነውን የእግዚአብሔርን ቃል መታጠቅ፣
- ያረጁና የተበላሹ አሠራሮችን ከቤተ ክርስቲያን ማስወገድ፣
- እግዚአብሔርን፣ ዘመኑን፣ ራሳቸውንና ተልዕኮአቸውን በቅጡ አውቀው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ለተግባራዊነቱ የሚገለጡ አገልጋዮችን ማፍራት፣

- አገልጋዩና ምዕመኑ የእግዚአብሔርን ቃል እንዲፈሩ ማድረግ፤ በእግዚአብሔር ቃል ላይ የሚታበዩትን ማቅናት፣ መገስጽና ተገቢውን እርምጃ መውሰድ። በአባላት ቁጥር በቤተ እምነት ማንነት ከመታበይ ይልቅ የመንፈስ ፍሬ ላይ ትኩረት መስጠት፣
- ከቤተ እምነታዊ ብሔርተኝነት ይልቅ የእግዚአብሔርን መንግሥት አመለካከት ማሳደግ፤ ሲወርድ ሲዋረድ ለመጣው አሮጌው አሠራርና አመለካከት ብቻ ሳይሆን፤ በአዳዲስ አሳቦች ላይ በግልጽ የመነጋገር ባሕልን ማዳበር፣
- የለውጥ አንቀሳቃሽ ሞተር የሆነውን አዲሱን ትውልድ በቃሉና በመንፈሱ ኮትኩቶ ማሳደግ፤በቤተ ክርስቲያን ያደጉና ኑሮአቸውን በቃሉ መርህ የቃኙ በፖለቲካው፣ በንግዱ፣ በግብርና፣ በትምህርት፣ ወ.ዘ.ተ እንዲገለጡ ማስተማር፣
- ቅዱሳንን ተጽዕኖ ፈጣሪዎች እንዲሆኑ ማደፋፈር፣ ተግቶ መሥራት፣ ትልቅ አገራዊና ዓለም አቀፋዊ ራእይ አንግበው መነሣት ይገባቸዋል።

ዛሬም በ21ኛው ክፍለ ዘመን በኢትዮጵያ ያሉ አብያተ ክርስቲያናት፣ ክርስቶስን ማዕከል ካላደረገው የሃይማኖት ግርግር፣ ወንጌል ከሌለበትና የሰዎች ምኞት እንደ ወንጌል ከሚሰበክባቸው አብዛኛው የኮንፍረንሶች ድግስ፣ የመስቀልንና የጸጋን ሥራ ከጋረዱ ባዶ ኢመጽሐፍ ቅደሳዊ ትውፊቶችና አገራዊ እውነቶች ወደ ጠራውና ወደ ጠለለው ቃል በመመለስ አስተምህሮዎቻቸውን በቃሉ ፈትሸው ለለውጥ ካልተዘጋጁ ጌታ እንዳለው ሕያው መሳይ ሙት ይሆናሉ። ግን ተሐድሶ/መለወጥ፣ መመለስ፣ ንስሐ/ እያለ ሞት ለምን? የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በደጅ ያለውን የተሐድሶ ድምፅ ቸል ማለት አይገባትም። ተሐድሶ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ያስፈልጋታል። የተሐድሶ ጥያቄ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የተነሳው የተሐድሶ ውጤት የሆኑ የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት በዓለም ላይ ሳይወለዱ ነበር።

በአገራችን የተሐድሶ ጥያቄ ከ800 ዓመታት በላይ የተቆጠረ ቢሆንም ዛሬም ፕሮቴስታንቶችን ተከትሎ ከ100 ዓመት ወዲህ ወደ አገር ውስጥ የገባ *"መጤ"* ጽንሰ ሐሳብ ተደርጎ ይታሰባል፤ ሲነገርም ይሰማል። ይህ ትልቅ ስህተት ነው። ከብዙ አገሮች ቀድማ የተሐድሶ ጥያቄ የተነሣባት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጥያቄውን ማስተናገድ አልቻለችም። ተሐድሶ የሚለው ስም በአገራችን በቤተ ክርስቲያን አካባቢ እንደ ጦር ከመፈራት አልፎ አንድን ሰው ወይም ቡድን ለማግለል፣ ለማራቅና ተቀባይነት እንዳይኖረው ከተፈለገ በስሙ ወይም በስማቸው ላይ የሚለጠፍ የውግዘት ታፔላ(ስሌዳ) መስሏል። በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የተሐድሶ ጥያቄ ዘመን ዘለቅ መሆኑን በታሪክ ገጽ የተቀመጠውን እውነት በመረጃ በማስደገፍ በሚቀጥለው ምዕራፎች በስፋትና በጥልቀት ቀርቧል።



# ፬

# ከሉተር የቀደመ የተሐድሶ ጥያቄ በኢትዮጵያ

## የዐፄ ያግብ ጽዮን ዘመን *(1278 - 1286)*

የተሐድሶ(ለውጥ) ጥያቄ ማርቲን ሉተር ከመወለዱ ከ150 ዓመት በፊት እንዲሁም፣ የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት በኢትዮጵያ ከመታወቃቸው ከ614 ዓመት በፊት በኢትዮጵያ ተወልዶ በደም የታተመ ታሪክ አለው። ይህ እውነት ታሪክን ከግለኝነትና ከጠባብነት ወጥቶ በሐቅ የሚያጠና ሁሉ በቀላሉ የሚረዳው እውነት ነው። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የተሐድሶ ጥያቄ ሲነሣ ደቂቀ እስጢፋኖስ የመጀመሪያ እንዳልሆነ የታሪክ ድርሳናት ያወሳሉ። አባ እስጢፋኖስና ተከታዮቻቸው ከመነሣታቸው ከመቶ ሃምሳ ዓመት በፊት ትግራይ ውስጥ ለሥዕልና ለመስቀል አንሰግድም *"ምክንያቱም ሥዕል ሠሌዳ ነው፤ መስቀልም የጎልጎታ እንጨት ነው"* ብለው ታላላቅ ሰዎች ተነሥተው እንደነበር ታሪክ ይናገራል። በጊዜው ለተነሣው የተሐድሶ (ወደ ቃሉ የመመለስ) ጥያቄ አፄ ያግብ ጽዮን፦

*እመቤታችን ተገልጸልኝ "ለሥዕሏና ለልጇ መስቀል መስገድ ይገባል" ብላኛለችና ያልታዘዘ "እንገቱ ለገመድ፣ ያከማቸው ንብረት ለሠራዊቱ፣ ቤቱ ለጠመንጃዬ አፎትና እሳት ይዳረጋል" ብሎ ስላወጀ ሕዝቡ ከፍርሃት የተነሣ "ንጉሡ ያለንን እናደርጋለን ለመስቀልና ለሥዕል እንሰግዳለን"*[116]

---

[116] *ደቂቀ እስጢፋኖስ ገጽ 23፣ የሚከተለው መጽሐፍ በግርጌ ጎዳግ ጠቅሰዋል።* K. Cont Rossini, *(1965 )'Vitae Sanctorum Indiginarum I Acta Marqoewos*, CSCO, vol.33/19, ,pp. 12-14